

## የሰሜን ተራሮች እሳት ወደ ገደላማ ቦታዎች ተዛመተ

ገጽ 9

### በውስጥ ገጾች


☞ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ

☞ዶክተር አክሎግ ቢራራ

☞ዶክተር ሼክስፒር ፈይሳ



# ኢትዮጲስ




ገጽ 4

## የሱዳኑ አልበሽር አምባገነናዊ አገዛዝ ተገረሰሰ


1ኛ ዓመት | ቁጥር 030 ሚያዝያ 6 ቀን 2011 ዓ.ም ዋጋ ብር 9.90


# “ጥቃት አድራሾቹ የኦነግ ታጣቂዎች ናቸው”

☞አንድ ሽማግሌ ታርደዋል፣ ሴቷ ታግተው ጠፍተዋል

☞ባልታጠቀ ህዝብ ላይ መትረየስ ተተኩሷል

☞በኃይማኖት ተቋማት ላይ ቦምብ ተወርውሯል

☞ህዝቡ ቤቱን እየለቀቀ ወደ ተራሮች ሸሽቷል

☞መከላከያ “ትዕዛዝ አልተሰጠኝም” ብሎ ተመልካች ነበር

☞የመከላከያ ደምብ ልብስ የለበሱ በርካታ ሰዎችን ገድለዋል



# ፍልሚያ በከሚሴና ሰሜን ሸዋ

ዝርዝር ዘገባ ገጽ 2 እና 3

# በከሚሴና በሰሜን ሸዋ ታጣቂዎች ጉዳት አደረሱ

## “ጥቃት አድራሾቹ የኦነግ ታጣቂዎች ናቸው”

- ☞አንድ ሸማግሌ ታርደዋል፣ ሴቷ ታግተው ጠፍተዋል
- ☞ባልታጠቀ ህዝብ ላይ መትረየስ ተተኩሷል
- ☞በኃይማኖት ተቋማት ላይ ቦምብ ተወርውሯል
- ☞ህዝቡ ቤቱን እየለቀቀ ወደ ተራሮች ሸሽቷል
- ☞መከላከያ “ትዕዛዝ አልተሰጠኝም” ብሎ ተመልካች ሆኖ ውሏል
- ☞የመከላከያ ደምብ ልብስ የለበሱ በርካታ ሰዎችን ገድለዋል


### የከሚሰው ጥቃት

በከሚሴና በሰሜን ሸዋ ሰሞኑን በተፈጸሙ ጥቃቶች ለብዙዎች ሞትና መፈናቀል፣ እንዲሁም ለንብረት ውድመት ምክንያት የነበረው ግጭት የተነሳው፣ ሆን ተብሎ በተሰራጨ ሀሰተኛ ወሬ ነው እየተባለ ይገኛል:: ባሳለፍነው ሳምንት መግቢያ ላይ ሲናፈስ የነበረው ወሬና አሉባልታ፣ የኦሮሞ ብሔረሰብ አስተዳደር የሆነው የከሚሴ ዞን ሊፈርስ ነው የሚል ይዘት ነበረው:: ከዚህ አሉባልታ በተጨማሪም፣ በአካባቢው ካለው ኃይማኖታዊ ሰላምና መከባበር በተፃራሪ፣ የእስልምና ተከታዮች ሊጨፈጭፉ ነው የሚል ሀሰተኛ ወሬ ሲናፈስ ነበር::

እነዚህ አሉባልታዎች በማህበራዊ ሚዲያዎች ብቅ ጥልቅ እያሉ ከሰነበቱ በኋላ፣ ውጥረቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያየለ ሄዶ፣ ረብዕ ማለዳ በገጠር አካባቢዎች ከፍተኛ ተኩስ ሊቀሰቀስ ችሏል:: እንደ አካባቢው ነዋሪዎት አገላለፅ፣ በደዌ ሃረዋ ወረዳ ለተቀሰቀሰው ግጭት አሉባልታው ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል::

ግጭት የተቀሰቀሰበት አካባቢ ከአፋር ክልል የሚያዋስን በመሆኑና፣ ከዚህ በፊትም አልፎ አልፎ ግጭት የሚነሳበት በመሆኑ፣ የአማራ ልዩ ኃይል በአካባቢው ይንቀሳቀስ እንደነበር ነዋሪዎቹ ይናገራሉ:: ከግጭቱ በፊትም ቢሆን፣ በአካባቢው መንደር የሚያቃጥሉና የህዝብን ሰላማዊ እንቅስቃሴ የሚያሰናክሉ ኃይሎች ስለነበሩ፣ ልዩ ኃይሉ እነሱን እንዲቆጣጠር ትዕዛዝ ተሰጥቶት በእንቅስቃሴ ላይ ነበር:: በዚህ ድባብ በአካባቢው ሲንቀሳቀስ የቆየው ልዩ ኃይል ረብዕ ወደ ገጠር አካባቢዎች ሲገባ፣ አየር ላይ በነበሩ አሉባልታዎች በተደናገሩ የአካባቢው ታጣቂዎች ተኩስ ተከፍቶበታል:: በዚህ ሁኔታ ግጭቱ መባባሱን ነዋሪዎች ይናገራሉ:: እንዲሁም፣ ልዩ ኃይሉ አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ባንዲራ በመያዙ የተበሳጩ በከሚሴ ገጠራማ አካባቢዎች የሚንቀሳቀሱ ታጣቂዎች ተኩስ ከፍተውበታል የሚል ወሬም በመሰማቱ፣ ለግጭቱ መባባስ አስተዋፅኦ ማበርከቱ እየተነገረ ይገኛል::

በዚህ መልክ በተነሳው የተኩስ ልውውጥ፣ የ4 ሰዎች ህይወት ማለፉን የክልሉ ቃል አቃባይ አቶ አሰማኸኝ አስረስ ተናግረዋል:: ቃል አቀባዩ፣ ከሟቾቹ መካከል የልዩ ኃይል አባላት እንደነበሩበት፣ 5 ሰዎች ደግሞ የመቁሰል አደጋ ደርሶባቸው በደሴ ሆስፒታል ህክምና ላይ እንደሚገኙ ገልፀዋል:: በግጭቱ ህይወቱ ያለፈ የአንድ የፀጥታ ባልደረባ የቀብር ስነ-ሥርዓት በደሴ ከተማ መጠነኛ ግርግር አስነስቶ የነበረ ሲሆን፣ ለተቃውሞው መንስኤ የሆነው ግጭቱ የሚዲያ ሽፋን አላገኘም የሚል ቁጣ እንደነበር ታውቋል:: እንደተባለውም፣ የኢትዮጲስ ዝግጅት ክፍል ባደረገው ማጣራት፣ ማክሰኞ ተቀስቅሶ ረብዕ የተባባሰው ይህ



ከ26 ታጣቂዎች ጋር ተፋልሞ፣ 26 መሣሪያዎችን ማርኮ (3 ስናይፐር) የተሰዋው ጥጋቡ ተፈራ

ግጭት፣ እስከ አርብ ድረስ በሚዲያ እንዳልተዘገበ ማረጋገጥ ችሏል:: ይህ ረብዕ የተባባሰው ግጭት፣ ሀሙስ ዕለት እየቀነሰ ሄዶ፣ አርብ ዕለት አንፃራዊ ሰላም ሰፍኖ መዋሉን የአካባቢ ነዋሪዎች ተናግረዋል::

ስለጥቃት አድራሾቹ ማንነት፣ የክልሉ ባለስልጣን አቶ ገደቤ ለመገናኛ ብዙሃን በሰጡት ማብራሪያ፣ “ራሱን በስውር ያደራጀ ያልታወቀ ቡድን” እንደነበርና፣ “ይህም ፀረ ሰላም ኃይል ማን እንደሆነ እያጣራን ነው:: ነገር ግን፣ በህቡዕ በተደራጀ መንገድ የሚንቀሳቀሱ የኦነግ አባላት ያሉ ነው የሚመስለው” ብለዋል:: ይህ ቡድን የተደራጀና የቡድን መሳሪያዎች የያዘ እንደነበረም አክለዋል::

### ከኦነግ ጋር የተነሳው ውዝግብ

ግጭቱ አርብ ላይ የቆመና የተፈታ ቢመስልም፣ አቶ ገደቤ ግን በሰጡት አስተያየት፣ ሰላም መጥቷል ማለት እንደማይቻል፤ ስራ እንደሚጠይቅ፤ የልዩ ኃይሉን ስምሪት እንደገና በማየትና ፈትሾ በማስተካከል፣ በህብረተሰቡ ዘንድ ያለውን ስጋት ለመቀነስ መስራት እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል:: ከነበረው ሁኔታ አኳያ፣ አለመረጋጋቱ ወደ ሰሜን ሸዋ አካባቢዎችም ሊከሰት እንደሚችል አስቀድመው ጠቁመዋል:: የግጭት አነሳሾቹን ማንነት አስመልክተውም በሰጡት አስተያየት፣ “አካባቢውን ለማተራመስ አጀንዳ ያለው፣ ከኦነግ አባላት ጋር ትስስር ያለው ቡድን እንደሆነ እያየን ስለሆነ፣ ለወደፊት ሊጣራና ሊገመገም ውጤቱ ይታወቃል” ብለዋል::

ለአቶ ገደቤና ለሌሎች የክልሉ ባለስልጣናት ወቀሳዎች ምላሹን በማህበራዊ ድህረ-ገጽ መግለጫ የሰጠው የኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦነግ፣) « የራስን ጥፋት ለመደበቅ የኦነግን ስም ማጠልሸት ከተጠያቂነት አያስመልጥም ፤ አሁንም ቢሆን ሰላማዊ ትግል ላይ ነን፤ የአማራ ልዩ ኃይሉ ተግባር የኦሮሞ ብሔረሰብ አስተዳደርን በማፍረስ ወደ ሌላ ዞን ለመቀላቀል የሚደረግ የድንበር ማስፋፋት ነው ብለን እናምናለን» በማለት “ተጠያቂው የክልሉ መንግስት እንጂ፣ እኛ አይደለንም “ብሏል:: “ክልሉ ግንባሩን ከመክሰስና የህዝቡን ሰላም ከማናጋት ሊቆጠብ ይገባዋል” ያለው ኦነግ፣ የፌዴራል መንግስቱ ችግሩ ወደ ሌላ አቅጣጫ እንዳይሄድ ቁጥጥር እንዲያደርግ ጠይቋል:: ግንባሩ ይህን የጠየቀው የሰሜን ሸዋው ግጭት ከመቀስቀሱ በፊት ነበር::


### የሰሜን ሸዋው ጥቃት

ቅዳሜ መጋቢት 28 የከሚሴው ግጭት ወደ አጎራባቹና የሰሜን ሸዋ ኤፍራትና ግድም ወረዳ የተሸጋገረ ሲሆን፣ የአይን እምኞች እንደገለጹልን ታጣቂዎቹ ገና ወደ ኤፌሶን/ አጣዬ ሲዘልቁ፣ ተራራ ላይ መትረየስ ጠምደው ወደ ህዝቡ ተኩስ መከፈታቸው ድንጋጤ ፈጥሯል::የተከፈተውን ድንገተኛ ጥቃት በጥይት ማነስ ሳቢያ ማስቆም ባለመቻሉ፣ ለመከላከል ሲሞክሩ የነበሩ የፀጥታ ኃይሎችና ሚሊሻዎች፣ እንዲሁም ሰላማዊ የከተማዋ ነዋሪዎች በአሰቃቂ ሁኔታ ህይወታቸውን አጥተዋል::

በዚህ ሁኔታ በሰሜን ሸዋ በተቀሰቀሰው ግጭት ከ40 የማያንሱ ሰዎች መገለዳቸውን የከተማዋ ነዋሪዎች ነግረውናል:: አንዳንዶች ደግሞ፣ ቁጥሩን ከ50 በላይ ያደርሱታል:: በሰሜን ሸዋ ጥቃት ከፈፀሙት መካከል በግምት ሦስት መቶ የሚሆኑ መገደላቸውን፣ አስከሬናቸውም በአይሱዙ ተጭኖ መጓጓዙን የአካባቢው ነዋሪዎች ለኢትዮጲስ ጋዜጣ ገልፀዋል::

በተፈጠረው ትርምስም የነዋሪው ስጋት በመጨመሩ ቀዬውን እየለቀቀ መሰደዱን በምስል ጭምር የታገዘ መረጃ ሲሰራጭ ሰንብቷል:: ህዝቡ ከተማ ያለውን ቤት እየለቀቀ ወደ ገጠራማ ቦታዎችና ወደ ተራራ ሸሽቷል:: ጥቃት አድራሾቹ ካጠፏቸው የሰው ህይወቶች ባሻገር፣ የንብረት ውድመትና ዘረፋ ፈፅመዋል:: እንዲሁም፣ ሰው

ወደ ቀጣዩ ገጽ 3



ከጥቃት አድራሾቹ ኪስ የተገኘ የኦነግ መታወቂያ


ጥቃት የደረሰበት ቤተክርስቲያን(ከቪዲዮ ምስል የተወሰደ)

እንዳገቱ፣ በተጨማሪም ቤተክርስቲያናት ላይ ቦምብ መወርወራቸውና ቃጠሎ ማድረሳቸው ታውቋል:: በሰሜን ሸዋ ይህንን ጥፋት ያደረሱት ኦነግ ያደራጃቸው ቡድኖች መሆናቸውን፣ ዓላማቸውም ሽብር ፈጥሮ ዝርፊያ መፈፀም እንደ ነበር ሲሉ የዞኑ ኃላፊዎች ለመገናኛ ብዙሃን ገልፀዋል::

የአጣዬ ከተማ ከንቲባ፣ በታጠቁት ኃይሎች የተካሄደው ጥቃትና ዘረፋ ከክልሉ ልዩ ኃይል አቅም በላይ ስለነበር በነጋታው መከላከያ ወደ ከተማዋ እንዲገባ ተደርጓል ብለዋል:: ከቤተክርስቲያናት ሌላ የንግድ ተቋማትና መኖሪያ ቤቶች የጥቃት አድራሾቹ ዒላማ እንደነበሩ የከተማዋ ነዋሪዎች ተናግረዋል::

በአጣዬ ከተማ ጥቃቱ ሲፈፀም የነበሩና የኢትዮጲስ ዝግጅት ክፍል ያነጋገርናቸው አንድ የአይን እማኝ፣ ታጣቂዎቹ ከስድስት ወራት በፊት በከተማዋ አቅራቢያ በሚገኝ ጫካ ውስጥ ሲሰለጥኑ የነበሩ ሲሆን፣ ነዋሪው ለከተማዋና ለዞኑ ኃላፊዎች ሲጠቁም፣ "ለበላይ አመልክተናል" የሚል ምላሽ እንደተሰጠው ገልፀውልናል::

ጥቃቱ በከተማዋ የተሰነዘረበት ዕለት፣ የቅዳሜ የገበያ ቀን ስለነበር፣ ነዋሪው ሳይታጠቅ ተዘናግቶ እንደነበርና፣ ጥቃት አድራሾቹ አካባቢውን ድንገት ከበው፣ በጉብታ የጠመዱትን መትረየስ በእሩምታ በመተኮስ ከባድ ጉዳት ለማድረስ ችለዋል:: አንዳንድ የከተማው ነዋሪዎችና ሚሊሻዎች አፀፋውን በተኩስ ቢመልሱም፣ የነበራቸው ጥይት አነስተኛ ስለነበር፣ መቋቋም አቅቷቸው ብዙዎች ህይወታቸውን እንዲያጡ ሁኔታዎች ምቹ ሆነዋል::

## በኦራል የተጫኑና የመከላከያ የደንብ ልብስ የለበሰ አጥቂ ኃይል

በቀጣይ፣ በተከላካይነት ለተሰለፉት ከመንግስት አካል ጥይት እንዲሰጥ ተጠይቆ እምቢ መባሉን የነገሩን እኚህ ነዋሪ፣ ከሞላ ጎደል ባዶ እጃቸውን ቅዳሜን ሲዋጉ መዋላቸውና ዋናው መንገድ መዘጋቱን ገልፅውልናል:: በዚያን ዕለት ከየትኛውም አቅጣጫ የሚረዳቸው ኃይል ሳይደርስላቸው እንደቀረም ይናገራሉ:: በዚህ ሁኔታ ውስጥ እያሉ፣ ከምሽቱ 3 ሰዓት ላይ የጣለው ከባድ ዝናብ ትልቅ እረፍት እንደሰጠና ከፍተኛ መተላለቅን እንዳስቀረ ይናገራሉ::

ቅዳሜ ዕለት በነበረው ውሎ፣ በውጊያው መሀል በአንድ ኦራል (የጭነት መኪና) "ልዩ ኃይል መጣ" ተብሎ የነበረ ቢሆንም፣ በተግባር ግን ጥቃት አድራሹ ኃይል (" የኦነግ ኃይል" ነው ብለው ነው የገለፁት ነዋሪው) ሆኖ ተገኝቷል:: "ብዙ ነዋሪም የሞተው በዚህ የመከላከያ የደንብ ልብስ በለበሰ ኃይል ነው" ብለውናል እማኙ:: ኦራሉ ይህን ዜና እስካዘጋጀንበት ወቅት እየተፈለገ እንደሆነም ሰምተናል::

የነዋሪውን ጥቃትና የጥይት እጥረት የቀረፈለት፣ ከላይ ከመንዝ ግሼና ራቤ የመጣ አጋዥ ኃይል እንደሆነና፣ ይህም ኃይል በቀጣዩ ቀን በነበረው ውጊያ የሰው ህይወት ለማትረፍ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማበርከቱን እማኙ ይናገራሉ::

በጥቃቱ ሴትና እናቶች ታግተው የተወሰዱ ሲሆን፣ አንድ ፀሀይ የምትባል እንጀራ በመጋገር የምትተዳደር ሴት በጥቃት አድራሾቹ ታግታ እስካሁን ድረስ የት እንደደረሰች አይታወቅም:: ከከተማው ምክር ቤት ፊት ለፊት የሚኖሩ ጡረታ የወጡ አቅመ ደካማ ሽማግሌንም፣ ከተደበቁበት አውጥተው እንዳረዷቸው፣ በዚህም ነዋሪው ክፉኛ ማዘኑን ሰምተናል:: አንድ የራያ ተወላጅ ተታኩሶ መሰዋቱንም እማኙ ነግረውናል::

## አንድ ኩንታል ጥይት

በቀጣይ ቀናትም፣ ሚያዝያ 1/2011 ዓ.ም ላይ አንድ ኩንታል ጥይትና አንድ መትረየስ ወደ አካባቢው ሊገባ ሲል ተይዟል:: እንዲሁም በአውቶቡስ ከወለጋ ተጭነው መጡ የተባሉ ወጣቶች ሸዋሮቢት ተይዘው ተለቀዋል:: እንደ እማኞችን እምነት ከሆነ፣ እንደ እነዚህ አይነት ክስተቶች፣ ጥቃቱ የተከሰተው በአጋጣሚ ሳይሆን ሆን ተብሎ ታቅዶበት የተደረገ መሆኑን ብቻ ሳይሆን፣ ወደፊትም ግጭቶች ሊከሰቱ እንደሚችል ያመላክታሉ:: በግጭቱ ሳቢያ ለተፈናቀሉት በደብረሲናና በሌሎች አካባቢዎች እርዳታ እየተሰበሰበ ሲሆን፣ መሃል ሜዳና ሞላሌ የገቡትን ስደተኞች ነዋሪው እያበላና እየረዳ ይገኛል::

## "ትዕዛዝ አልተሰጠኝም"

የእሁዱን ግጭት አስመልክቶ የወረዳው ባለስልጣናት በሰጡት አስተያየት፤ ጥቃቱ ሲፈፀም በቦንብና በከባድ መሳሪያ የታገዘ እንደነበር፣ ጥቃት የደረሰውም በተደራጁና ስልጠና በወሰዱ ቡድኖች የተፈጸመ መሆኑን ተናግረዋል::

እንደነዋሪዎቹ አስተያየት በቦታው የመከላከያ ሰራዊት የነበረ ቢሆንም « ትዕዛዝ አልተሰጠኝም» በሚል በተፈለገው መጠን ከጥፋት እንዳልታደጋቸው በማዘን ይናገራሉ:: መከላከያ ኃይሉ ቅዳሜ ዕለት ምንም ጣልቃ ሳይገባ ከቆየ በኋላ፣ እሁድ ዕለት "ኃይሌ አነስተኛ ነው" በማለቱ፣ ተጨማሪ ኃይል ተልኮለት፣ ከቀኑ 9 ሰዓት ገደማ ተጨማሪ ኃይል ደርሶለት በአካባቢው መንቀሳቀስ በመጀመሩ ግጭቱ መቀነሱን ይናገራሉ:: እሁድ ማምሻውን በከተማ ተረጋጋ የተባለው ግጭት፣ ሰኞ መጋቢት 30ም እንደገና አገርሽቶ፣ በገጠራማ አካባቢዎች እና በመንገድ ዳርቻዎች የፀጥታ ችግር ተፈጥሯል::

ሰኞ ዕለት ማብራሪያ የሰጡት የኢፌዴሪ መከላከያ ሚኒስቴር ኢታማዦር ሹም ጽ/ቤት ኃላፊ ኮሎኔል ተስፋዬ አያሌው፣ በክልሉ ጥያቄ መሰረት መከላከያ ሰራዊቱ ወደ አካባቢው መግባቱንና አልፎ አልፎ ተኩስ መሰማቱንም ተናግረዋል:: ቦታው ሰፊ በመሆኑና ተጨማሪ ኃይል በማስፈለጉ አካባቢውን ሙሉ በሙሉ መቆጣጠር አለመቻላቸውንና፣ የግጭቱን መንስኤ እያጣሩ እንደሆኑ ተናግረዋል:: "በሁለቱም ወገን ያለው ታጣቂ በመሆኑ፣ የአካባቢው አመራሮች ከጉዳዩ እጃቸውን ሊያወጡ ይገባል" ብለዋል:: የኮሎኔሉ አባባል ጥቃት በደረሰባቸው በኩል ጥሩ ስሜት አልፈጠረም::

## የጥይት ጉዳይ

ከኤፌሶን/አጣዬ ተነስቶ ወደ ማጀቴ ገጠራማ ክፍል በዘለቀው ግጭት፣ ተጠቂው አርሶ አደርና ሚሊሻው ራሱን ለመከላከል ሲታኮስ ጥይት አልቆበት ተጨማሪ እንዲሰጠው ቢጠይቅም፣ በቦታው በነበሩ ኃላፊዎች መከልከሉን ነዋሪዎች እማኝነታቸውን ሰጥተዋል:: በዚሁ ዕለት፣ 990 የክላሽ ጥይት በህገ-ወጥ መንገድ ከአፋር ክልል ወደ ወሎ መስመር ሲጓጓዝ፣ ሚሌ ባቲ መገንጠያ ባለው የጉምሩክ ኬላ ላይ ተይዟል:: እንደ ብዙዎች ግምት ከሆነ፣ ጥይቱ ለጥቃት አድራሾቹ የተላከ ነበር:: የሰሜን ሸዋ ዞን ኮንስታብል ሰኢድ እንድሪስ ለመገናኛ ብዙሃን በሰጡት አስተያየት፣ ለኦነግ አባላት (ለጥቃት አድራሾቹ) የሚያስታጥቁት የኦሮሞ ብሔርሰብ አስተዳደር ልዩ ዞን ባለስልጣናት ናቸው ብለዋል::

ግጭቱን ተከትሎ በደብረብርሃን ከፍተኛ ህዝብ ጎዳና ወጥቶ የተቃውሞ ድምፅ አሰምቷል:: እንዲሁም፣ በአዲስ አበባም የሚገኙ 500 የሚጠጉ የአካባቢው ተወላጆች ድርጊቱን በማውገዝ የአቋም መግለጫ አውጥተዋል:: ግድያውን አፈናውንና ዘረፋውን የፈጸሙትን መንግስት በአፋጣኝ እርምጃ ይዞ ለፍርድ እንዲያቀርባቸው፣ እንዲሁም፣ ተጨማሪ የፀጥታ አካላት እንዲመደቡ፣ በጥቃቱ የተጎዱም አፋጣኝ እርዳታ እንዲያገኙ ጠይቀዋል:: ግጭቱ ታስቦበት ታቅዶና



ተጠንቶ የተደረገ እንጂ ተራ በአካባቢው የተለመደ ግጭት አለመሆኑን፣ ታጣቂዎቹ ስልጠና ወስደው፣ ግለሰብ የማይዘውን ከባድ የቡድን መሳሪያ ታጥቀው በዓላማ ነው ያጠቁት ብለዋል::

ይህን ተከትሎ፣ ሰኞ መጋቢት 30 የፌዴራልና የክልል የፀጥታ አካላት « አስፈላጊውን ህጋዊ ተመጣጣኝ እርምጃ» እንዲወስዱ የኢትዮጵያ ብሔራዊ የፀጥታ ምክር ቤት አዟል:: ምክር ቤቱ ጥቃቱን « ብጥብጥ» ነው በማለት፣ እጁ ያለበት ማንኛውም አካል ተጠያቂ እንደሚሆን፣ ያነሳሱትን ለህግ ለማቅረብ ጥናት የሚያደርግ ቡደን ማሰማራቱንም አሳውቋል::

ይህን ጥቃት የፈፀሙት የኦነግ ታጣቂዎች መሆናቸውን የክልሉ ኃላፊዎችና በቦታው የነበሩ እማኞች ቢናገሩም፣ ግንባሩ ግን በድጋሚ አስተባብሎታል:: ቃል አቀባዩ አቶ ቶሌራ አዳባ፣ "በአማራ ክልል የሚንቀሳቀስ ምንም የታጠቀ ኃይል የለንም" ብለው ለዶቼቬሌ ቢናገሩም፣ የኦሮሞዎች አባ ገዳ የሆኑት አቶ በየነ ሰንበቶ፣ ከወራት በፊት በሰሜን ሸዋ ከሚሴና ከረዩ የሚገኝ የኦነግ ጦርን በማስመልከት፣ "ከአማራ ክልል ጋር እንነጋገርበታለን" ማለታቸው ይታወሳል::

የኦነግ ቃል አቀባዩ ለጥቃቱ ተጠያቂ ያደረጉት፣ አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ሰንደቅ ዓላማ የያዙ አካላት ሰንደቅ ዓላማ ይዘው ወደ አካባቢው መሄዳቸው ነው ብለዋል:: ይህ አባባላቸው፣ በከሚሴ ይንቀሳቀስ በነበረው የአማራ ክልል ልዩ ኃይል ላይ ተኩሱ የተከፈተው፣ አረንጓዴ ቢጫ ቀይ የሆነውን ሰንደቅ ዓላማ በመያዛቸው በተበሳጩ የኦነግ ታጣቂዎች ነው በማለት ነዋሪዎች የተናገሩትን የሚያረጋግጥ ሆኗል:: የኢትዮጲስ ዝግጅት ክፍል ያነጋገርናቸው የአካባቢው ነዋሪዎች፣ ከሟቾች ላይ የኦነግ መታወቂያ እንደተገኘ ታጣቂዎቹ አርማውን በተለያየ መንገድ እንደሚጠቀሙበት ለማወቅ ተችሏል::

ሚያዚያ አንድ ቀን ሰለ ወቅታዊው ሁኔታ መግለጫ ያወጣው ገዢው ፓርቲ የኦሮሞ ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ (ኦዴፓ፣) ጥቃት አድራሾቹን፣ "በህዝብ ደም የሚነግዱ የፖለቲካ ቁማርተኞች" ያላቸው ሲሆን፣ ጥቃቱን ደግሞ "በየትኛውም መልኩ ተቀባይነት የሌለው፣ ማንኛውንም ህዝብ የማይወክል" ነው ብሎታል::

"ግጭቱ የተቀሰቀሰውም ጽንፈኛ ኃይሎች ከከሰሩ የፖለቲካ ኃይሎች ጋር በመቀናጀት የለኮሱት እሳት ነው ያለው" የፓርቲው መግለጫ፣ "የህዝብ ለህዝብ ግጭት በማስመሰል፣ ችግሩ ወደ ኦሮሚያ ክልል እንዲስፋፋ በማድረግ፤ ወንድማማች ህዝብን ለማጋጨትና በእሳቱ ለመማገድ የታሰበ፣ የፖለቲካ ትርፍ ለማጋበስ አቅደው የተንቀሳቀሱበት ነው" ብሏል:: ግጭቱ እንዳይዛመት፤ ቀስቃሾቹንና ጥፋተኞቹን ለማወቅ እንዲሁም ለመያዝ ከአማራ ክልል ጋር አብሮ እየሰራ መሆኑንም አሳውቋል::

# ሰሞኑን በከሚሴና በሰሜን ሸዋ ያየነው

በግምት ከ8 ወራት ቢፊት፣ ዐቢይ አህመድ በምድረ አሜሪካ ጉብኝት ላይ ነበሩ። ያኔ ስልጣን ከያዙ ገና 4 ወራት ብቻ ስለነበር፣ ቁመናቸውና የአነጋገር ቃናቸው ልበ ሙሉነት ይታይበት ነበር። ህዝቡም፣ በወጣት መሪው የራስ መተማመን መንፈስ ውስጥ ለሀገሩ ብሩህ ተስፋ ያየበት ጊዜ ነበር፤ በዋሽንግተን የተደረገላቸው የሞቀ አቀባበል የፈነደቀውን ተስፋ አንፀባርቋል። በዚህ የተስፋ ወጋገን ነበር ጠ/ሚ/ሩ ስለ ሽግግር መንግስት ተጠይቀው፣ "የሽግግር መንግስት አያስፈልገንም፣ እኔ አሻጋግራችኋለሁ" የሚል ምላሽ የሰጡት።

ኢትዮጵያን በመሳሰሉ እጅግ የተወሳሰበ ፖለቲካ ባላቸው ሀገራት ግን፣ ወደ ዲሞክራሲያዊ ስርዓት የሚደረግ ታሪካዊ ሽግግር ከአንድ ግለሰብና ከአንድ ድርጅት አቅም በላይ ነው። "እውነትና ንጋት እያደር ይጠራል" እንዲሉ፣ ይህ እውነታ ባለፈው አንድ ዓመት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጠራ በመሄድ ላይ ይገኛል።

በዚህ ሂደት፣ ያሳለፍነው የአንድ ዓመት ጉዞ ዋናኛ ክስተት የፌደራል መንግስቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተዳከመ መሄድ ሆኖል። በሀገሪቱ በአራቱም አቅጣጫዎች የሚፈነዱት ግጭቶች የዚህ እውነታ ዋነኛ መገለጫዎች ናቸው። ይህን ሁኔታ መረዳትና መቀበል የመፍትሄው ግማሽ አካል ነው፤ በተቃራኒው፣ እውነታውን በአግባቡ አለመረዳት ከመፍትሄው ጋር ሆድና ጀርባ ያደርገናል። በኦህዴድ/ኦ.ዴ.ፓ የሚመራው ማዕከላዊ መንግስት ይህን እውነታ እንደምንም ብሎ ከተቀበለ፣ የሚቀጥለው ጥያቄ የሚሆነው፣ የማዕከላዊ መንግስቱን ጥንካሬ ለማስመለስ ምን መደረግ አለበት? የሚለው ይሆናል።

በሀገሪቱ ውስጥ ያለው የኃይል ሚዛን ሲቃኝ፣ በአንድ በኩል፣ የሰው ብዛትና የጦር መሳሪያን ብዛት እንደ ልኬት የምንወስደው ከሆነ፣ ግልፅ ወታደራዊ የበላይነት ያለው በፌደራል መንግስቱ እጅ ነው። ይህ ሰራዊት ከውጭ ጠላት ጋር ካልሆነ፣ በአሁኑ ጊዜ በሀገር ውስጥ የመዋጋት ፍላጎቱ በጣም የቀዘቀዘ ነው። በሌላ በኩል፣ ለየክልል መስተዳድሮቻቸው ታማኝ የሆኑና ቁጥራቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ የሚገኙት የክልል የፀጥታ ኃይሎች ይገኛሉ። በአንፃሩ፣ እነዚህ ደግሞ፣ በየትኛውም ዓይነት ውጊያ ለመሳተፍ ከፍተኛ ጉጉት የሚታይባቸው ናቸው።

ከእነዚህ የክልል ኃይሎች መካከል፣ ከፌደራል መንግስቱ ወታደራዊ ኃይል ጋር በተፎካካሪነትና በጠላትነት ቁመና ላይ የሚገኙት የትግራይ የፀጥታ ኃይሎች ይገኛሉ። እነዚህ የትግራይ የፀጥታ ኃይሎች ለሌሎቹ የክልል ኃይሎች መጥፎ አርአያ ሆነው፣ ሌሎቹም እንደ እነሱ "አልታዘዝም" ባይ ጡንቸኛ መሆን መፈለጋቸው፣ የማዕከላዊ መንግስቱን ህልውና አደጋ ላይ ጥሎታል። የፌደራል መንግስቱ ግልፅ የሆነ የበላይነቱን ማስረገጥ ከፈለገ (ማስረገጥም አለበት፣) የትግራይ ፀጥታ ኃይሎች ተፎካካሪውና ተቀናቃኙ ሊሆኑ እንደማይችሉ በግልፅ ማሳየት አለበት። ይህን ማድረግ ከቻለ፣ ቀሪዎቹ የክልል ኃይሎች በቅፅበት ወደ መስመር ይገባሉ። በዚህ ድባብ፣ የፌድራል መንግስቱ እንደቀድሞው የሚደመጥና የሚከበር ኃይል ይሆናል።

ፌድራልዝም ማለት የስልጣን ክፍፍል እንጂ፣ በአንድ ሀገር ሁለት መንግስታት ይኖራሉ ማለት እንዳልሆነ ሁሉ፣ በአንድ ሀገር ሁለት፣ ወይንም ከዚያ በላይ፣ የሆኑ ተፃራሪ ወታደራዊ ኃይሎች ይኖራሉ ማለት አይደለም። በፌድራሊዝም አንድ ሀገራዊ ሰራዊት ነው ያለው፤ ሌሎች ታጣቂዎች ሁሉ ለዚህ ኃይል ታዛዥና ተገዥዎች ናቸው። አሁን በኢትዮጵያ ያለው ሁኔታ፣ ዩጎዝላቪያ ወደለየለት የእርስ በእርስ ጦርነት ከመግባቷ በፊት ከነበረችበት ሁኔታ ጋር ተመሳስሏል። ሁኔታው አንድ መፍትሄ ይሻል፤ ባለበት ሊቀጥል አይችልም።

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ግን፣ አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ፣ "የአበጠው ይፈንዳ" በሚል ስሜት፣ የፌደራል ሠራዊቱንና የትግራይን የፀጥታ ኃይሎች በጦር ሜዳ በማጋጠም ወደ መፍትሄ መሄድ አይቻልም። የፌድራል ሠራዊቱ ይህንን ግዳጅ ለመወጣት ያለው ስነ ልቦናዊ ዝግጅት አጠራጣሪ ነው። ስነ ልቦናዊ ዝግጅቱን አስተማማኝ ለማድረግ ብዙሃኑ ኢትዮጵያዊያንን በጋራ ራዕይ ዙሪያ የሚያስተሳስራቸው የፖለቲካ ቀመር ማምጣት ያስፈልጋል። ይህ የጋራ ራዕይ ነው የማዕከላዊ መንግስቱን ትዕዛዝ ተቀብሎ መሬት ላይ ለማዋል የሚችል ሀገራዊ ሰራዊትና የፀጥታ ኃይል መፍጠር የሚያስችለው።

የፌደራል ሠራዊቱ የስነ ልቦና ጉድለት የፌደራል መንግስቱ የፖለቲካ ድክመት ውጤት ነው፤ የፌድራል መንግስቱ የፖለቲካ ድክመት ደግሞ፣ የኢህአዴግ ድክመት ውጤት ነው፤ የኢህአዴግ ድክመት የጋራ የሆነ ሀገራዊ ራዕይ መደብዘዝ ነፀብራቅ ነው፤ እንዲህ እንዲህ እያለ፣ አንዱ ከአንዱ ጋር የተሳሰረ ነው፤ ፈረንጆቹ Chain of events (አንዱ አንዱን የወለደ ክስተት) እንደሚሉት ማለት ነው።

ጠ/ሚ/ሩ የተዳከመውን ኢህአዴግ ብቻ ይዘው፣ በቃላቸው መሰረት፣ ሀገሪቷን ወደ ዲሞክራሲ ማሻገር አይችሉም። ለነገሩ፣ እንኳን የተዳከመውን ኢህአዴግ ይዘው ይቅርና፣ ጠንካራው ኢህአዴግንም ይዘው ቢሆን እንኳን፣ ይችን ሀገር አንድ ድርጅት ብቻ ወደ ዲሞክራሲ ሊያሸጋግራት አይችልም።

ወደ ቁም ነገሩ እንምጣ። በመርህ ደረጃ፣ ዲሞክራሲ፣ የጋራ ሀገራዊ ራዕያችንና ግባችን ሊሆን ይችላል። አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ግን፣ አንዳችን አሻጋሪ፣ ሌሎቻችን ተሻጋሪ ሆነን፣ በሂደቱ ላይ የጋራ ባለቤት መሆን ስላልቻልን፣ ሃሳባችን ተበትኗል፣ አካሄዳችን ተበትኗል፣ ከዚያም አልፎ ራዕያችንንም እየበተነው ይገኛል። ይሄ ነው ማዕከላዊ መንግስቱን አዳክሞ እርስ በእርስ እያጋጨን (ሰሞኑን በከሚሴና በሰሜን ሸዋ እንዳየነው) ወደ ስርዓት አልበኝነት እያንዳረደረን የሚገኘው።

ወደ ዲሞክራሲ በምናደርገው የሽግግር ጉዞ አንዱ አሻጋሪ፣ ሌሎቻችን ሁሉ ተሻጋሪ መሆናችን ብዙ ችግሮችን ወልዷል፤ እነዚህ ችግሮች በሀገር ሰላም ላይ ብቻ ሳይሆን፣ በሀገር አንድነትም ላይ አደጋ ሆነዋል። ኢትዮጵያ የሀገርን ሰላምና አንድነት ለማስጠበቅ የሚችል የሞራልና የፖለቲካ አቅም ያለው ማዕከላዊ መንግስትና የሚታዘዘው ጠንካራ ሠራዊት በአፋጣኝ ትሻለች። ይህን እውን ለማድረግ መምከር የሁሉም ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዊያን ቀዳሚ ተግባር መሆን ይገባዋል።



# የሱዳኑ አልበሽር አምባገነናዊ አገዛዝ ተገረሰሰ

የሱዳኑ ፕሬዚዳንት ኦማር አልባሽር የሶስት አስርት ዓመታት አገዛዝ አበቃ። ፕሬዚዳንቱ ትላንት በመኖሪያ ቤታቸው ታግተው ከስልጣናቸው ወርደዋል። በምትካቸው የሀገሪቱ ምክትል ፕሬዘዳንትና መከላከያ ሚኒስተር የሆኑት ሌተናል ጀኔራል አዋድ ኢብን አውፍ ሥልጣን ይዘዋል።

አልበሽር ወዲያው በቁጥጥር ስር መዋላቸው በሀገሪቱ ብሄራዊ ጣቢያ ተገልጿል። አዲሱ መንግስት ለ2 ዓመታት እንደሚቆይ የተነገረ ሲሆን፣ የሶስት ወራት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አስነግሮ ህገ መንግስቱን አግዷል። በተጨማሪም፣ የአየር ክልል ለ24 ሰዓት የየብስ ድንበሮቹን ደግሞ ላልተወሰነ ጊዜ ዘግቷል። አልባሽር ለደህንነታቸው ሲባል በሚስጥራዊ ቦታ እንዲቆዩ መደረጉን፣ በሁለት ዓመታት ውስጥ ምርጫ እንደሚደረግ ተገልጿል። አልበሽር ከስልጣን ከመውረዳቸው ጥቂት ጊዜ በፊት በርካታ መኪኖች ቤተመንግስታቸውን ከበው የተቃውሞ ድምፅ እያሰሙ ነበር።

ለአራት ወራት በተቃውሞ ስትናጥ የቆየችው ሱዳን፣ እ.ኤ.አ ሚያዚያ 6 ቀን 2019 ተቋውሞው ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰበት ዕለት የነበረ ሲሆን፣ ዕለቱ የቀድሞ የሀገሪቱ ፕሬዝዳንት ጃፋር ኑሜሪን በ1985 ዓ.ም ግጭት አልባ በሆነ ህዝባዊ ተቃውሞ ከስልጣን የወረዱበት ቀን ነበር።

ተቃውሞው ከሰሜናዊዋ የአትባራ ከተማ የጀመረ ሲሆን፣ የመጀመሪያው ዓላማ ኢኮኖሚያዊ አጀንዳ ላይ ያተኮረ ነበር። ይሁንና ቀስ በቀስ ጥያቄው ፖለቲካዊ

ወደ 21 ዞሯል

**ሥራ አስኪያጅ፡- እስክንድር ነጋ**
ጉለሌ ክ/ከተማ፣ ወረዳ 03 ፣
የቤ.ቁ.434

**ዋና አዘጋጅ፡-** ጌጤ ታደሰ
አዲስ ከተማ ክ/ከተማ፣
ወረዳ 04፣ ቤ.ቁ.273

**የዚህ ሣምንት የአምድ ተስተናጋጆች**
ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ
ዶክተር አክሎግ ቢራራ
ዶክተር ሉክ ፓቲ
አማንዳ ስፐርበር
ከንፉ አሰፋ

**ኮምፒውተር ጽሁፍ**
ፍቅሬ ታደሰ

**ሌይ አውት ዲዛይን**
ሀብታሙ መኮንን

መስከረም 12/2011 ዓ.ም ተመሰረተ፡፡
ዘወትር ቅዳሜ የሚታተም ሳምንታዊ ጋዜጣ
አሳታሚ፡- ናሁእ ኃ.የተ.የግ.ማ
አታሚ፡- ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፣
አራዳ ክ/ከተማ ቀበሌ 17/የቤት ቁ.984

**አድራሻ**
አዲስ አበባ፣ አራዳ ክ/ከተማ
ወረዳ 09፣ አራት ኪሎ፣
ቤት.ቁ 3-13 ሦስተኛ ፎቅ፣
ስልክ 0930 59 44 88
email- ethiopis27@gmail.com



**ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ**
**ደራሲ፣ ተርጓሚ፣ የታሪክ አጥኚና የቋንቋ ሊቅ**
**አሜሪካ**

# የአንድ ዓመት አስተዳደርና አዲስ ራእይ



ከሁሉ አስቀድሜ፣ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስቴራችንን ዶክተር ዐቢይ አሕመድን፣ "እንኳን የአንድ ዓመት የሥልጣን ዘመኖን ለማክበር አበቃዎ" እላለሁ። መሪዎች እንደሚያደርጉት፣ በዚህ አንድ ዓመት ውስጥ ለኢትዮጵያ ያበረከቱትን ሲገልጹልን በጸጥታ አዳምጫለሁ። የተቻለውን ያህል እንደኔ በየቀኑ ለሚከታተለዎ፥ ብዙዎቹን ሥራዎች በተፈጸሙ ጊዜ ስለሰማቸው፥ የጆሮ ምስክር ሊሆን ይችላል።በበኩሌ ዋና ዋና ሥምረቶች የምላቸውን አራቱን ልመስክር።

### ሥምረቶች፤
### አንደኛ፥

ኢሕአዴግ ራሱ ደንግጎ ራሱ የጣሰውን ሕግ (አብዛኛው ሕዝብ የጠላውን ሕገ መንግሥት) አስከብረዋል። እዚያው ከዓዋጁ የቀረው የመናገርና የመጻፍ የመሰብሰብ መብታችን ተለቆልን ሳንገላመጥ እንጽፋለን፥ እንናገራለን፥ እንሰበሰባለን። ሆኖም፥ ባልደራስ አዳራሽ የተሰበሰበው የአዲስ አበባ ሕዝብ ባላደራዎቹ (ወኪሎቹ) ለሁለተኛ ጊዜ እንዳይሰበሰቡ መከልከላቸውን ስሰማ፥ በሳቸው ላይ ያለኝ እምነት ለመጀመሪያ ጊዜ ተናጋ። "ከዕውቀት ማነስና ከሁኔታዎች አለመመቸት" ያሉትም አላጽናናኝም። የሚሻለው አማካሪ ያሳሳታቸው እንደፈጠረው እንቅፋት ቈጥረን ስናልፈው እሱም ያልፋል ማለቱን መርጫለሁ። በስደት ምክንያት ከሀገራቸው ከዘመዶቻቸው ተለያይተው የቀሩ ኢትዮጵያውያን ሀገራቸው ሊገቡ ችለዋል።

### ሁለተኛ፥

የሀገሪቱ ካዝና በመዘረፉ ምክንያት፥ የውጪ አገር የኢንዱስትሪ ምርት መግዛት ስላልተቻለ፥ ሥራ ቆሞ ነበር። ጠቅላይ ሚንስቴሩ ከየትም ከየትም ብለው ኢኮኖሚውን ሊያንቀሳቅስ የሚያስችለው ዶላር አስገኝተዋል፤ የብድሮችን ክብደት የሚያቀሉ ዘዴዎችን አግኝተዋል።

### ሦስተኛ፥

ራሱ ሰላም አጥቶ ዓለምን ሰላም የነሣውን የአፍሪካ ቀንድ ሕዝቦች ችግር በተአምራታዊ ቅጽበት ለውጠውታል። በጎሪጥ የሚተያዩ መሪዎች ኅብስት ከአንድ ገበታ ቈረሱ። ያዝልቅላቸው።

### አራተኛ፥

የሀገሪቱ ባለሥልጣኖች ገጽታ በአብዛኛው "አበበ፥ ወንዳፍራሽ፥ ገብረ ክርስቶስ፥ ካሕሳይ፥ ዘርአ ቡሩክ፥ ኀይቶም፥ ወልደ ማርያም. . ." መሆኑ ቀርቶ፥ "መገርሳ፥ መኰንን፥ ጣይባ፥ ገመቹ፥ ዳውድ፥ ገልቱ፥ ሐቢባ፥ ፍቅርተ፥ ኂሩት፥ አይሻ፥ ደመቀ . . ." ሆኗል።

### በተቃራኒ፤

ከግራኝ ዐመፅ ወዲህ ኢትዮጵያ ላይ ታይቶ የማይታወቅ ሰው-ሠራሽ መፈናቀል ተፈጽሟል። የረኀቡ ክብደት እንደ ድርቅ ዘመን የውጪ እርዳታ የሚያስፈልገው ሆኗል።

### ሰው ሠራሽ ችግር፤

ሰው ሠራሹ የጎሳ ፖለቲካ እስካልተሻረና ክልል እስካልፈረሰ ድረስ፥ በአንድ ዓመት ውስጥ ከዚህ የበለጠ ለውጥ ማምጣት አይቻልም። ይህን ያህልም ቢሆን የተቻለው፥ ዶክተር ዐቢይ ሥልጣን ከመያዛቸው በፊት ያሰቡበት ቢሆን ነው። ሕዝቡ (እኔን ጨምሮ) ለውጥ እንደመጣ ያመነው፥ ዶክተር ዐቢይ፥ "ኢትዮጵያ ሀገራችንን አምላክ ይባርካት" ሲሉ የሰማን ጊዜ ነው። ኮሚኒዝም አገራችን ሥር ከሰደደበት ጊዜ ጀምሮ፥ የኢትዮጵያ አምላክ ስሙ በሀገሪቱ መሪ ተጠርቶ አያውቅም ነበር። ይህ አምላክ አምላኪ ሕዝብ ከዶክተር ዐቢይ አፍ የወጣውን ሲሰማ፥ የሚፈልጋትን ኢትዮጵያ የሚሰጠው መስሎት ጨፈረ፤ ሰከረ። ሕዝቡ ዶክተር ዐቢይን ሲያምን፥ ያየው ኢትዮጵያዊ መሆናቸውን እንጂ፥ የኦሮሞ ፓርቲ ምልምልና ኩትኩት መሆናቸው ትዝ አላለውም። ዶክተር ዐቢይም ምንም ግራ ሳይጋቡ ባደጉበት ቤትና ንግግራቸው በማረከው ቤት እኩል ቤተኛ ሆኑ--ሁለት ትዳር ያዙ፤ ሁለት ቤት እንዳለው የእስላም ሼኽና እንደ ዱሮ የኢትዮጵያ ነገሥታት።

### አንድ አሽከር ለሁለት ጌታ፤

ግን መጽሐፉ እንደሚለው አንድ አሽከር ለሁለት ጌታ አይገዛም። አንዱን ይጠላና ሁለተኛውን ይወዳል፤ ወይም ወዳንዱ ይጠጋና ሁለተኛውን ይንቃል። ዶክተር ዐቢይ እዚያ ቤት ሲሄዱ፥ የዚህ ቤት ሕዝብ ያጕረመርማል። እዚህ ቤት ሲገቡ፥ የዚያ ቤት ሕዝብ ያጕረመርማል። ሁኔታው እንዲያውም ከትዳር ያልፋል። የሁለት ሃይማኖት ካህን መሰሉ--ዓርብ ዓርብ በመስጊድ ኢማም፥ እሑድ እሑድ በቤተ ክርስቲያን ቆሞስ እንደመሆን ማለት ነው። ዶክተር ዐቢይ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስቴር ሲሆኑ ጠቅልለው የኢትዮጵያ መሪ መሆን አልታያቸውም፤ ወይም "ሁኔታው አላመቻቸውም"።

በዚህ ምክንያት የአዴፓና የኢትዮጵያ መሪ ርእዮተ ዓለም "ሞት የማይለያቸው" መንታዎች ወይም አንድ አካል ሁለት ራስ ያለው ፍጡር ሆኑ። በኢትዮጵያ ሕዝብ ብዙ ሕዝቦችነትና በአንድ በሕዝብነት የሚያምኑ ሁለት የማይጣጣሙ ወገኖች አለቃ መሆን የሚነግርል ሰው ወይም የሚሰማ ጆሮ አጣን።

### ማነው ጨቋኙ?፤

ዶክተር ዐቢይ የመጡት "የአማራው መንግሥት ጨቋኝ ነው" ከሚለው ወገን ነው። እንዲህ ከሆነ፥ ያንን መንግሥት ሲወርሱ፥ መጀመሪያ ያ እምነት ስሕተት መሆኑን በይፋ ማመን ወይም የኢትዮጵያን ታሪክ ከታሪክ ምሁራን ጋር ተከራክሮ መርታት ወይም "አጉራህ ጠናኝ" ማለት ነበረባቸው። እሳቸው ግን አንድ ጊዜ የኢትዮጵያን ገናናነት (የጎሳ ጭቆና የለም እንደሚሉት)፥ ሌላ ጊዜ የጎሳ ጭቆና ነበረ የሚሉትን እየደገሙ ያዘግማሉ።

እስከ መቼ ነው በጭቈና እያመካኙ ሀገሪቷን በክልል፥ ሕዝቧን በርእዮተ ዓለም አጣርሶ ለማስተዳደር የሚቻለው? ክልሉም ሆነ የጎሳው ርእዮተ ዓለም የተፈለሰፉት ሕዝብን ለመጕዳት፥ መሪን ለመጥቀም መሆኑን መቀበል አለባቸው። ውይይቱን የፈሩት "ዓሣ ጐርጓሪ ዘንዶ ያወጣል" በማለት ከሆነ፥ የተዛባውን ትርክት (የአብየን ለእምየ) ወዲያ ቀብረን ወደፊት እንገሥግሥ።

ጎሰኝነትን የሚፈልጉ ኋላ-ቀር ወገኖች እንዳሉ እናውቃለን። መኖርም መብታቸው ነው። ግን በምን ምክንያት ነው "ጎሰኝነት ከፋፋይና አገር አጥፊ ነው" የሚለው ብዙኀኑ ሕዝብ ለኋላ-ቀሮቹ ተገዢ የሚሆነው? ሥልጣን በነሱ እጅ ስለሆነ ነው ከተባለ፥ የዲሞክራሲን ስም አናጥፋው። በበኩሌ ዶክተር ዐቢይ ለሀገር አንድነት እንደሚሠሩ አምናለሁ። መዳኒቱ፥ በእናታችን (በኢትዮጵያ) መጠራት ነው ያሉት ግን ከውይይት የሚያልፍ ቁም ነገር አይደለም። መፍትሔው ኢትዮጵያን ወጥሮ የያዛትን የጎሰኝነት ፍልስፍናን መሻር ነው።

### "እኔ አሻግራችኋለሁ"፤

ይልቅስ "እኔ አሻግራችኋለሁ" ያሉትንና "ኢሕአዴግን ወደ አንድ ኢትዮጵያዊ ፓርቲ እንለውጣለን" ያሉት የሚያጓጓ ነው። በነዚህ ጉዳዮች ላይ ሙሉ ተስፋ እንድንጥልባቸው፥ ከምን ወደ ምን እንደሚያሻግሩን ይንገሩን? ብዙኃኑ ወደሚፈልጉት ዲሞክራሲ ከሆነ፥ መጀመሪያ፥ የምክር ቤቱ ይፈታና አባላቱ ይሰናበቱ። ዶክተር ዐቢይ ከሚንስትሮቹ ጋር ሆነው ሀገሪቱን በጊዜያዊ መንግሥትነት ይምሩ። ሚስት ያለባል፥ መንግሥት ያለመሪ አይኖሩም ይባላል።

ሁለተኛ፥ ለጎሳዎች ማኅበራዊ መብታቸውን፥ ለሕዝቡ ፖለቲካዊ መብቱን የሚያስጠብቅ አዲስ ሕገ መንግሥት ይረቀቅ። ዲሞክራሲን ያስፋፉ ብዙ ጎሳዎች ያሏቸው አገሮች ሕገ መንግሥት ትምህርት ሊሰጥ ይችላል።

ሦስተኛ፥ ፓርቲዎች ለምርጫ እንዲዘጋጁ ፍጹም ዕድል (ጊዜና ነፃነት) ይሰጣቸው። ዶክተር ዐቢይ፤ ይህ

ወደ 20 ዞሯል



ዶክተር አክሎግ ቢራራ
የዓለም ባንክ አማካሪ የነበሩ
አሜሪካ

# የብሄር ፌደራሊዝም ካለ የብሄር ፖለቲካ የግድ ይኖራል

## "ተፎካካሪ ፓርቲዎችና" የኢትዮጵያ ብሄራዊ አንድነት

በቅርቡ ዘ ኒውዮርክ ታይምስ (the New York Times) ዘ ጋርዲያን (the Guardian) ኢንተር ናሽናል ክራይስስ ግሩፕ (International Crisis Group) እና ሌሎች በዓለም የታወቁ ተቋማት ያለፈውን አንድ ዓመት ቃኝተው እንደጠቆሙት፣ በሀገራችን ገና ያልተፈቱ ብዙ ችግሮች አሉ፤ ጠ/ሚ/ር ዐብይ አህመድ የጀመሩት ሰላማዊ የለውጥ ሂደት ብዙ መሰናክሎች ገጥመውታል።

በአሁኑ ወቅት፤ ጠ/ሚ/ሩ የሚመሩትን የለውጥ ሂደት ከመደገፍ ውጭ ሌላ አማራጭ የለንም። ፈተናዎች መኖራቸው እንዳለ ሆኖ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዙ ፈተናዎችን ያለፈ ስለሆነ፣ የአሁኑንም ፈተና ያልፈዋል የሚል እምነት አለኝ። ጠንካራና አንድነቷ የተከበረ ኢትዮጵያን ለመመስርት ይቻላል;፡ ጠ/ሚ/ር ዐብይ እንዳስቀመጡት፣ የእያንዳንዳችን ጥረት መሆን ያለበት፣ "የበለጸገች፤ የሰለጠነች፤ አንድነቷ የተጠበቀ፤ በዓለም ፊት በሞገስና በኩራት የምትቆም፤ ዲሞክራሲና ፍትህ የሰፈነባት፤ ዜጎቿ የትም ክልል በሰላምና በጤና የሚኖሩባትን ኢትዮጵያ መገንባት ነው (ለዲያስፖራው የተጻፈ ደብዳቤ፤ March 28, 2019)።

ይህን መርህ ስኬታማ ለማድረግ ግን፣ ቋንቋን ብቻ መስፈርት አድርገው የተዋቀሩት ክልሎች መፍረስ ይኖርባቸዋል። ለምሳሌ፣ የታወቀው የጥናትና የምርምር ተቋም የሆነው ኢንተርናሽናል ክራይስስ ግሩፕ (International Crisis Group, Report No. 269, February 21, 2019) ባቀረበው ዘገባና ምክር እንዲህ ብሏል፡-

"At the top of Prime Minister Abiy Ahmed's priority list must be the restoration of security through calming of ethnic tension and violence. To encourage a positive national tone, Abiy should develop a governance style that matches his inclusive rhetoric." Among other things, inclusion of stakeolders "can help dispel the impression shared by some that he is governing from a closed circle of co-ethnic and regional advisrors."

የጠ/ሚ/ር ዐቢይ አህመድ ቀዳሚ ትኩረት በብሄሮች መካከል ያለውን ውጥረትና ግጭት ማብረድ መሆን ይገባዋል። በዚህ ረገድ አሞች ሀገራዊ ድባብ ለመፍጠር፣ በሚናገሩትና በሚሰሩት መካከል ክፍተት እንዳይኖር፣ አስተዳደራቸው ሁሉን አቀፍ መሆኑን በግላጭ ማሳየት መቻል አለባቸው። ይህ መሆኑ፣ አንዳንዶች እንደሚያስቡት፣ የቅርብ አማካሪዎቻቸው ከአንድ ወንዝ የተቀዱ አለመሆናቸውን ማሳየት ይገባቸዋል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ በተለይ የዐማራውና የኦሮሞው ወጣት ትውልድ፣ በህወሓት አልሞ ተኳሾች የተጨፈጨፈው ህወሕትን በአዴፓም ሆነ በሌላ የብሄር አምባገነን ቡድን ለመተካት አይደለም። ስለዚህ፤ በኢንተርናሽናል ክራይሲስ ግሩፕ የቀረበውን ምክር እኔም እጋራለሁ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠ/ሚ/ር ዐብይን አልመረጣቸውም፤ የመረጣቸው ኢህአዴግ ነው፤ ኢህአዴግ የዘውግ ፓርቲዎች ስብስብ ነው፤ ይህ ፓርቲ አንቀጽ ሰላሳ ዘጠኝን አላነሳም፤ በዘውግ መደራጀትን አላነሳም። እንዲያውም፤ አዴፓና ህወሓት፣ ተመካክረውም ባይሆን፣ ለየብቻቸው ሆነው ባወጡት መግለጫ፣ "ዘውግ ተኮሩ ሕገ መንግሥትና ክልላዊው አወቃቀር ለድርድር አይቀርብም" የሚል አቋም ወስደዋል። ይህ ሁሉ የኢትዮጵያን ህዝብ በእጅጉ ያሳስበዋል፤ ውሎ አድሮ ምላሽ የሚሹ ጉዳዮች ናቸው። እስካሁን ያለው ዝምታ፣ ለጠ/ሚ/ሩ የእፎይታ ጊዜ ይገባቸዋል በሚል መንፈስ ነው። ይህ የእፎይታ ጊዜ፣ ከአሁን በኋላ ለረጅም ጊዜ ሊቀጥል አይችልም።



እኔ በግሌ፣ ጠ/ሚ/ሩ እነዚህ አሳሳቢ ጉዳዮች አያሳስቧቸውም የሚል እምነት የለኝም፤ ከሚናገሩት ጋር ይጋጫሉ። ፓርቲያቸው ምንም አለ ምንም፣ ጠ/ሚ/ሩ በግል ያላቸው አቋም ግልፅ አይደለም። ይህንን እውነታ ኢንተርናሽናል ክራይሲስ ግሩፕ ታዝቧል፡-

"Abiy has avoided taking a clear position on ethnic federalism. Though he rode a wave of regional and ethnic grievance to his current position, since assuming high office he has made frequent reference to Ethiopiawinet (ኢትዮጵያዊነት)-, a term invoking national unity rather than decentralization."

ዐብይ በብሄር ፌደራሊዝም ላይ ግልፅ የሆነ አቋም ከመውሰድ ተቆጥበዋል። ምንም እንኳን ወደ ስልጣን ያወጣቸው ከብሄር ጋር የተሳሰሩ ብሶቶች ቢሆኑም፣ ስልጣን ከያዙ ጊዜ አንስቶ ኢትዮጵያዊነት የሚለውን አጥብቀው ይናገራሉ፤ ይህ ደግሞ ብሄራዊ አንድነትን የሚያጎላ ነው።

ብሄር ተኮር ፌደራሊዝም የመለያያ ቀመር ነው። መለያያ ስለሆነ፣ በጥናትና በምርምር፤ በሕዝብ ውይይትና ድምጽ የሚወሰን ሌላ አማራጭ ያስፈልጋል። ሕገ መንግሥቱ መጽሃፍ ቅዱስ ወይንም ቁራን አይደለም። የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች አቋማቸውን መመራመር አለባቸው፤ ሀገር ልትጠፋ ትችላለች።

## በ March 14, 2019 እትሙ፣ ዘ ጋርዲያን

(the Guardian) በኢትዮጵያ ለውጥ ላይ ያጠላው ጥላ (Shadow Falls over Ethiopia's Reforms) በሚል እርእስት በጌድዮ ስለተከሰተው ብሄር ተኮር ግጭት፣ ረሃብ፤ በሽታ እንዲህ ሲል ጠቁሟል፡-

"Despite reports of lynchings, rapes and beheadings, the Ethiopian government is trying to force people displaced by conflict to return to their villages." ግድያ፣ አስገድዶ መድፈርና መቅላት (አንገት መቁረጥ) የመሳሰሉ

ነገሮች እንዳሉ እየተገለፀ ቢገኝም፣ የኢትዮጵያ መንግስት ተፈናቃዮች ወደ ቀየአቸው እንዲመለሱ ለማስገደድ እየሞከረ ነው።

የሰብአዊ እርዳታ ሰራተኞች እንደሚሉት፤ በእነዚህ ኢትዮጵያዊያን ላይ የደረሰው ሰው ሰራሽ ረሃብ፣ "ከቁጥጥር ውጭ የሆነ ሰብዓዊ ቀውስ" "full-blown humanitarian crisis" ደረጃ ላይ ደርሷል። "The dire situation facing millions of people forced from their homes by conflict, and the new regime's approach to their plight, has invited a more sceptical response from some observers." በግጭቶቹ ሳቢያ፣ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ሰዎች ከባድ ችግር ላይ የወደቁ ቢሆኑም፣ የመንግስት የተለሳሰለሰ ምላሽ ብዙ ታዛቢዎችን በእጅጉ አሳስቧል።

የዓለም መንግሥታት ጠ/ሚ/ር ዐብይ አህመድን ከፍ አድርገው ያመሰግኑትን ያህል፤ በእነዚህና በሌሎች ብዙ ኢትዮጵያዊያን ላይ በደረሰው መፈናቀልና ረሃብ ምክንያት፣ የአስተዳደር ችሎታቸውን መጠራጠር መጀመራቸው በዘገባው ላይ ተጠቁሟል። በእኔ እምነት ግን፤ እኒህ መሪ፣ የደለበውንና ስር የሰደደውን ብሄር ተኮር አገዛዝ ብቻቸውን ለመቅረፍ አይችሉም።

በሶስተኛ የምጠቅሰው ዘገባ፣ በታወቀው የዩጋንዳው ተወላጅና በኮሎምቢያ ዩኒቨርስቲ የሚያስተምረው ምሁር፣ ፕሮፌሰር ማህሙድ ማህዳኒ፣ በኒውዮርክ ታይምስ January 3, 2019 የኢትዮጵያ የብሄር ፌድራሊዝም ችግር (The Trouble With Ethiopia's Ethnic Federalism) በሚል አርእስት የጻፈውን ሃተታ ጭማቂ ነው።

"The 1994 Constitution, introduced by Prime Minister Meles Zenawi and the Ethiopian People's Revolutionary Democratic Front governing coalition, recast the country from a centrally unified republic to a federation of nine regional ethnic states and two federally administered city-states. It bases key rights — to land, government jobs, representation in local and federal bodies — not on Ethiopian citizenship but on being considered ethnically indigenous in constituent ethnic states. "

በመለስ ዜናዊ የሚመራው ኢህአዴግ፣ በ1987 ባወጣው ህገ መንግስት፣ ኢትዮጵያን ከተማከለ ሪፖብሊክነት ወደ ዘጠኝ የብሄር ክልሎችና ሁለት የከተማ አስተዳድሮች ፌደሬሽን ወስዷታል። በዚህ ህገ መንግስት፣ የህዝቡን መብት (የመሬት ባለቤትነት፣ የመመረጥ መብት፣ የመንግስት ቅጥር መሆን፣ ወዘተ) ከኢትዮጵያዊ ዜግነት ይልቅ በብሄር ማንነት ላይ የሚመነጭ አድርጓታል።

መለስ ዜናዊና አጋሮቻቸው የግጭትን፣ የንትርክና የመበታተን በር ከፍተው አልፈዋል። ለአሁኑና ለተከታታይ ትውልዶች ያላለፈው አደገኛ "ጥሪት፣" ጠባብ ብሄርተኝነት፣ ጽንፈኛነት፣ ጠብ ጫሪነት፣ ጥላቻ፣ ስጋትና ፍርሃት ናቸው፤ ይህ መቀየር አለበት።

የችግሩ እምብርት ይኼው ነው፤ ለውጥ አስፈላጊ ነው። ፕሮፌሴር ማህዳኔ ችግሩን ሲያብራራ እንዲህ ይላል፡-

"The reforms by the country's new prime minister are clashing with its flawed Constitution and could push the country toward an interethnic conflict.....As in the Soviet Union, every piece of land in Ethiopia was inscribed as the ethnic homeland of a particular group, constitutionally dividing the population into a permanent majority alongside permanent minorities with little stake in the system. Mr. Zenawi and his party had both Sovietized and Africanized Ethiopia."

የጠ/ሚ/ሩ ለውጥ ከተበላሹ ህገ መንግስት ጋር እየተጣረዘ ሀገሪቷን ወደ ብሄር ግጭት ሊከታት ይችላል። ልክ እንደ ሶቭየት ህብረት፣ ክልሎች ለየብሄሮቹ ተሸንሽነው ስለተሰጡ፣ በውስጣቸው ያሉት የሌላ ብሄረሰብ አባላት መብት ከይስሙላ ያለፈ አይደለም የሚል ስሜት ፈጥሯል። መለስ ዜናዊ ኢትዮጵያን በአንድ ቅፅበት ሶቭየታዊና አፍሪካዊ ገፅታ አላብሰዋታል።

ባለፉት ሃያ ስምንት ዓመታት በተደጋጋሚ በሚታይ፤ በሚዳሰስ፤ በሚለካና በሚዘገንን ደረጃ፣ ይህ ብሄር ተኮር ፌደራሊዝም ኢትዮጵያን ሊያፈርሳት እንደሚችል ታይቷል። ይሄው ተመራማሪና ምሁር እንዲህ ይላል፡-

ወደ 20 ዞሯል



ክንፉ አሰፋ
የኢትዮፎረም ድረ-ገጽ አዘጋጅና ሶፍትዌር ኢንጂነር
አምስተርዳም፣ ኔዘርላንድስ

# የታከለ ኡማ “ተራ አክቲቪስቶች” ወግ

## እንዴት ታወዳድሩኛላችሁ?

“ውስጥን ሳይሆን፣ ይልቁንም ሌሎችን ብቻ ከመመልከት.... ናፖሊዮን በቄሳር ይቀና ነበር፣ ቄሳር ደግሞ በአሌክሳንድር ይቀና ነበር፣ አሌክሳንድርም ቢሆን፣ በህይወት ኖሮ በማያውቀው የልብ ወለዱ ገፀ ባህሪ ሄርኩለስ ይቀና ነበር....” ይላሉ እንግሊዛዊው ፈላስፋና የታሪክ ተመራማሪ በርትራንድ ዊልየም ሩስል።

ራስን ከሌሎች ጋር የማነጻጸር አባዜ ሌሎችን በልጦ ለመገኘት ከማሰብ ከሚመጣ የስሜት ርሃብ መሆኑን የስነ ልቦና ጠበብት ሁሉ ይስማሙበታል። ኢንጅነር ታከለ ኡማ ብሄራዊ ቴሌቭዥን ላይ ተከስተው፤ “... እንዴት እኔ ታከለ ኡማን ከተራ አክቲቪስት ጋር ታወዳድራላችሁ?” ብለው የመናገራቸው አባዜ ከዚህ መስመር የወጣ አልመሰለኝም። እኚህ ሰው ከሌሎች በልጠው ስለመገኘታቸው ያቀረቡት ውሃ የማይቋጥር ምክንያት፤ ጉዳዩን በስነ-ልቦና መነጽር እንድንመለከተው ያደርገናል።

“ሰዎች መናገር በማይችሉበት ዘመን ኢህአዴግን የተናገርኩ ማንንም የማልፈራ ሰው ነኝ” ብለዋል ታከለ።

ታከለ ኡማ ይህንን ጉዳይ ከምን አንፃር ተናገሩት? ምንስ ለማለት ፈለገው ነው?... ወዘተ የሚሉ ይሁንታዎችን እያነሳሁ መላ ምቶች ውስጥ መግባት አልፈልግም። “ተራ” የሚለውን ጥሬ ቃል ብቻ ይዘን፤ ቃሉን ምንም ቀለም ሳንቀባ እና ሳንሰነጣጠቅ የመልዕክቱን አንደምታ ብቻ እንይ።

አንድ ነገር ግልጽ ነው። ማንም ይሁን ማንም፣ ሰዉን “ተራ” በሚል ዘለፋ የሚገለፅ፤ ከንቲባ ወንበር ላይ መቀመጥ አይገባውም - ንግግሩ ከሞራል ዝቅጠት በታች ነው:: ፈሪሃ እግዚአብሄር ያለውን ህዝብ ለመምራት፣ ትልቁ ግብዓት ሊሆን የሚችለው የሞራል እሴት ነው። “ተራ” የሚለው ዘለፋ የሞራል እሴትን አያመላክትም::

ራስን ከሌላ ለማነጻጸር መሞከሩ ችግር ላይኖርበት ይችላል። ከመጠን ያለፈ ራስን መውደድና ለራስ ዋጋ መስጠትን ግን፣ ጤናማ ከሆነ አስተሳሰብ የሚጠበቅ አይደለም። የአዲስ አበባን ከስድስት ሚልየን የማይተናነስ ሕዝብ ከሚመራ ሰው ይህንን ስናደምጠው፤ የችግሩን መንስኤ መፈተሽ ግድ ይለናል። እኚህ ሰው ይህንን ሕዝብ የመምራት ሞራሉ እንኳ ቢኖራቸው፤ ራስን አግዝፎ ሌላውን በንቀት የመመልከት እሳቤያቸው በብቃታቸው ላይ የጥያቄ ምልክት እንድናነሳ ያስገድደናል። በዚህ የልቀት እና የእውቀት ዘመን፤ ፊደል ያልቆጠረ አርሶ አደር እንኳ መገናኛ ብዙሃን ላይ ወጥቶ እንዲህ ከወረደ ሃሳብ ከመናገር ይቆጠባል።

ድህነታችን የቁስ እንጂ የሥነ ምግባር እንዳልሆነ ለሳቸውም የሚጠፉቸው አይመስለኝም። ስነ-ልቦና ውቅራችን የተገነባበት መከባበር እና “በሰላም አብሮ መኖር” የምንለው ትልቅ እሴት አለን። ይህንን ትልቅ እሴት ማጣጣል መሞከር፣ በራሱ የራስ ደካማነትን እና ያለማስተዋልን እንደመስታወት ያሳየናል።

ኢንጂነር ታከለ ኡማ “ተራ” ያሉት አክቲቪስት ማንም ይሁን ማን፤ ንግግራቸው ጤነኛ አስተሳሰብ እና በጎ አመለካከት ካለው ዜጋ የሚጠበቅ አይደለም። እሳቸውን ከሌላ ጋር የማወዳደር ስሌት ውስጥ እንግባ ካልን ደግሞ፣ ዝቀን የማንጨርሰው ጉድፍ ማውጣት እንችላለን። “አክቲቪስት” ያሉትን በጥቁር እና ነጭ ባያስቀምጡትም፣ ጣታቸው ማን ላይ እያነጠጠረ መሆኑን መገመት ግን አይከብድም። ንግግራቸውን እያደመጠ ያለው ሕዝብ ስንዴን ከእንክርዳድ የማይለይ፤ ትላንት የተወለደ ህጻን አለመሆኑን መዘንጋት አልነበረባቸውም።



ንግግሩ አንድን አካል ኢላማ ለማድረግ ሂሳብ ተሰርቶበት የተደረገ ጉንተላ እንጂ፣ የአፍ ወለምታ አይደለም። ጉንተላ ግን በመሪዎች አያምርም። ትንኮሳም ለሀገር አይጠቅምም። አፍላ ጉልበት እና ወኔያቸውን አክቲቪስቶችን ለመተቸት ከሚያውሉት፤ ከእነሱ ጋር ተነጋግሮ መፍትሄ ማምጣቱ ላይ አብዝተው ቢሰሩ መልካም ነበር።

የሃሳብ ገበያው በደራበት በዚህ የማህበራዊ ትስስር ዘመን፣ በሃሳብ ልቆ፤ የሌላውን ሃሳብ ማሸነፍ መጣር አንድ ነገር ነው። እጅግ በተጋነነ መልኩ የሌለ ማንነትን መፍጠር መሞከር ደግሞ አደጋ ነው። ኢንጅነሩ አንዱን ዝቅ አድርገው ራሳቸውን ከፍ ለማድገር የሄዱበት መንገድ፣ ከሽንፈት ስነ ልቦናዊ የመነጨ ስለመሆኑ አንድ ሺህ ምክንያቶችን መደርደር አያሻንም።

“ክላሲካል አድለሪያን ሳይኮሎጂ” ን ለሳይንሱ አለም ያበረከተው ኦስትሪያዊው የሥነ ልቦና ሀኪም፤ አልፍሬድ አድለር፤ በሥነ ልቦና አስተምሮት ራስን ከሌላ ማነጻጸርን በሁለት ዓይነት የበታችነት ስሜት ይከፍለዋል።

### የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ደረጃ የበታችነት ስሜት

የመጀመርያው የበታችነት ስሜት ስሜት በተለይ በህጻናት ላይ የሚከሰት ጤናማ የሆነ ንፅፅር ነው። ይህ ስሜት አቅመ-ቢስ ከመሆን በሚመነጭ የጥገኝነት ስሜት ሳብያ ይከሰታል። ነብስ ያወቀ አንድ ሰው፣ በራሱ ማድረግ የፈለገውን ለመከወን በቂ ሳይሆን በመቅረቱ የሚፈጠረው የበታችነት ስሜት ደግሞ፣ ሁለተኛው ዓይነት ነው።

በቀላል አማርኛ፣ ሰውየው ችግርን ማሸነፍ ዳገት ሲሆንበት፣ በራስ ያለመተማመን ስሜት ይጠቃል። በእውቀትም ሆነ በብቃትም የማይመጥን ሰው ጋር ራስን ማነጻጸር፣ በራሱ ህመም እንደሆነ ነው አልፍሬድ የሚነግረን።

“እኔ እኮ ማንንም የማልፈራ ሰው ነኝ” የሚል ዲስኩር ከአንድ የሕዝብ መሪ አፍ ውስጥ ሲሰማ፣ ጆሯችንን ልንጠራጠር እንችል ይሆናል፤ ዓይናችንን ያለማመን ግን አንችልም። “ማንንም የማይፈሩ ከሆነ፣ በግርግሩ ግዜ ወደ አሜሪካ ለምን ሸሹ?” ብሎ የሚጠይቅ ቢኖር ምላሹ ምን ይሆን?

## ሌሎቹ በአስር ዓመታት ውስጥ ከሰሩት

ምክትል ከንቲባው ትንፋሽ እንዳጠራቸው የሚያመላክተውን ንግግራቸው በዚህ አላበቁም። “ሌሎቹ በአስር ዓመታት ውስጥ ከሰሩት ስራዎች ይልቅ፣ እኔ በሰባት ወር የሰራሁት ይበልጣል” ብለውናል። ይህ ደግሞ የአዲስ አበባ የቀድሞዎቹ ከንቲባዎች፣ የኩማ ደመቅሳ እና የድሪባ ኩማን ተግባራት በዜሮ የሚያባዛ ንግግር ነው።

የፖለቲካውን ወደ ጎን ትተን፣ የኢኮኖሚውን ሂሳብ ስናወራርድ የሚያሳየን ስዕል ከገለጻው ጋር ባይሄድም፣ ይህንንም ያሉበት ምክንያት ራስን ለመከላከል ይመስላል። መረጃ ይዘን ለመሞገት ብንነስዳ፤ ታከለ አኡማ ቢሮውን በተቆጣጠሩ የ6 ወራት ጊዜ ውስጥ ለልማት ሳይሆን ለመስተንግዶ ብቻ 12 ሚሊየን ብር ወጪ አድርገዋል። በሳቸው የስራ ዘመን በከተማዋ ውስጥ ስንት ህገ ወጥ መታወቅያ እንደታደለ ልቦናቸው ያውቀዋል።

ምክትል ከንቲባነት ሲሾሙ ህዝብ እንዲያስተዳድሩ እንጂ፣ ከሌሎች ጋር እራሳቸውን እንዲያወዳድሩ አልነበረም። አንድ ግዜ የቱርክ፤ ሌላ ግዜ ደግሞ የህንድ አክተር እየመሰሉ አደባባይ ከመውጣት ባሻገር፣ ዐይን ውስጥ የገባ መዋቅራዊ ለውጥ አድርገው ከሆነ፣ እስኪ ይህንን ይንገሩን:: ህዝብን መምራት ከአደባባይ ላይ ትርኢት ከፍ ይላል፤ ሰከን ማለትን ይጠይቃል።

“የማይሳሳት የማይሰራ ብቻ ነው” የሚለውን እንመን። ስህተት ተፈጥሯዊ ነው ክስተት መሆኑንም በግርድፉ እንቀበል። ችግሩ ያለው፣ የራስ ስብዕናን ከፍ ለማድረግ ብቻ ሲባል፣ ሆን ተብሎ የሚሰራ ጥፋት ላይ ነው። “ሰው ምንድን ነው?” ሲል ይጠይቃል አሜሪካዊ ፀሃፊ ማርክ ትዌይን። "የሰው ልጅ ክፉና ደግን መለየት መቻሉ ከሌሎቹ ፍጥረታት የላቀ ያደርገዋ፤ የሰው ልጅ የሞራል ልዕልናውን የሚያጣው እያወቀ በሚሰራው ጥፋት ነው።”

ሕዝብን ማስተዳደር ራሱን የቻለ ሳይንስ ነው። ችግርን መፍታት ደግሞ ጥበብን ይጠይቃል። የፖለቲካው ቴርሞሜትር የሚለካው ሕዝብ መሆኑን መረዳት ራሱ መሪውን የሚፈትን ተግባር ነው። የስኬት መለኪያ የሚሆነው የመሪው ቁርጠኝነት በተግባር ሲፈተን እንጂ፣ የህዝብን ልቀት ዝቅ ከሚያደርግ መግለጫ አይደለም። ጋዜጠኛም ሆነ አክቲቪስት፣ ሁሉም ህዝብ መሆናቸውን ለአፍታ ዘንግተውት ካልሆነ በቀር፣ የራስን ጥንካሬ መለፈፍ እና ገጽታን መገንባት የሌላውን ድክመት አያመላክትም።

## ስለ ድል አጥቢያ ከተነሳ አይቀር

ስለ ድል አጥቢያ አርበኞች ነግረውናል። በፐ/ር መረራ ጉዲና ፓርቲ ውስጥ እያሉ ድርጅቱን ለማን አሳልፈው እንደሰጡ እያወቅን፣ እሳቸው ስለ ድል አጥብያ ባይነግሩን መልካም ነበር። ይህንን ቃል በመናገር ድክመትን ለመሸፈን የሚሄዱበት መንገድ እና የተጓዙት ርቀት ይለያይ እንጂ፣ ድርጊቱ አሁንም አጉልቶ የሚያሳየን፣ በሌላ የመበለጥ ስሜትን ነው። ዓላማው የጋለውን የሕዝብ ስሜት ለማብረድ ከሆነ፣ ነገሩን በዚህ መልኩ ማስኬዱ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ያመዝናል።

የፖለቲካቸውን የነርቭ ማእከል ነክቶ ድንጋዩን ያስነቀላቸው የባልዳራስ ጥያቄ ከሆነ፤ ለምላሹ እዚያ ድረስ ርቆ መሄዱ አስፈላጊ አልነበረም፤ ጥያቄው ከድንጋይ የከበደ አልነበረም። “ማንም ይቀመጥ ማን፣ ከተማዋ በህጉ አግባብ ትመራ” ነበር ጥያቄው። በጎ ምላሽ የሚሻ ግልጽ ጥያቄ። እንደ ሀገር እና እንደ ህዝብ ልዩነታችንን አቻችለን ወደ ፊት እንራመድ፤ ወንዙንም እንሻገር ካልን፣ አቋራጭ መንገድ ከፍቶ ትርፍ ማውራቱ ምንም አይፈይድም። መፍትሄው የነቆራውን ገበያ ዘግቶ የሃሳብ ገበያውን ክፍት ማድረግ ብቻ ነው።

# ለስኳር ኮርፖሬሽን ዋና ሥራ አስፈጻሚ ተሾመ



አቶ ወዮ ሮባ አካኮ የስኳር ኮርፖሬሽን ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሆነው ተሾሙ። ላለፉት ሦስት ወራት በተጠባባቂ ዋና ሥራ አስፈጻሚነት የመሩት አቶ ወዮ ሮባ፣ ከመጋቢት 27 ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ የተቋሙ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሆነው ተሹመዋል። አቶ ወዮ ከ2004 ዓ.ም አንስቶ ለሰባት ዓመታት የኮፖሬሽኑ ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሆነው ሠርተዋል። ወደ ኮርፖሬሽኑ ከመምጣታቸው አስቀድሞም በኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት በተለያዩ የኃላፊነት ቦታዎች አገልግለዋል።

በተያያዘ ዜና፣የኦሮሚያ ኢንተርናሽናል ባንክን በዳይሬክተርነት ሲመሩ የቆዩት አቶ ኑሪ ሁሴን፣ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ምክትል ፕሬዚዳንት ሆነው መሾማቸው ታውቋል። የንግድ ባንክ ፕሬዚደንት አቶ ባጫ ጊኒ፣ የኦሮሚያ ህብረት ሥራ ባንክ ፕሬዚደንት ነበሩ።

# የዓለም የጤና ድርጅት የጌዲዖ ተፈናቃዮች አየ ያዝ እንዲሻሻል ጠየቀ

የዓለም የጤና ድርጅት በጌዲዖ የሚገኙ ተፈናቃዮች አያያዝ፣ የንጹህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት፣ ንፅህናና የከትባት አሰጣጥ መሻሻል ይገባዋል አለ። ድርጅቱ ተፈናቃዮቹን ለማገዝ የሕክምና ባለሙያዎች ፣ መድሃኒቶች እና የሕክምና ግብዓቶችን ልኳል። ከእነዚህ መካከል ለሶስት ወራት አስቸኳይ የጤና እገዛ መስጠት የሚያስችሉ ቁሳቁሶች፣ ጓንቶች፣ መርፌዎች እና ሲሪንጆች ይገኙበታል።

ድርጅቱ ባወጣው መግለጫ እንዳለው ከሆነ፣ 250 የከፋ የምግብ እጥረት ያለባቸው ሕፃናት የሚገጥሟቸውን ውስብስብ የጤና ችግሮች ለሶስት ወራት ማገዝ የሚችሉ ግብዓቶችን አሰራጭቷል። ድርጅቱ ወደተፈናቃዮቹ ባለሙያዎችን የላከ ሲሆን፣ በገደብ ወረዳ የሚገኙ ሁለት መጠለያዎች እና የከፋ የተመጣጠነ የምግብ እጥረት ለገጠማቸው ሕጻናት ሕክምና የሚሰጥበትን የገደብ ሆስፒታል ጎብኝተዋል።

የዓለም የጤና ድርጅት ከኢትዮጵያ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅቶች፣ ዓለም አቀፍ ተቋማት እና የግብረ ሰናይ ድርጅቶች ጋር በመተባበር የውሃ አቅርቦት፣ የንጽሕና አገልግሎት እና የከትባት ዘመቻዎችን ለማጠናከር እንደሚፈልግ ገልጿል።

የኢትዮጵያ መንግሥት በተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ ተፈናቃዮችን ወደ መኖሪያ ቀያቸው ለመመለስ ከ650 እስከ 700 ሚሊዮን ዶላር እንደሚያስፈልግ አስታውቋል፤ ሆኖም ለዚህ ሥራ እስከአሁን የመደበው 800 ሚሊዮን ብር ብቻ ነው።

# በቶጎ ጫሌ 20 ሺህ ዶላር የሚገመቱ የወጭ ገንዘቦች በጫማ ውስጥ ተያዙ

20 ሺህ ዶላር ገደማ የሚገመቱ የተለያዩ የውጭ ገንዘቦችን ጫማው ውስጥ ደብቆ ከሀገር ለማስወጣት የሞከረ ግለሰብ በቁጥጥር ስር መዋሉ ተገለፀ።ተጠርጣሪው በቁጥጥር ስር የዋለው በቶጎ ጫሌ ኬላ በተደረገ ፍተሻ ነው ተብሏል። ገንዘቦቹም፣ 18 ሺህ 838 የአሜሪካ ዶላር፣ 270 ፓውንድ ፣2 ሺህ ዩሮ፣ 1 ሺህ 600 የሳዑዲ ሪያል እና 25 ሺህ 550 የዩናይትድ አረብ ኤሚሬቶች ድርሃም ናቸው።

በተያያዘ ዜና፣ 1 ነጥብ 5 ሚሊየን ብር ግምት ያለው የኮንትሮባድ እቃ ጭኖ ከቶጎ ጫሌ ወደ ሀረር ሲጓዝ የነበረ ደረቅ የጭነት ማመላለሻ አይሱዙ ተሽከርካሪ ባሳለፍነው ቅዳሜ ተይዟል። ተሽከርካሪው ጭናቅሰን ከተማ ሲደርስ፣ ከህዝብ በተሰጠ ጥቆማ ከሌሊት 8 ሰዓት አካባቢ መያዙ ነው የተገለፀው።የበ

በቁጥጥር ስር የዋሉት የኮንትሮባምድ ዕቃዎችም የሰልክ ባትሪዎች፣ ቬንትሌተር፣ ፍሪጅ እና ሌሎች የኤሌክትሮኒክስ እቃዎችና መሰል ይዘት ያላቸው ቁሶች ናቸው። ጃርሶ፣ ኮምቦልቻና ባቢሌ ወረዳዎች የኮንትሮባንድ ማለፊያ ቀጠናዎች ሲሆኑ፣ በአካባቢው ቄሮ ነ ን የሚሉ ወጣቶች በስፋት ይንቀሳቀሳሉ።

# የኢትዮ ጅቡቲ ባቡር አደጋ ሦስት ፉርጎዎች ከጥቅም ውጭ አደረገ



ከአዲስ አበባ ወደ ጅቡቲ በመጓዝ ላይ የነበረ 17 ፉርጎ የሚጎትት የዕቃ መጫኛ ባቡር አደጋ ደረሰበት። አዲስ አበባ 129 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በደረሰዉ በዚሁ አደጋ፣ የአዲስ አበባ ጅቡቲ የባቡር እንቅስቃሴ በጊዜያዊነት ለመቋረጥ ተገዷል። በአደጋዉ የባቡሩ ሦስት ፉርጎ ሙሉ በሙሉ የተጎዳ ሲሆን፣ ፉርጎዉን ይጎትት የነበረዉ ዋናዉ የሞተር ፉርጎም የደረሰበት ጉዳት ከፍተኛ መሆኑ፣ በተጨማሪም፣ ሰባት ፉርጎዎች ተጣመው ከባድ ጥገና እንደሚያስፈልጋቸው ታውቋል። ፉርጎዎቹ ወደ ቻይና ተጭነዉ ካልሄዱ በስተቀር ኢትዮጵያ ለመጠገን አቅሙ የላትም እየተባለ ነው።

ባቡሩን የሚያሽከረክሩትም ሆነ የሚጠግኑት ቻይናዉያን ብቻ ሲሆኑ፣ በዘርፉ የሰለጠኑ ኢትዮጵያዊያን ችላ ተብለው ይገኛሉ የሚል ቅሬታም እየተሰማ ነው። በሚቀጥለዉ ዓመት ይጠናቀቃል ተብሎ በሚጠበቀውና እስከ መቀሌ የሚዘልቀዉ የአዋሽ ወልድያ የባቡር መስመር ግንባታ ከተመረቀ በኋላ፣ ለሚቀጥሉት አምስት ዓመታት የባቡር ሃዲድ ግንባታ እንደማይደረግ እየተነገረም ይገኛል።

# "ቱርክ፣ ሱዳንና ቀጠርን የጥፋት መልዕክተኞች ናቸው" የኤርትራ ማስታወቂያ ሚኒስተር

ኤርትራ፤ «የጥፋት መልዕክተኞች» ያለቻቸዉን ቱርክን፣ ቀጠርንና ሱዳንን አወገዘች። የኤርትራ ማስታወቂያ ሚኒስቴር በድረ-ገፁ ባሠራጨዉ መግለጫ፤ ሶስቱ መንግሥታት በኤርትራና በኢትዮጵያ መካከል የተጀመረዉን የሠላም ሂደት ለማደናቀፍ እያሴሩ ነዉ ብሏል። መግለጫዉ፤ «አርባና ቢስ» ያላቸዉን እርምጃዎች ቀጠር በመደበኛዉ ገንዘብ የሚቀነባበሩ ናቸዉ ሲል ገልፆል። ቀጠር የኤርትራ የቅርብ ወዳጅ፣ የኤርትራና የጅቡቲ ሸምጋይም ነበረች። በሳዑዲ አረቢያ የሚመሩት የዓረብ መንግሥታት ከቀጠር ጋር ዉዝግብ ከገጠሙ ወዲህ ግን፣ ኤርትራ ከሳዑዲ አረቢያ ጎን ቆማለች፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ፣ የኤርትራ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ኦስማን ሳሌሕ እና የ ኢሳያስ አፈወርቂ አማካሪ አቶ የማነ ገብረአብ ሶማሊያን ገበኙ። ሁለቱ ባለሥልጣናት በኢትዮጵያ አየር መንገድ ተጉዘው ሞቃዲሾ ሲደርሱ፣ የሶማሊያ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አሕመድ ኢሴ አዋድ ተቀብለዋቸዋል። በቀጣይነትም፣ ከሶማሊያው ፕሬዝዳንት መሐመድ ፎርማጆ ጋር ተገናኝተው ሰለ ሁለትዮሽ ግንኙነታቸውና የቀጣናውን ምጣኔ ሃብታዊ ውኅደት ስለማጠናከር መወያየታቸው ተገልጿል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ እና ፕሬዝዳንት ኢሳያስ አፈወርቂ ዕርቅ ካወረዱ በኋላ፣ ኤርትራ በቀጠናው ያላትን ትስስር የማጠናከርና ሻክሮ የቆየ ግንኙነቷን የማደስ እንቅስቃሴ ላይ ትገኛለች። ውጭ ጉዳይ ምኒስትር ኦስማን ሳሌሕ እና አቶ የማነ ገብረአብ ባለፈው ሳምንት ወደ ካይሮ አቅንተው ከግብጽ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ጋር ተገናኝተዋል። ኤርትራ ከጅቡቲና ከሱዳን ጋር ያላትን ግንኙነት ለማሻሻል እየሞከረች ቢሆንም፣ እስካሁን አመርቂ ውጤት ማስገኘት አልቻለችም፡፡

# በቤንሻንጉል በኦሮምኛ ማስተማር ተጀመረ

በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል በአማርኛና በበርትኛ ሲያስተምሩ የነበሩ ትምህርት ቤቶች ዘንድሮ በኦሮምኛ ማስተማር መጀመራቸው ተነገረ፡፡ በክልሉ ትምህርት በተጀመረባቸው አምስት አካባቢዎች በሚገኙ ሀያ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በኦሮምኛ ቋንቋ ትምህርት እየተሰጠ ይገኛል፡፡ የኦሮሚያና የቤኒሻንጉል ህዝቦችን ያስተሳስራል የተባለው ይህ ለውጥ የተካሄደው፣ በመተከል ዞን በከማሺ፣ በማኦ፣ ኮሞና፣ በአሶሳ በሚገኙ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ነው፡፡

የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ አሻድሊ ሐሰን እንደገለፁት፣ በክልሉ የሚኖሩ የኦሮሞ ተወላጆች ልጆቻቸው በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው እንዲማሩ ባቀረቡት ጥያቄ መሰረት ትምህርቱ በኦሮምኛ እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡ ይህን የተናገሩት ዘንድሮ ለውጡን ተግባራዊ ካደረጉት ትምህርት ቤቶች መካከል የባምባሲ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤትን ከኦሮምያ ክልል ከመጡ ከፍተኛ ባለስልጣናት ጋር በጎበኙበት ወቅት ነው፡፡

እንደገለፃቸው ከሆነ፣ አሁን የፀጥታ ችግር በሌለባቸው አካባቢዎች የሚሰጠው ይህ ትምህርት፣ የፀጥታ ችግራቸው እየረገበ ሲመጣ በሌሎች አካባቢዎችም ተጠናክሮ ይቀጥላል፡፡ ለጊዜው በአንደኛ ክፍል ለሚማሩት ተማሪዎች የተጀመረ ቢሆንም፣ ቀስ በቀስ ዝግጅቱን ለሌሎች ክፍሎች ከፍ የማድረግ ስራ ይሰራል ብለዋል፡፡

የኦሮምያ ክልል የግብርናና ገጠር ልማት ዘርፍ አስተባባሪ የሆኑት ዶ/ር ግርማ አመንቴ በበኩላቸው፣ ክልሉ የተለያዩ ምክንያቶች ሳያቀርብ ለጥያቄው ምላሽ መስጠቱ ያስመሰግነዋል ብለዋል፡፡ በክልሉ ብዙ የኦሮምኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች አሉ የተባለ ሲሆን፣ በመምህራን በኩል ችግር አላጋጠመም ተብሏል፡፡ ከቤኒሻንጉል ክልል በተጨማሪም በሀረሪ፣ በሶማሌና በአዲስ አበባ በኦሮምኛ ትምህርት እየተሰጠ መሆኑ ተመልክቷል፡፡

# ታከለ ኡማ ከአዲስ አበባ ሶማሌ ተወላጆች ጋር ተወያዩ



ታከለ ኡማ የአዲስ አበባ ነዋሪ ከሆኑ የሶማሌ ተወላጆች ጋር አወያዩ። በውይይቱ የከተማ አስተዳደሩ ቀዳሚ ኃላፊነት የከተማውን ነዋሪ ህይወት መቀየር መሆኑን፣ በዚህም ሂደት የሶማሌ ተወላጆች ተጠቃሚ ይሆናሉ ብለዋል።

በአዲስ አበባ ውስጥ የሚኖሩ ከ30 ሺህ በላይ የሶማሌ ተወላጆች፣ እንደ ከተማዋ ነዋሪነታቸው የስራ ዕድል ተጠቃሚ ፣ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ዕድልና የመንግስት አገልግሎቶች ተጠቃሚ ይሆናሉ ብለዋል።

# የሰሜን ተራሮች እሳት ወደ ገደላማ ቦታዎች ተዛመተ

በሰሜን ተራሮች ብሄራዊ ፓርክ ላይ የተነሳውን እሳት ለማጥፋት ይረዳ ዘንድ ከኬኒያ ሄሊኮፕተር ለማስመጣት መንግስት ጥረት እየተደረገ መሆኑ ተገለፀ፡፡ እሳቱ በአሁኑ ሰዓት ከፍተኛ ጉዳት እያደረሰ ሲሆን፣ ሰው ሊደርስባቸው ወደማይችሉ ገደላማ ቦታዎች በፍጥነት እየወረደ ይገኛል፡፡ ሄሊኮፕተሮቹ ያስፈለጉት ወደእነዚህ ገደላማ አካባቢዎች ለመድረስ መሆኑ ተገልጿል፡፡ እሳቱን ለማጥፋት ከፍተኛ እርብርብ እየተደረገ ሲሆን፣ ዘመቻውን ለመቀላቀል ከአዲስ አበባ ወደአካባቢው መሄድ ለሚፈልጉ ምዝገባ እየተደረገ ይገኛል፡፡ ጎንደር የሚገኙት የፋሲል እግር ኳስ ቡድን በርካታ ወጣቶች ወደ አካባቢው በመላክ፣ የእሳት ማጥፋቱን እንቅስቃሴ እንዲቀላቀሉ አድርጓል፡፡

የእሳት አደጋው የደረሰው ግጭ ከሚባለውና ድሮ መንደር የነበረበት አካባቢ መሆኑ ታውቋል፡፡ አደጋው በድጋሚ የተከሰተው ማክሰኞ 9 ሰዓት አካባቢ ጀምሮ ነበር፡፡ እሳቱ እንደተነሳ የአካባቢው አርሶ አደሮች ሄደው አጥፍተውት የነበረ ቢሆንም፣ መልሶ አገርሽቷል።

እስከ ማክሰኞ እረፋዱ ድረስ፣ እሳቱን ለመቆጣጠር የአካባቢው አርሶ አደሮች፣ የፀጥታ ኃይሎች፣ ስካውቶችና ሚሊሻዎች ወደ አካባቢው ተሠማርተዋል ተረባርበዋል። ይሁን እንጂ፣ ቃጠሎው በነፋስ እየታገዘ በመስፋፋቱ በቀላሉ በቁጥጥር ስር ሊውል አልቻለም፡፡

የሰሜን ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ ከመጋቢት 19 ቀን 2011ዓ.ም ምሽት ጀምሮ ባጋጠመው የእሳት አደጋ በሳንቃ በር እና እሜት ጎጎ አካባቢ 342 ሄክታር ደን ወድሟል፡፡ እሳቱ መጋቢት 26 ቀን 2011 ዓ.ም ሙሉ በሙሉ ጠፍቶም ነበር፡፡ ብሄራዊ ፓርኩ በቱሪስቶች ዘንድ ከፍተኛ ተወዳጅነት ያለው ሲሆን፣ ቱሪስቶቹን ወደ ሀገሪቷ በመሳቡ ረገድ ቀዳሚ ቦታ ይዞ ይገኛል፡፡

# አምባሳደር ፍፁም አረጋ ከዶናልድ ትራምፕ ጋር ተገናኙ

በአሜሪካ የኢትዮጵያ ባለሙሉ ስልጣን አምባሳደር ሆነው የተሾሙት ፍፁም አረጋ የሹመት ደብዳቤያቸውን ለዶናልድ ትራምፕ አቀረቡ። አምባሳደር ፍፁም አረጋ የሹመት ደብዳቤያቸውን ያቀረቡት በኋይት ሀውስ በተዘጋጀ ስነ ስርዓት ነበር፡፡

ከአምባሳደሩ ጋር የተዋወቁት ዶናልድ ትራምፕ በሰጡት አስተያየት፣ በጠቅላይ ሚኒስትር ዐብይ አህመድ የሚመራው የለውጥ እንቅስቃሴ፣ ኢትዮጵያ በአፍሪካ የምትጫወተውን የመሪነት ሚና በአግባቡ እየተወጣች መሆኑን የሚያጠናክር ነው ብለዋል። እንዲሁም፣ በሁለቱ ሀገራት መካከል ያለውን የጠበቀ ግንኙነት ለማሻሻል እንደሚሰሩ ተናግረዋል፡፡

አምባሳደር ፍፁም አረጋ በበኩላቸው፥ በሁለቱ ሀገራት መካከል ያለውን ወዳጅነት ለማስቀጠል እንደሚሰሩ፣ በተለይም በኢኮኖሚ እና በቀጠናዊ ሰላም ዙሪያ በማተኮር ትስስሩ የበለጠ እንዲዳብር እንደሚሰሩ ገልፀዋል።

# ቦይንግ 737 ማክስ 8 በቅርቡ ወደ ሥራ እንዲመለስ ሊፈቀድለት ይችላል ተባለ




የኢትዮጵያ ትራንስፖርት ሚንስቴር የመጀመሪያ ደረጃ የምርመራ ውጤት ይፋ ካደረገ በኋላ፣ የቦይንግ ኩባንያ ዋና ሥራ አስኪያጅ ዴኒስ ሙሊንበርግ በሰጡት መግለጫ፣ በቦይንግ 737 ማክስ 8 ላይ በደረሰው አደጋ ለሞቱ ሰዎች እና ቤተሰቦቻቸው ጥልቅ ሐዘናቸዉን ገለፁ። ንብረትነቱ የላየን ኤር የሆነው የበረራ ቁጥር 610 እና የኢትዮጵው የበረራ ቁጥር 302 ቦይንግ 737 ማክስ አውሮፕላን ላይ በተከታታይ የደረሰው አደጋም ተመሳሳይነት እንዳለው አምነዋል።

በአውሮፕላኑ ላይ ያለውን ችግር ከአብራሪዎች መረዳታቸውን በማመልከትም፣ አውሮፕላኑ አስተማማኝ እንዲሆን ኩባንያቸው አጥብቆ እንደሚሠራ አስታውቀዋል። የደረሰዉን አደጋ መንስኤ መረዳት እና ማጣራት የበረራ ደህንነትን ለማረጋገጥ ወሳኝ ነው ያሉት ዴኒስ ሙሊንበርግ ፤ የቦይንግ ኩባንያ ከአሜሪካ የፌደራል አቪዬሽን አስተዳደር እና ከሶፍትዌር የስልጠና መርሃግብር እና ከሌሎች መሰል ተቋማት ጋር አብሮ እየሰራ መሆኑን አስታውቀዋል።

ቦይንግ ኩባንያ የአውሮፕላኑን የበረራ ሶፍትዌር እያሻሻለ መሆኑን በማመልከትም፣ በመጪው ሳምንታት ከበረራ የተገለለው ቦይንግ 737 ማክስ 8 ዳግም ወደ ሥራ እንዲገባ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ያገኛል የሚል ተስፋ እንዳላቸው ተናግረዋል፡፡ በሶፍትዌሩ ላይ የተደረገው ማሻሻያ፣ ለአብራሪዎችም የሚደረገው ስልጠና አደጋ ያስከተለውን ዓይነት ችግር ዳግም እንዳይከሰት ይረዳል ብለዋል፡፡ አውሮፕላኑ እንዳይበር መደረጉ፣ በደንበኞች እና መንገደኞች ላይ ባስከተለው ተፅዕኖም እንደሚያዝኑ አመልክተዋል።

ባለፈዉ ሳምንት ይፋ በተደረገው የመጀመሪያ ደረጃ ምርመራ፣ መጋቢት 1 ቀን 2011ዓ,ም እንደተነሳ ብዙም ሳይቆይ ቢሾፍቱ አጠገብ የተከሰከሰው የኢትዮጵያ አየር መንገድ የበረራ ቁጥር ET 302 ቦይንግ 737 MAX 8 አውሮፕላን አብራሪዎች፣ አዉሮፕላኑን ከአደጋ ለማዳን የቦይንግ መመሪያ የሚያዘዉን ሁሉ ጥረት ማድረጋቸው ተረጋግጧል፡፡ በውጤቱ መሠረት፣ አብራሪዎቹ በአሜሪካዉ የበረራ ደህንነት ባለስልጣን (FAA) የፀደቀዉና የአዉሮፕላኑ አምራች ኩባንያ የቦይንግ የአስቸኳይ ወይም የአደጋ ጊዜ መመሪያ ብሎ ያወጣውን በሙሉ ገቢራዊ ቢያደርጉም፣ አዉሮፕላኑን ባፍንጫዉ ቁልቁል ከመከስከስ ሊያስቆሙት እንዳልቻሉ አመልክቷል።

# ለተፈናቀሉ ዜጎች ማቋቋሚያ እስከ 700 ሚሊዮን ዶላር ያስፈልጋል ተባለ

የተፈናቀሉ ዜጎች ደህንነታቸውን አስጠብቆ ወደ ቀያቸው መልሶ በዘላቂነት ለማቋቋምም ከ650 እስከ 700 ሚሊየን የአሜሪካ ዶላር እንደሚያስፈልግ በኢትዮጵያ መንግስት ተገለፀ። ተፈናቃዮችን መልሶ ለማቋቋም ከሃገር ውስጥ ባለሀብቶች ገንዘብ እየተፈላለገ ሲሆን፣ በመንግስት በኩል 800 ሚሊየን ብር አካባቢ ተመድቦ እንቅስቃሴ ተጀምሯል፡፡

የተፈናቀሉ ዜጎችን መልሶ ለማቋቋም የሚካሄደው ትግበራ በሶስት ምዕራፍ ተከፋፍሎ የሚደረግ ይሆናል። አንድ ወር በሚወስደው የመጀመሪያው ምዕራፍ፣ ወደ 800 ሺህ ዜጎች ወደቀያቸው የሚመለሱ ሲሆን፥ በሁለተኛው ዙር ተፈናቃዮችን መልሶ ለማቋቋም እስከ ስድስት ወር የሚያስፈልግ ሲሆን፣ በመጨረሻውና በሶስተኛው ዙር ደግሞ፣ እስከ አንድ ዓመት በሚደርስ ጊዜ የመልሶ የማቋቋሙ ሂደት ይከናወናል።

# የሲዳማ ሴቶች የሲዳማ ጥያቄ ምላሽ እንዲሰጠው ጠየቁ

የሲዳማ ሴቶች ብቻ የተሳተፉበት ሰላማዊ ሰልፍ በሀዋሳ ከተማ ተካሄደ፡፡

ሰላማዊ ሰልፉ የሲዳማ የክልል ጥያቄነት አፋጣኝ ምላሽ እንዲሰጠው የጠየቀ ሲሆን፣ ሴቶቹ እርጥብ ቅጠል በመያዝ ሰላማዊ ሰልፉን አካሄደዋል፡፡ የሲዳማ ህዝብ ክልል ለመሆን የጠየቀው ጥያቄ፣ እስካሁን ምላሽ ባለማግኘቱ ቅሬታ እንደተሰማቸው ገልፀዋል፡፡ ሰላማዊ ሰልፉ የሲዳማ አባቶችና ወጣት ወንዶች የካቲት 14 ቀን 2011 ዓ.ም በሀዋሳ ዓለም አቀፍ ስታዲየም ካደረጉት የቀጠለ ነው ተብሏል።

በዚህ ሰልፍ ተሳታፊ የሆኑት እናቶችና ወጣት ሴቶች፣ የሲዳማ ክልል የመሆን ጥያቄ የወንዶች ጥያቄ ብቻ ሳይሆን የእነርሱም ጭምር በመሆኑ፥ ያላቸውን የትግል አጋርነት ለማሳየትና ስሜታቸውን ለመግለፅ አደባባይ መውጣታቸውን ገልፀዋል። ሰላማዊ ሰልፉን በማስተባበር የዞኑ መስተዳድርና ገዥ ፓርቲ ዋናኛውን ሚና መጫወታቸውን የከተማ ነዋሪዎች ተናግረዋል፡፡

# የመምህራን አገልግሎት ኮሚሽን እንደሚቋቋም ተገለፀ

በመምህራን ጉዳዮች ላይ የሚሰራ የመምህራን አገልግሎት ኮሚሽን ሊቋቋም መሆኑን የትምህርት ሚኒስቴር አስታወቀ።የትምህርትን ጥራት ለማሻሻል የትምህርት ሙያተኛውን ኑሮ ማሻሻል ይገባል ተብሏል፡፡ለዚህም ዘርፉን ለመምራት ከሲቪል ሰርቪስ የተለየና ተጠሪነቱም ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሆነ ኮሚሽን እንዲቋቋም የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር መጠየቁ ታውቋል፡፡

ኮሚሽኑ በጥናት ላይ ተመስርቶ የመምህራንን ጥቅማ ጥቅም ለማሰከበር በዝርዝር እንዲሰራ የታሰበ ሲሆን፣ ኮሚሽኑን ለማቋቋም የህግ ማዕቀፎች እየተዘጋጁ ይገኛሉ፡፡ በሚመለከታቸው አካላት ሃሳብ ተሰጥቶበት የትምህርት ማኅበረሰቡን አደረጃጀት፣ ዲሲፒሊኑን

# አልኮል ማስተዋወቅ የሚከለክለው ህግ ከ2 ወር በኋላ ተግባራዊ ይሆናል

አልኮልን በብሮድካስት ማስተዋወቅ የሚከለክለው ህግ ከግንቦት 21 ጀምሮ ተፈጻሚ እንደሚሆን ተገለፀ። ይህን የሚደነግገው የምግብ እና የመድኃኒት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1112፣ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ የካቲት 21 ቀን 2011 ዓ.ም ታትሞ መውጣቱ ይታወሳል። አዋጁ ቁጥር 1112 ባሳለፍነው ጥር 28 ቀን 2011 ዓ.ም በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መፅደቁ ይታወሳል።

በአዋጁ አንቀጽ 74(4) መሰረት የአልኮል መጠጥ በቴሌቪዥን እና ሬድዮ አማካኝነት ማስተዋወቅ ተከልክሏል፡፡ በዚሁ መሰረት፣ ማንኛውም የአልኮል

# የመምህራን አገልግሎት ኮሚሽን እንደሚቋቋም ተገለፀ

በመምህራን ጉዳዮች ላይ የሚሰራ የመምህራን አገልግሎት ኮሚሽን ሊቋቋም መሆኑን የትምህርት ሚኒስቴር አስታወቀ።የትምህርትን ጥራት ለማሻሻል የትምህርት ሙያተኛውን ኑሮ ማሻሻል ይገባል ተብሏል፡፡ለዚህም ዘርፉን ለመምራት ከሲቪል ሰርቪስ የተለየና ተጠሪነቱም ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሆነ ኮሚሽን እንዲቋቋም የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር መጠየቁ ታውቋል፡፡

ኮሚሽኑ በጥናት ላይ ተመስርቶ የመምህራንን ጥቅማ ጥቅም ለማሰከበር በዝርዝር እንዲሰራ የታሰበ ሲሆን፣ ኮሚሽኑን ለማቋቋም የህግ ማዕቀፎች እየተዘጋጁ ይገኛሉ፡፡ በሚመለከታቸው አካላት ሃሳብ ተሰጥቶበት የትምህርት ማኅበረሰቡን አደረጃጀት፣ ዲሲፒሊኑን እንዲሁም፣ ጥቅማ ጥቅሙን በሚመለከት ነጻ በሆነ አካል ተጠንቶ ይቋቋማል የተባለው ኮሚሽኑ፣ ተጠሪነቱ ለህዝብ ተወካየፐች ምክር ቤት እንደሚሆንም ተገልጿል።

የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር በዶክተር ታዬ ወልደ ሰማያት የፕሬዘዳንትትነት ዘመን በነፃነት ለመንቀሳቀስ ያደረገው ሙከራ በኃይል መጨፍለቁ ይታወሳል፡፡ ከዚያ በኋላ ለመንግስትታማኝ በሆኑ አመራሮች መዳፍ ስር ወድቆ ይገኛል፡፡ ዶክተር ታዬ በአሁኑ ጊዜ በስደት በሚኖሩባት አሜሪካ በቀድሞ ዩኒቨርሲቲያቸው (በተመረቁበት ዩኒቨርሲቲ) ውስጥ እያስተማሩ ይገኛሉ፡፡

ኢንተርናሽናል ክራይሲስ ግሩፕ
International Crisis Group
አሜሪካ

# የአባይ ወንዝ ታችኛው ተፋሰስ ሀገራት እና ታላቁ ህዳሴ ግድብ



### እንደመግቢያ

የዓለማችን ረዥሙ ወንዝ፣ አባይ፣ 437 ሚሊዮን ሕዝብ የሚኖርባቸውን 11 የአፍሪቃ ሀገራት አቆራርጦ ያልፋል:: ከኢትዮጵያ ደጋማ አካባቢ የሚፈልቀው ጥቁር ዓባይ፣ እንዲሁም የታላላቅ ሀይቆች ሀገራት ከሆኑት ሩዋንዳ እና ብሩንዲ የሚነሣው ነጭ ዓባይ፣ በግብጽ በኩል ወደ ሜዲተራኒያን ባሕር ከመግባታቸው በፊት በሱዳን ርዕሰ-ከተማ፣ ካርቱም፣ ተገናኝተው 'አባይ' የሚል መጠሪያ የተሰጠውን አንድ ወንዝ ይፈጥራሉ:: ወደሱዳን እና ግብጽ የሚፈስሰው ውኃ፣ ዋነኛው ምንጭ ጥቁር ዓባይ ሲሆን፣ የተከዜ-አትባራ እና የባሮ-አኮቦ-ሶባት ወንዞችም እንዲሁ ከኢትዮጵያ ከፍተኛ ተራሮች የሚነሡ የዚህ ታላቅ ወንዝ ትላልቅ ገባሮች ናቸው:: በአጠቃላይ፣ ከአባይ ወንዝ ውኃ 84% የሚሆነው መነሻው የኢትዮጵያ ደጋማ አካባቢ ነው::የአባይ ተፋሰስ ሀገራት ሕዝቦች፣ ወንዙን ለበርካታ ምዕተ-ዓመታት ለኃይል ምንጭነት፣ ለዓሣ፣ ለመጠጥ ውኃ፣ ለእርሻ፣ ለመዝናኛ፣ እንዲሁም ለቱሪዝም ተጠቅመውበታል፣ እየተጠቀሙበትም ነው::

አባይ ከሌሎች የዓለማችን ትላልቅ ወንዞች ጋር ሲነፃፀር፣ ብዙም ውኃ ይዞ አይጓዝም:: ለምሳሌ፣ የአባይ ይዘት፣ የኮንጎ ወንዝ ይዞት ከሚጓዘው ውኃ 5% ብቻ ነው:: የሕዝብ ቁጥር መጨመር እና የዓየር ንብረት ለውጥ የአባይ ውኃ አቅርቦትን ተለዋዋጭ ባደረገበት በአሁኑ ዘመን፣ በተፋፈሱ ሀገራት መካከል በሚኖረው ግንኙነት ላይ ተጽዕኗቸውን የሚያሳድሩት ውኃውን ለመቆጣጠር የሚደረጉ ጂኦፖለቲካዊ ፍልሚያዎች ከጊዜ ወደጊዜ እየተጠናከሩ መጥተዋል::

ግብጽ ለበርካታ ምዕተ-ዓመታት የአባይ ወንዝ ውኃን ሙሉ በሙሉ ያለገደብ ስትጠቀምበት ቆይታለች:: የእንግሊዝ ቅኝ አገዛዝ ባለሥልጣናት በበኩላቸው፣ በ1902 እና 1929 (እ.አ.አ.) በግብጽ እና በሱዳን ስም በተደራደሯው ስምምነቶች፣ ካይሮ የአባይ ውኃ ዋነኛ ተጠቃሚነቷን ከዓለም ዓቀፍ ሕግ አንጻር አስረግጠዋል:: ግብጽ እና በቅርቡ ነጻነቷን የተቀዳጀችው ሱዳን፣ የቀድሞዎቹን ሁለት ስምምነቶች ይበልጥ የሚያጠናክር ስምምነት በ1959 (እ.አ.አ.) ተፈራርመዋል:: ግሪካዊው ታሪክ ጸሐፊ፣ ሄሮዶቱስ፣ "የአባይ ስጦታ" ሲል የገለጻት ግብጽ፣ ህልውናዋ በአባይ ውኃ ላይ የተመሠረተ ነው:: ስለዚህም፣ የውኃ ፍላጎቷን ለማሟላት እና የላይኛው ተፋሰስ ሀገራት የውኃ ፍሰቱን የሚያደናቅፉ ፕሮጄክቶችን ተግባራዊ እንዳያደርጉ ለመከላከል ያልፈነቀለችው ድንጋይ የለም:: በአነስተኛ መጠን ቢሆንም፣ ሱዳንም ብትሆን የአባይ ወንዝ ጥገኛ ናት::

ኢትዮጵያ የቅኝ አገዛዝ ዘመን ስምምነቶች የአንዱን ወገን ጥቅም ብቻ ታሳቢ ያደረጉ ናቸው በሚል መነሻ፣ ይህን ሁኔታ አጥብቃ ስታቃወም ቆየታለች:: የወንዙን ውኃ ተጠቅማ ኢኮኖሚዋን ማሳደግ የምትፈልገው ኢትዮጵያ፣ የ1902 (እ.አ.አ.) ስምምነቱ የዘውድ አገዛዙ ያለፈ ታሪክ አካል ነው፣ እንዲሁም በቀጣዮቹ ሁለት ስምምነቶች ዙሪያ ሐሳቧን አልተጠየቅኩም በማለት፣ ዕውቅናዋን ለመስጠት ፈቃደኛ ሳትሆን ቀርታለች::

በዚህም ምክንያት፣ ኢትዮጵያ መጋቢት 30/2011 (እ.አ.አ.) በጥቁር ዓባይ ወንዝ ላይ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ በሚል መጠሪያ የሚታወቅ ግዙፍ ግድብ የመገንባት ዕቅዷን ይፋ ማድረጓ፣ በካይሮ እና በካርቱም መንግሥታት ዘንድ ከባድ ጭንቀት መፍጠሩ ብዙም ሊገርመን አይገባም:: በወቅቱ፣ ሁለቱ የታችኛው ተፋሰስ ሀገራት ሳይውሉ ሳያድሩ ቁጣን በተላበሰ መልኩ ኢትዮጵያ ፕሮጄክቱን ተግባራዊ ከማድረግ እንድትቆጠብ አሳስበዋል:: ከዚህን ጊዜ ወዲህ የህዳሴው ግድብ የአባይ ውኃ ሙግት ዋነኛ መገለጫ ሆኗል:: ቀደም ሲል ከግብጽ ጋር በመወገን የግድቡን ግንባታ አጥብቃ ስትቃወም የቆየችው ሱዳን፣ በአሁኑ ወቅት አቋሟን አለሳልሳለች፤ ይሁንና፣ ሙግቱ እስካሁን ድረስ መቋጫ አልተበጀለትም:: ኢትዮጵያ ግድቡን የምትፈልገው የኤሌክትሪክ ኃይል ለማመንጨት እና ለኢንዱስትሪ ልማት ነው፤ ግብጽ በበኩሏ፣ 'ፕሮጄክቱ የውኃ አቅርቦትን ይጐዳዋል' የሚል ሥጋት አላት፤ ሱዳን ደግሞ፣ ግድቡ በክረምት ወቅት የሚፈጠረውን ጐርፍ በመቆጣጠር፣ የግብርና ምርቷን ለማሳደግ እንደሚያግዛት ተስፋ አድጋለች:: የህዳሴው ግድብ እየተካሄደ ባለበት በአሁኑ ወቅት፣ የታችኛው የተፋሰሱ ሀገራት በአባይ ውኃ አስተዳደር፣ በተለይም ኢትዮጵያ ሰው ሠራሽ ሐይቁን በውኃ በምትሞላበት ፍጥነት፣ ዙሪያ ከስምምነት ላይ መድረሳቸው ወሳኝ ነው::

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ባለሥልጣን በየካቲት 2019 (እ.አ.አ.) ሦስተኛው ሳምንት በ2022 (እ.አ.አ.) ይጠናቀቃል ተብሎ ለሚጠበቀው የግድቡ ሥራ፣ ከሁለት የቻይና ኩባንያዎች የኮንትራት ስምምነት መፈራረሙን አስታውቋል:: የኢትዮጵያ የውኃ ሀብት ሚኒስትር እንደገለጹት፣ ግድቡ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨት የሚጀምረው በ2020 (እ.አ.አ.) ነው:: የፕሮጄክቱ ሥራ እንደተጀመረ፣ ግድቡ በ2017 (እ.አ.አ.) የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨት ይጀምራል ተብሎ ነበር፤ ይሁንና፣ በአስተዳደራዊ እና በፋይናንስ ችግሮች ሳቢያ ዕቅዱ ተግባራዊ ሳይሆን ቀርቷል:: በአሁኑ ወቅት የተከሰተው የግድቡ ግንባታ መዘግየት፣ ፕሮጄክቱ የሚመለከታቸው ሀገራት ግድቡ በውኃ ፍሰት ላይ በሚኖረው ተጽዕኖ ዙሪያ ከስምምነት ላይ ለመድረስ ጥሩ ዕድል ይሰጣቸዋል:: የግድቡ ሥራ እስኪጠናቀቅ ድረስ መጠበቁ፣ በሀገራቱ መካከል ግጭት የሚፈጠርበትን ዕድል ከፍ የሚያደርገው ይሆናል::

## ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ እና የህዳሴው ግድብ

በገዢው ፓርቲ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ ግንባር (ኢ.ሕ.አ.ዲ.ግ.)፣ ውስጥ የታቀፉ አንዳንድ የአመራር አባላት አዲሱ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር፣ የህዳሴ ግድብን በተመለከተ ያላቸውን አቋም ቢጠራጠሩም፣ ዐቢይ የፕሮጄክቱ ግንባታ እንዲቀጥል ያላቸውን ቆራጥነት አሳይተዋል:: ይሁን እንጂ፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሀገሪቷ ኢኮኖሚ ነፍስ እንዲዘራበት የሚያደርጉ የለውጥ እርምጃዎችን መውሰድ እና ቀቢጸ-ተስፋቸውን በየጐዳናው ወጥተው ለገለጹት ሥራ አጦች የሥራ ዕድል መፍጠር ይጠበቅባቸዋል:: በርካታ ኢትዮጵያውያን ደግሞ፣ የህዳሴው ግድብ በዚህ ረገድ

ወደ ቀጣዩ ገጽ 11

ትልቅ እገዛ እንደሚያደርግ ያምናሉ:: የግድቡ ግንባታ ሲጠናቀቅ ሥር የሰደደውን የኃይል አቅርቦት እጥረትን ከመቅረፍ ባለፈ፣ ዋነኛ የውጭ ምንዛሬ ምንጭ መሆኑ አይቀርም::

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ የመራሔ መንግሥትነት ሥልጣናቸውን ከተረከቡ ከጥቂት ሳምንታት በኋላ ከግንብታው ዋና ሥራ እስኪያጅ፣ ኢንጂኔር ስመኘው በቀለ፣ ጋር ግድቡን በመጐብኘት፣ ግድቡ ለኢትዮጵያ ያለውን ጠቀሜታ አሥምረውበታል:: ይሁን እንጂ፣ ስመኘው ሐምሌ 26/2018 (እ.አ.አ.) በመኻል አዲስ አበባ፣ መስቀል አደባባይ፣ መኪናቸው ውስጥ ሞተው በመገኘታቸው፣ ፕሮጀክቱ አንድ ተጨማሪ መሰናክል ገጥሞት ነበር:: የስመኘው ስም ከግድቡ ጋር በመተሳሰሩ፣ በኢትዮጵያውያን ዘንድ ትልቅ ክብር አስገኝቶላቸዋል፤ በሺሕዎች የሚቆጠሩ ዜጎች አዲስ አበባን ጨምሮ በተለያዩ የሀገሪቷ ከተሞች የተሰማቸውን ኀዘን ገልጸዋል:: ብዙኃን መገናኛዎች ኢንጂኔሩ የተገደሉት በሰው እጅ እንደሆነ ግምታቸውን ቢሰነዝሩም፣ ፖሊስ በስተመጨረሻ ላይ 'ራሳቸውን አጥፍተዋል' ከሚል ድምዳሜ ላይ መድረሱን አስታውቋል::

ይህ በእንዲህ እያለ፣ ጠቅላይ ሚኒስር ዐቢይ በሰጡት የመጀመሪያው ጋዜጣዊ መግለጫ፣ የብረታ ብረት ኢንጂኔሪንግ ኮርፖሬሽን (ሜቴክ) ለግድቡ ግንባታ የገባውን ቃል በማጠፉ፣ ተቋሙ ከዚህን ጊዜ ወዲህ ከግድቡ ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት እንደማይኖረው አስታውቀዋል:: ይህን ተከትሎ፣ ፖሊስ 63 የሜቴክ የሥራ ኃላፊዎችን ኀዳር 12/2018 (እ.አ.አ.) በቁጥጥር ሥር አውሏል::

የኢትዮጵያ ባለሥልጣናት እንደሚሉት፣ የግንባታው ሥራ 60% ተጠናቅቋል፤ የግድቡን ግንባታ የጐበኙ ምዕራባውያን ዲፕሎማቶች በበኩላቸው፣ አብዛኛው የመሠረተ-ልማት አውታር ግንባታ መጠናቀቁን ገልጸዋል:: ይሁን እንጂ፣ በቀጣይነት በግድቡ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ውስብስብ ሥራዎች ይቀራሉ፤ የኢትዮጵያ መንግሥትም ተርባይኖችን እና ጄነሬተሮችን የመግጠሙን ኃላፊነት ቻይና ጌዞባ ግሩፕ እና ቮይት ሃይድሮ ሻንጋይ ለተባሉ ሁለት የቻይና ኩባንያዎች ሰጥቷል:: ከዚህ በተጨማሪም፣ የኢትዮጵያ መንግሥት ባጋጠመው አሳሳቢ የውጭ ምንዛሬ እጥረት የግንባታውን የመጨረሻ ምዕራፎች ለማጠናቀቅ እና የዋና ተቋራጩን ሂሳብ ለመክፈል ውጥረት አለበት::

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ለታችኛው ተፋሰስ ሀገራት፣ ማለትም ለግብጽ እና ለሱዳን፣ ጭንቀት እና ፍላጎት ከቀድሞዎቹ የኢትዮጵያ መሪዎች የተሻለ የተቆርቋሪነት ስሜት አሳይተዋል:: ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ የደኅንነት መሥሪያ ቤቱን ኃላፊ፣ ጌታቸው አሰፋ፣ እና የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኤታ ማዦር ሹሙን፣ ሌተናንት ጄነራል ሳሞራ ዩኑስ፣ ሰኔ 2018 (እ.አ.አ.) በጡረታ እንዲገለሉ መወሰናቸው፣ በካይሮ መንግሥት ዘንድ ደስታን ፈጥሯል፡፤ ግብጽ ሁለቱ ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣናት የአባይ ወንዝን በተመለከተ ጽንፈኛ አቋም ያራምዳሉ የሚል አመለካከት ነበራት::

## የግብጽ አዲስ ሕገ - መንግሥት አቋም

የታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታን በተመለከተ፣ የግብጽ ባለሥልጣናት ቀዳሚው ኃላፊነት ፕሮጀክቱ ሲጠናቀቅ ሀገሪቷ ከአሳሳቢ የውኃ እጥረት ችግር ጋር አለመፋጠጧን ማረጋገጥ ነው:: ለጸጥታ ኃይሎች ቀረቤታ ያላቸው የግብጽ ብዙኃን መገናኛዎች በበኩላቸው፣ ግድቡ የግብጽ ህልውናን ሥጋት ላይ የሚጥል እንደሆነ በተደጋጋሚ ዘግበዋል:: በመጋቢት 2018 (እ.አ.አ.) በግብጽ በተካሄደው ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ፣ ሁሉም ዕጩዎች ሀገሪቷ በአባይ ወንዝ ያላትን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ለመራጩ ሕዝብ ቃል ገብተዋል:: አልፎ ተርፎም፣ በ2014 (እ.አ.አ.) በጸደቀው የሀገሪቷ አዲስ ሕገ-መንግሥት መሠረት፣ ግዛተ-መንግሥቱ ግብጽ የአባይ ወንዝን በተመለከተ ያሏትን "ታሪካዊ መብቶች" ጠብቆ የማቆየት ግዴታ ተጥሎበታል::

ፕሬዚዳንት አብደል ፈታህ አል-ሲሲ በ2014 የግብጽ ፕሬዚዳንት ሆነው ከተመረጡ ወዲህ ሀገራቸው በአባይ ወንዝ ዙሪያ የምታካሂደውን ዲፕሎማሲያዊ እንቅስቃሴ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ አጠናክረው ቀጥለውበታል:: አል-ሲሲ የመሪነቱን እርካብ ከጨበጡ በኋላ፣ የደኅንነት እና የዲፕሎማሲ መዋቅሮች ካይሮ ከአዲስ አበባ እና ከካርቱም ጋር ከስምምነት ላይ እንድትደርስ ተንቀሳቅሰዋል:: በተደጋጋሚ በተካሄዱ ድርድሮችም፣ ሦስቱ ሀገራት ኢትዮጵያ የታችኛው የተፋሰሱ ሀገራትን በህዳሴ ግድብ ሳቢያ ሊፈጠሩ ከሚችሉ "ከባድ ጉዳቶች" የመጠበቅ ኃላፊነትን የተቀበለችበት የመጋቢት 2015 (እ.አ.አ.) "የመርሆዎች ሰነድ" ለመፈራረም በቅተዋል::

የግብጽ ዲፕሎማቶች የግድቡን ግንባታ ማስቆም እንደማይቻል አምነው ቢቀበሉም፣ ኢትዮጵያ እና ሱዳን መጋቢት 23/2015 የፈረሙት "የመርሆዎች ሰነድ" ተገዢ እንዲሆኑ ለማሳመን ብርቱ ጥረት አድርገዋል፤ ቀደም ሲል እንደተገለጸው፣ በዚሁ ሰነድ መሠረት፣ ሁሉም ባለድርሻ አካላት የህዳሴው ግድብ በታችኛው የተፋሰሱ ሀገራት ላይ ከባድ ጉዳቶችን እንዳያደርስ የማረጋገጥ ኃላፊነት ተጥሎባቸዋል:: በዚህም መሠረት፣ ሀገራቱ የህዳሴው ግድብ የታችኛው የተፋሰሱን ሀገራት የአባይ ወንዝ የውኃ ፍሰት በአሳሳቢ ደረጃ አለመቀነሱን የማረጋገጥ ግዴታ አለባቸው:: የታችኛው የተፋሰሱ ሀገራት ለዚህ ጉዳይ ትኩረት የሰጡት ኢትዮጵያ የሕዳሴው ግድብ መጠናቀቁን ተከትሎ የልብ ልብ ተሰምቷት 45,000 ሜጋ ዋት የማመንጨት እምቅ ዓቅሟን በቀጣይነት እንዳትጠቀም ለማሳመን ካላቸው ፍላጎት የመነጨ ነው:: በእርግጥ፣ ካይሮ ይህን መሰሉን አካሄድ አጥብቃ እንደምትቃወመው ሳይታለም የተፈታ ጉዳይ ነው::

የተፋሰሱ ሀገራት በ2015 (እ.አ.አ.) የህዳሴ ግድቡ ሊያስከትለው በሚችለው ጉዳት ዙሪያ ከአንድ የፈረንሳይ እና ከአንድ የኔዘርላንድ ተቋማት ጋር ከስምምነት ላይ ደርሰው ነበር:: ይሁን እንጂ፣ በካይሮ የተመረጠው የኔዘርላንዱ ተቋም ሥራውን አቋርጧል:: ከዚህ በተጨማሪም፣ የግብጽ ባለሥልጣናት የኢትዮጵያ መንግሥት በሂደቱ 'በቂ ትብብር አላሳየም' ሲሉ ውንጀላቸውን ሰንዝረዋል:: የፈረንሳዩ ተቋም በበኩሉ፣ ሥራውን በመቀጠል፣ በፕሮጀክቱ ዙሪያ ተጨማሪ ግምገማ እንደሚያስፈልግ የሚገልጽ ሪፖርት ቢያወጣም፣ ባለድርሻ አካላቱ ሂደቱ በሚቀጥልበት አሠራር ላይ ከስምምነት ላይ መድረስ አልቻሉም:: የግብጽ መንግሥት በታኅሣሥ 2017 (እ.አ.አ.) የዓለም ባንክ ፕሮጀክቱን በገለልተኝነት እንዲያጠና ሐሳብ ቢያቀርብም፣ ኢትዮጵያ ውድቅ አድርገዋለች::

የግብጽ፣ የሱዳን እና የኢትዮጵያ የውኃ እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች (እ.አ.አ.) አዲስ አበባ ተገናኝተው ፕሮጀክቱን የሚያጠና አንድ የባለሙያዎች ቡድን ለማቋቋም ተስማምተዋል:: ያም ሆኖ፣ ስምምነቱ እያንዳንዱ የተፋሰሱ ሀገር የየራሳቸውን ባለሙያዎች እንዲቀጥሩ እና የየራሳቸውን ሪፖርት እንዲያቀርቡ ስለሚፈቅድ ሂደቱ ብዙም ርቀት መጓዝ አልቻለም::

የምዕራቡ ዓለም ባለሥልጣናት፣ የግብጽ መንግሥት በህዳሴ ግድብ ዙሪያ በሚያራምዱት አቋም እና በግብጽ የውኃ አጠቃቀም ደስተኞች አይደሉም:: ይሁን እንጂ፣ ግብጽ የህዳሴ ግድቡ በሚኖረው ተጽዕኖ ዙሪያ የተሟላ ጥናት እንዲካሄድ የምታራምደውን አቋም ይደግፋሉ::

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ከቅርብ ጊዜ በፊት ከግብጽ ጋር የፈጠሩት ግንኙነት፣ በሁለቱ ሀገራት መካከል የነበረውን ውጥረት ለማርገብ ቢያግዝም፣ አሁንም ቢሆን የሚተያዩት በጥርጣሬ ዓይን ነው:: ግብጽ ስለአዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር የሥልጣን ዕድሜ እርግጠኛ ባለመሆኗ እና 'ኢትዮጵያ የግብጽን የአባይ ወንዝ ተጠቃሚነት ለመጉዳት ፍላጎት የላትም' ማለታቸውን ባለማመን፣ ዐቢይን እና አስተዳደራቸውን በተመለከተ በቀጣይነት የሚሆነውን ነገር መጠባበቁን መርጣለች::

የግብጽ ባለሥልጣናት የግድቡ ግንባታ እንደማይቆም ቢያውቁም፣ ሕዝባቸውን ለዚሁ እውነታ ለማዘጋጀት በቂ ሥራ አልሠሩም:: የግብጽ ብዙኃን መገናኛዎች 'ወታደራዊ እርምጃ የግድቡን ግንባታ ሊያስቆመው ይችላል' የሚሉ ሐሳቦችን ከመሰንዘር ቦዝነው አያውቁም:: የሀገሪቱ የፕሬስ ውጤቶች እና የማኅበራዊ ሚዲያ ገጾች፣ ስለካይሮ ወታደራዊ ዓቅም የበላይትና በላይኛው የተፋሰሱ ሀገራት ላይ ኃይል መጠቀም እንደሚያስችላት፣ እንዲሁም የህዳሴው ግድብ የሀገራቸው ብሔራዊ የደኅንነት ሥጋት እንደሆነ ገልጸዋል፣ እየገለጹም ነው::

## የሱዳን አቋም

ሱዳን በህዳሴ ግድቡ ተጠቃሚ እንደምትሆን የታወቀ ነው:: ለእርሻ አገልግሎት ሊውል የሚችል ሰፊ መሬት እና የውኃ ሀብት ያላት በመሆኗ፣ ሱዳን የእርሻ ክፍለ-ኢኮኖሚዋን የማሳደግ ትልቅ ዕድል አላት:: የህዳሴው ግድብ ሲጠናቀቅ፣ ሱዳን ቀደም ሲል በጐርፍ የመጥለቅለቅ አደጋ ስለሚቀንስላት፣ ሀገሪቷ በየዓመቱ ከእርሻ መሬቷ የአፈር ደለል ለማንሣት የምታወጣውን በሚሊዮን የሚቆጠር የአሜሪካ ዶላር ያስቀርላታል:: ከዚህም በላይ፣ ግድቡ ሱዳን በዓመት ውስጥ የምታገኘው የአዝመራ ብዛት እንዲጨምር ያግዛል:: የግድቡ ግንባታ የሚፈጠረው ሰው ሠራሽ ሐይቅ በውኃ ሲሞላ፣ ሱዳን በሚሊዮኖች የሚቆጠር ሄክታር አዲስ የእርሻ መሬት በመስኖ ማልማት ትችላለች::

የህዳሴ ግድቡ ለሱዳን የሚሰጠው አንድ ሌላ ተጨማሪ ጥቅም አለ:: ካርቱም ከኢትዮጵያ የምትገዛው የኤሌክትሪክ ኃይል በሀገር ውስጥ ከምታመርተው ዋጋው ዝቅ ማለቱ አይቀርም:: ከዚህ ጋር በተያያዘም፣ የራሷን የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨት ትችላለች::

በዚህም ምክንያት፣ ሱዳን በአብዛኛው የግድቡን ግንባታ ደግፋዋለች:: 'ግድቡ የውኃ ፍሰትን ይቀንሳል' የሚለውን የግብጽ ሥጋት በማጣጣል፣ ካይሮ ከግድቡ ከሚገኘው የኤሌክትሪክ ኃይል ተጠቃሚ መሆን ስለምትችል ግንባታውን እንድትቀበል ግፊት አድርጋለች:: የሱዳን ዋነኛ ጥያቄ ኢትዮጵያ በፕሮጀክቱ ዙሪያ ግልጽ ጥናት እንዲካሄድ ነው:: ከዚህ ጋር በተያያዘ በግድቡ ላይ የሚኖር ማንኛውም የግንባታ ጉድለት በሱዳን ላይ ትልቅ ጉዳት ያስከትላል የሚል ጭንቀት በካርቱም መንግሥት ዘንድ አለ፤ ግድቡ የሚገነባው ኢትዮጵያን ከሱዳን ጋር በሚያዋስናት ድንበር አካባቢ ሲሆን፣ ግድቡ ቢሰነጠቅ ወይም ቢፈርስ ከባድ የጐርፍ አደጋ ሊያስከትል ይችላል:: ያም ሆኖ፣ ሱዳን የሦስትዮሽ ድርድሩ እንዲቀጥል ገንቢ ሚና ተጫውታለች::

ሱዳን የህዳሴውን ግድብ በተመለከተ የምታራምደው አቋም፣ ከግብጽ ጋር ያላትን ግንኙነት አሻክሮታል:: ሁለቱ ሀገራት በቀይ ባሕር ዳርቻ በሚገኘው የሃላዩብ ግዛት የይገባኛል ጥያቄ እየተወዛገቡ ባለበት በአሁኑ ወቅት፣ ካርቱም ለሙስሊም ወንድማማችነት

**“**

**በግድቡ ላይ የሚኖር ማንኛውም የግንባታ ጉድለት በሱዳን ላይ ትልቅ ጉዳት ያስከትላል የሚል ጭንቀት በካርቱም መንግሥት ዘንድ አለ**

አባላት መጠለያ መስጠቷ በካይሮ ዘንድ ቅያሜን ፈጥሯል:: ከዚህ በተጨማሪም፣ ፕሬዚዳንት ኦማር አል-በሽር በግድቡ ዙሪያ የተለሳለሰ አቋም መያዛቸው ካይሮን አበሳጭቷታል:: በሌላ በኩል፣ የግብጽ መንግሥት ሱዳንን በክልሉ የእስላማዊነት ንቅናቄ ማዕከል አድርጎ ይመለከታታል::

ካርቱም ከአዲስ አበባ ጋር ያላት ግንኙነት በአመዛኙ ከካይሮ ጋር ካላት የተሻለ ነው:: የፕሬዚዳንት አል-በሽር መንግሥት በትጥቅ ትግሉ ወቅት በኢ.ሕ.አ.ዲ.ግ. መንግሥት ከፍተኛ የሥልጣን እርከን ላይ ከሚቀመጡ ባለሥልጣናት ጋር ጥሩ ግንኙነት መሥርቷል:: ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ለደቡብ ሱዳን ንቅናቄ በሰጡት ድጋፍ የሁለቱ ሀገራት ግንኙነት ቢሻከርም፣ በሂደት ተሻሽሏል:: ኢትዮጵያ በቅርቡ ከኤርትራ ጋር የሰላም ስምምነት እስከተፈራረም ድረስ ካርቱም እና አዲስ አበባ የአስመራ ጠላቶች ነበሩ፤ የካርቱም መንግሥት የፕሬዚዳንት ኢሳይያስ አፈወርቂ መንግሥት 'በምሥራቃዊ ሱዳን የሚንቀሳቀሱ ዐማፂያንን ይደግፋል' በሚል ይወነጅለው ነበር::

ሱዳንን ከሚያሳስቧት ጉዳዮች መካከል አንዱ፣ 'ፕሬዚዳንት አል-በሽር የህዳሴ ግድቡን ጠቀሜታ ለመቋደስ በሥልጣን ላይ ይቆዩ ይሆን?' የሚለው ነው:: ፕሬዚዳንት አል-በሽር በሥልጣን ላይ የመቆየታቸው ጉዳይ እንዳለ ሆኖ፣ ሱዳን የህዳሴው ግድብ ተጠቃሚ ለመሆን የሚያስፈልጓትን የመሠረተ-ልማት አውታሮች ለመገንባት የሚያስፈልገውን ገንዘብስ ታገኝ ይሆን? በእርግጥ፣ በዚህ ረገድ ለጋሾችን ወይም አበዳሪዎችን ማግኘቱ ቀላል አይሆንም:: በሱዳን ያለው የግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ የኢንቬስትመንት ድባብ ደካማ ከመሆኑም ሌላ፣ በርካታ የውጭ ኢንቬስተሮች በዚህ ረገድ የሀገሪቷን ቀጣይ ሁኔታ ማየቱን መርጠዋል:: ፕሬዚዳንት አል-በሽር ትኩረት የሰጡት ለሀገሪቱ የጸጥታ ሁኔታ እንጂ ለኢኮኖሚው አይደለም::

## እንደመደምደሚያ

የታችኛው ተፋሰስ ሀገራት በአባይ ወንዝ ዙሪያ የተፈጠረውን አለመግባባት ለመፍታት ሦስቱንም ሀገራት፣ ማለትም ግብጽ፣ ሱዳን እና ኢትዮጵያ፣ ተጠቃሚ ከሚያደርግ ስምምነት ላይ መድረስ ይኖርባቸዋል:: በዚህም መሠረት፣ ሰው ሠራሽ ሐይቁ በውኃ የሚሞላበትን የጊዜ ገደብ ማስቀመጥ ይኖርባቸዋል:: ይኸው እርምጃ በአባይ ወንዝ ውኃ አጠቃቀም ዙሪያ ከታችኛው የተፋሰሱ ሀገራት ባለፈ፣ የላይኛው የተፋሰሱ ሀገራትም ፍትሐዊ ተጠቃሚ የሚሆኑበት ዕድል ይፈጠራል::

የህዳሴው ግድብ የኢትዮጵያን ኢኮኖሚን እንደሚያሳድግ ምንም ጥርጥር የለውም፤ ይሁንና፣ እንደመንግሥት ፕሮፓጋንዳ ሀገሪቷን ፍጹም የሚለውጥ አይደለም:: የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ደካማ ከመሆኑም ባሻገር፣ ረዥም የለውጥ ሂደት ያስፈልገዋል:: ከአምስት ኢትዮጵያውያን መካከል አራቱ የሚኖሩት በገጠር ነው:: ከሀገሪቷ ሕዝብ 85% ያህሉ የሚተዳደረው ከእጅ ወደአፍ በሆነ የግብርና ዘርፍ ነው:: የህዳሴው ግድብ የኢትዮጵያን ደካማ ኢኮኖሚ ለማሳደግ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ይታመናል::

ሱዳን የኢንቬስትመንት ድባቧን ለማሻሻል፣ እንዲሁም ለእርሻ መዋል የሚችለውን ሰፊ መሬቷን ለማልማት የሚያግዙ እርምጃዎችን መውሰድ ይኖርባታል:: ሀገሪቷ፣ ግብጽን ጨምሮ፣ ከክልሉ ሀገራት ጋር መተባበር ይኖርባታል:: በሂደቱም፣ ሱዳን የውጭ ምንዛሬ ስታገኝ፣ ግብጽም የምግብ ዋስትናዋን ማረጋገጥ ትችላለች::

ከክልሉ ሀገራት ጋር ሲነፃፀር ግዙፍ ኢኮኖሚ ያላት ግብጽ በበኩሏ፣ ለሌሎቹ የተፋሰሱ ሀገራት ማጋራት የምትችለው ብዙ ነገር አላት:: ይህ በእንዲህ እያለ፣ ከተፋሰሱ ሀገራት መካከል ለከፍተኛ የውኃ እጥረት የተጋለጠች ሀገር ናት:: ስለዚህም፣ እነኝህን ሁኔታዎች ሁሉንም የተፋሰሱን ሀገራት በሚጠቅም መልኩ ማጣጣሙ፣ ግብጽን በከፍተኛ ሁኔታ የሚጠቅማት ይሆናል::



# “የህወሓት ማብቂያ እዛው (ትግራይ) እንደሆነ ይሰማኛል”

## ዛዲግ አብርሃ
## የቀድሞ ሚኒስተር የህወሓት ከፍተኛ አመራር አባል

**ዛዲግ አብርሃ የቀድሞ የህወሓት ከፍተኛ አመራር የነበሩ ሲሆን፣ አሁን ደግሞ፣ ድርጅቱን ለቀቅው በእንግሊዝ ሀገር ለዶክትሬት ዲግሪያቸው እየተማሩ ይገኛሉ፡፡ ዛዲግ ድርጅቱን ለመልቀቅ ካበቃቸው ምክንያቶች መካከል በህወሓት ውስጥ ያለው ፀረ ዲሞክራሲያዊነትና በራያ ተወላጆች ላይ ይፈፀማል ያሏቸው አድልኦ ይገኙባቸዋል፡፡ ድርጅቱን ከለቀቁ በኋላ እህታቸው በፖሊስ ተይዘው ለእስር ተዳርገዋል፡፡ ዛዲግ ትምህርታቸውን እንደጨረሱ ወደ ሀገር ቤት በመመለስ፣ የራያ ህዝብ የማንነት ጥያቄ ምላሽ እንዲያገኝ እንደሚታገሉ አስታውቀዋል፣ እኛም የዚህ ሳምንት እንግዳ አድርገናቸዋል፡፡**

**ኢትዮጲስ፡-** **ህወሓት በተለያዩ አጋጣሚዎች ጥልቅ ተሃድሶዎችን ያለቸውን አድርጓል፡፡ እነዚያን እንቅስቃሴዎች እንዴት ይመለከቷቸዋል?**

**ዛዲግ፡-** እንደሚታወቀው TPLF (ህወሓት) በተለያዩ አጋጣሚዎች እራሴን አስተካክላለሁ በማለት የተሃድሶ እንቅስቃሴዎች አድርጎ ነበር:: ለ44 ዓመታት በተለያዩ ጊዜያት አቋም ለማስተካል ጥልቅ ተሃድሶዎችን ሲያደርግ ነበር:: የህወሓት ጥልቅ ተሃድሶ ወይንም አቋምን የማስተካከል ሥራ የተጀመረው ገና ዳዴ የማለት እንቅስቃሴ በጀመረበት በ1968 ዓ.ም ነበር:: በዚህ የአቋም ማስተካከያ እንቅስቃሴዎች እራሱን ከመክሰም ሊታደግ ችሏል:: ሆኖም፣ የማስተካከል እንቅስቃሴው ዲሞክራሲያዊ ባልሆነ መንገድ የተንቀሳቀሰበት ሂደት ነበር:: ሌላው ደግሞ፣ በ1978 እና 1979 አካባቢም ትልቅ ችግር ገጥሞት በድጋሜ እራሱን ለማስተካከል ጥልቅ ተሀድሶ አድርጎ ነበር፤ ይሄኛውም ቢሆን ብዙ ችግሮች ነበሩበት:: ካደረጋቸው የጥልቅ ተሃድሶዎች መካከል በሦስተኛነት የሚጠቀሰው በ1993 ዓ.ም ያደረገው ነው፤ ይህ ወቅት አመራሩ የተከፋፈለበት ጊዜ ነበር:: በተመሳሳይ መልኩ፣ ከ10 ዓመት ቆይታ በኋላ በ2006 ዓ.ም ሌላ ጥልቅ ተሃድሶ አድርጎ ነበር:: ከዚህ በተጨማሪ፣ 2008 ዓ.ም ያደረገው ጥልቅ ተሃድሶ ሳይሳካለት ወይንም የተሰበውን ያክል ውጤት ሳያመጣ ቀርቷል::

ህወሓት ያደረጋቸውን ሁሉንም ጥልቅ ተሃድሶዎች ብንመለከት፣ መነሻቸው ፀረ ደሞክራሲ አሰራር የለም የሚል ነበር፤ ሁሌም መነሻ ምክንያቱ ዲሞክራሲያዊ ድርጅት መሆን አለመቻሉ ነው:: ተሃድሶው በዚህ መሰረታዊ ነጥብ ዙሪያ ማውጠንጠን ሲገባው ግን፣ አብዛኛው ጊዜ የሚጠፋው በአባላቱ የስልጣን ፉክክር ነው:: ስለዚህ ጥልቅ ተሃድሶዎች የሚደረጉት እውነተኛ ዲሞክራሲ ለማምጣት ነው ቢባልም፣ በተግባር ግን የግለሰቦችን የስልጣን ጥማት ለማርካት ይሆናል:: ይህ መሆኑ ህወሓትን ታጥቦ ጭቃ አድርጎታል፤ ሲጀምርም ሲጠናቀቅም በፀረ ዲሞክራሲያዊነቱ ፀንቶ ነው የቀረው:: በዚህ ምክንያት፣ የህወሓት የጥልቅ ተሃድሶ ሙከራ ያልተሳካና ለግለሰቦች ጥቅም ብቻ የሚደረግ ነበር ማለት ይቻላል::

ህወሓት “መስርቸዋለሁ (ፈጥሬዋለሁ)” የሚለው አብዮታዊ ዲሞክራሲ፣ አይደለም ለህዝብ፣ ለኢህአዴግ አመራሮች እንኳን አልጠቀምም:: የህወሓት አብዮታዊ

ወደ ቀጣዩ ገጽ 13

ዲሞክራሲ፣ በራሱ በድርጅቱ ውስጥ የነበሩ አመራሮች እንኳን ሃሳባቸውን በነፃነት መግለፅ እንዳይችሉ የሚያሽማቅቅ ነው። በተግባር ደረጃ፣ ህወሓት ራሱንም ሆነ ሀገሪቱን ዲሞክራሲያዊ ለማድርግ አልቻለም። ከዚያ ይልቅ፣ ህዝብ በተለያዩ አጋጣሚዎች የሚያነሳቸውን ጥያቄዎች በበጎ ጎኑ የሚመለከቱ አመራሮችን ከስልጣናቸው ማንሳት ዋነኛ ተግባሩ ነበር፤ አሁንም በዚያው ቀጥሏል።

እኔ በህወሓት አባል በነበርኩበት ጊዜ ከፍተኛ የኃላፊነት ቦታዎች ላይ የነበርኩ ቢሆንም፣ እራሴን እንደ ባይተዋር እንደመለከት ጫና ይደርስብኝ ነበር። እርግጥ ህወሓት በሚያደርጋቸው ጥልቅ ተሃድሶዎች ለውጥ ያመጣ ይሆናል የሚል ተስፋ ነበረኝ። በሂደት ግን፣ ህወሓት በውስጥም ሆነ በውጪ የሚነሱ የዲሞክራሲ ጥያቄዎችን የመመለስ ቁርጠኛ አቋም እንደሌለው ተገንዝቢያለሁ። ህወሓት በቅርቡ ያደረገው ጥልቅ ተሃድሶ ህዝብን ለመጥቀም፣ አሊያም፣ እውነተኛ ዲሞክራሲ ለማምጣት አልነበረም፤ ዲሞክራሲያዊነት የድርጅቱ ባህሪ አይደለም።

በኢህአዴግ አባል ድርጅቶች ውስጥ የሚደረጉ ተሃድሶዎች ዋነኛ ዓላማም ቢሆን፣ ለህወሓት ተፎካካሪ የሆኑ እህት ድርጅቶች እንዳይፈጠሩ መከላከል ነበር። ይፈለግ የነበረው ጠንካራ ህወሓት እንጂ፣ ጠንካራ ኢህአዴግ አልነበረም።

**ኢትዮጲስ፡- በህወሓት አመራሮች መካከል ያለውን የስልጣን ሽኩቻ እንዴት ይገለፃል?**

**ዛዲግ፡-** ድርጅቱ ከተመሰረተበት ጊዜ አንስቶ፣ የህወሓት አመራሮች ለስልጣን ሲሻኮቱና ሲፋተጉ የኖሩ ናቸው። ለዚህም ማሳያው ደግሞ፣ በ1968 ዓ.ም የነበራቸው ክፍፍል ነው። በወቅቱ "ከአድዋ፣ ሽሬና አክሱም የመጣ ኃይል የህወሓትን ስልጣን ተቆጣጥሮታል" በሚል፣ ከመቐለ እንደርታ አካባቢ የነበሩ ሰዎች ቅሬታ አንስተው ነበር። በድርጅቱ ውስጥ ስልጣንን በቡድን፣ በጎጥና በሞኖፖል የመያዝ ባህል አለ፤ በጣም ውስብስብ ነው። በህወሓት ውስጥ ስልጣን በስስትም በጉጉትም ትጠበቃለች፤ ከ1968 ጀምሮ የተተከለ መጥፎ ባህል ነው።

በ1978 እና 1979 ዓ.ም በህወሓት ውስጥ ሌላ የስልጣን ትንቅንቅ ተፈጥሮ ነበር። በወቅቱ ህወሓትን ሲመሩ የነበሩት እነ አረጋዊ በርሄና ግዳይ የመሳሰሉት፣ በአዳዲሶቹ፣ ማለትም በእነ መለስ ዜናዊ፣ ለመተካት እሰጣገባ ተነስቷል። በዚህ ወቀት የነበረው የህወሓት ሪፎርምም፣ ድርጅቱንም ሆነ ሀገርን የማደስ ሳይሆን፣ የራስን ጥቅምንና ፍላጎት የማስጠበቅ ነበር። ተከሰቱ የተባሉት የመስመር ልዩነቶች ጥልቀት አልነበራቸውም፤ ለስልጣን ሽኩቻው ፖለቲካዊ ሽፋን ለመስጠት የተፈጠሩ ሰበቦች ነበሩ፤ ዋናው ምክንያት ስልጣን ነበር፤ በዚህ ትንቅንቅ እነ መለስ አሸነፈው፣ በሂደት በስልጣናቸው ላይ አደጋ ያሉትን ሁሉ እየበሉ ይኸው እስከዛሬ ዘልቀዋል።

ይህም ሆኖ ግን፣ ድርጅቱ በ1983 ስልጣን ከመያዙ በፊት ህወሓት የጋራ የሆነ ሃሳብ፣ አመለካከለት፣ ፍላጎትና ዓላማ ነበረው ማለት ይቻላል። ነገር ግን፣ ወደ ስልጣን ከወጡ ቦኋላ፣ በአመራሮቹ ዘንድ የነበረው የጋራ ፍላጎት ከስሞ የግል ጥቅሞቻቸው አይለው ወጥተዋል። ከዚያ በኋላ ድርጅቱ በቁልቁለት መንገድ ላይ ነበር ማለት ይቻላል።

ህወሓት ባደረጋቸው ተሃድሶዎች ችግሮችን የሚቀርፍ ለውጥ ማምጣት አልቻለም። ህወሓት የሚያነሳቸው "ዲሞክራሲን አመጣለሁ" የሚሉ ፉከራዎች፣ የአንድ ወቅት ጮኸት ይሆኑና ተግባራዊ ሳይደረጉ ይቀራሉ። በ1993 ዓ.ም ህወሓት ዲሞክራሲን ለማስፈን በአንፃራዊነት የተሻለ ተሃድሶ ያደረገ ቢሆንም፣ በ1997 ዓ.ም በተደረገው ምርጫ ስልጣኑን ለማጣት የተቃረበ በመሆኑ፣ እውነተኛው ባህሪው ወጥቶ፣ ሰዎችን በግላጭ ለማፈንና ለመጨቆን ተገድዷል፤ ሁሌም ቢሆን የህወሓት አመራሮች ከስልጣን በላይ የሚያስቀድሙት ነገር የላቸውም፤ ዋናው ጉዳያቸው እዚያ ላይ የተንጠለጠለ ነው።

የህወሓት አመራሮች ስልጣኑን የያዙት ከደርግ ጋር ተዋግተው የብዙ ሰዎችን ህይወት መሰዋዕት በማድረግ ስለነበር፣ በክልልም ሆነ በፌድራል ደረጃ፣ "ስልጣን ይገባኛል" የሚል እሳቤ አላቸው። ይህንንም ስልጣን ለማስጠበቅ ማንኛውንም ዓይነት ዋጋ ከመክፈል ወደኋላ አይሉም፤ ለዚህ ነው አሁን ያለውን ሀገራዊ ለውጥ ከመቀሌ ሆነው እየተቃወሙ የሚገኙት።

ዲሞክራሲ ስልጣንን ለመልቀቅ፣ ስልጣንን ለማጋራት እንዲሁም ከኃላፊነትም ለመውረድ ዝግጁ መሆንን ይጠይቃል። የህወሓት አመራ ግን ለዚህ ዝግጁ አይደለም፤ ምርጫን የሚቀበለው ስልጣኑን ካስጠበቀለት ብቻ ነው፤ ለእሱ ምርጫ ማስመሰያ ነው።

ህወሓት ከስልጣን ከወረደ በኋላ በሀገሪቱ የተደረጉ ለውጦች፣ ከዚህ ቀደም ከተደረጉ ለውጦች የተለዩና የተሻሉ ናቸው። ለዚህ ቀላል ማሳያ የሚሆኑት ደግሞ፣ በተለያዩ ምክንያቶች የታሰሩና የታፈኑ እስረኞች መለቀቃቸውና የመደራጀት መብት መከበሩ ተጠቃሽ ናቸው። በእርግጥ የዚህም ለውጥ እውነተኝነት ከምርጫው በኋላ የሚረጋገጥ ይሆናል።

በጥቅሉ ግን፣ ህወሓት በስልጣን ላይ በነበረ ጊዜ ሀገሪቱን ይቅርና ድርጅቱን ዲሞክራሲያዊ ሊያደርግ አልቻለም። ሌላው ቀርቶ፣ የድርጅቱ አባላት ሃሳባቸውን እስከአሁን ድረስ በነፃነት እንዲገልፁ አይፈቅድም። ባነሱት ሃሳብ ምክንያት "ከሃዲ" እየተባሉ ይፈረጃሉ፣ ከህብረተሰቡ ይገለላሉ። ከጥላቻው የተነሳ ታሪክ ለመሰረዝም ይሞክራል። የእነ አረጋዊ በርሄ፣ ግዳይና ስዬ አብርሃ ፎቶዎች ከድርጅቱ ታሪክ ውስጥ ተነቅለው እንዲወጡ ትዕዛዝ ተሰጥቶ የነበረበት አጋጣሚ ስለነበር፣ ፎቶአቸው ከፎቶ አውዶች እንዲነሱ ተደርገዋል። በህወሓት ውስጥ የተለየ ሃሳብን የሚያመጣ ሰው፣ ከህወሓት ታሪክ ውስጥ በላጲስ እንዲጠፋ እና ታሪኩ እንዲደበዝዝ ይፈለጋል። በአጠቃላይ በህወሓት ውስጥ የሃሳብ ልዩነት ቦታ የለውም። ስለዚህ፣ ህወሓት እንደ አዲስ የዲሞክራሲ አብዮት ያስፈልገዋል።

> "
> **ከህወሓት አባልነት መልቀቄ የሀገሬን ህዝብ ከማገልገል አያግደኝም፡፡ ከህወሓት አባልነት መልቀቄን በአደባባይ ስናገር፣ ህዝብ ከፍተኛ የሆነ ድጋፍ አድርጎልኛል**

**ኢትዮጲስ፡- በቀጣይ ህወሓት ምን ሊያደርግ ይችላል ብለው ያስባሉ?**

**ዛዲግ፡-** ህወሓት ዓላማ አሁንም ቢሆን የተነጠቀውን ስልጣን ማስመለስ ነው። ለዚህም ደግሞ ማድርግ ያለበትን ነገር ሁሉ ከማድረግ ወደኋላ አይልም። ህወሓት፣ አሁን በሀገሪቱ ውስጥ የተፈጠረውን ለውጥ እንደሌሎቹ የኢህአዴግ ድርጅቶች አሜን ብሎ የሚቀበል ድርጅት አይደለም። "በቀጣይ፣ የነበሩኝን ችግሮች አስተካክዬ ተወዳድሬና በምርጫ አሸንፌ፣ ስልጣንን እይዛለሁ" የሚል አመለካከት የለውም።

የህወሓት አመራሮች ስልጣንን ህዝብን አቀራኝተው አይመለከቷቸውም። ይህ ማለት፣ ስልጣንን የሚሹት ህዝብን ለማገልገል ሳይሆን፣ እራሳቸውን ለመጥቀም ነው። ድርጅቱን አሁን ያለበት አሳዛን ሁኔታ በዚህ የአመራር ንቅዘት የሚገለፅ ነው። የህወሓት አመራሮች ስልጣናቸውን እንደ ግል ስኬታቸው ነው የሚቆጥሩት፤ ስልጣናቸውን ሲቀሙ በግል እንደተሸነፉ ነው የሚመለከቱት፤ በሌላ ቦታ ስኬትና ህይወት ያለ አይመስላቸውም፤ ስልጣን አልፈና ኦሜጋቸው ነው፤ የሁሉ ነገር መጀመሪያና መጨረሻ።

በእርግጥ ህወሓት ውስጥ በዲሞክራሲ የሚያምኑ ጥቂት ሰዎች እንዳሉ አውቃለሁ። ነገር ግን፣ ዋናውን ስልጣን የያዙት የህወሓት አመራሮችም ሆኑ ከበስተጀርባ ሆነው አመራሮችን የሚደግፉ አካላት፣ በእውነተኛ ዲሞክራሲ የሚያምኑ አይደሉም። ቢቻለው፣ አሁን ያለው ለውጥ ብዙ እንዳይራመድ በህወሓት በኩል የማይፈነቀል ድንጋይ አይኖርም። ሆኖም ግን፣ ብዙሃኑ የኢትዮጵያ ህዝብ አሁን ያለውን ለውጥ እንደሚደግፍ በግልፅ ተረድቶታል፤ በዚህ ሁኔታም ምንም ዓይነት ነገር መፍጠር እንደማይችል አምኗል። ነገር ግን፣ በሆነ ወቅት ላይ ያልተጠበቀ ፈንጅ ማፈንዳቱ እንደማይቀር ይሰማኛል።

አሁን ባለው ሁኔታ፣ ህወሓት በኢትዮጵያ ህዝብ ብቻ ሳይሆን፣ በትግራይም ሳይቀር ተቃውሞ እየገጠመው ይገኛል፤ ተቃውሞው ፊት ለፊት የማይታይ ቢሆንም፣ ውስጥ ውስጡን ግን እየተንተከተከ ነው። የህወሓት ማብቂያ እዛው (ትግራይ) እንደሆነ ይሰማኛል። ከትግራይ ህዝብ ቀጣይነት ያለው ድጋፍ የማግኘት እድሉ እየጠበበ ነው።

በጥቅሉ ህወሓት ሁለት አማራጮች ብቻ ነው ያሉት። የመጀመሪያ ምርጫው፣ በሀገሪቱ የተፈጠረውን ለውጥ አምኖ መቀበልና መደገፍ ነው። ካልሆነ ደግሞ፣ ሌላው አማራጭ አሁን እየሄደ ባለው መንገድ ቀጥሎ፣ ለውጡን እየተቃወመ ሀገርንም ሆነ የትግራይን ህዝብ ለእልቂት እንዲዳረጉ መጣር ነው፤ ይህ የአጥፍቶ መጥፋት መንገድ ነው።

የትግራይ ህዝብ ይህንን የጥፋት መንገድ አስቀድሞ በመገንዘብና ኃላፊነት በመውሰድ፣ በፍጥነት የለውጥ ፕሮግራሞችን በመንደፍ፣ ድርጅቱንም ሆነ የትግራይን ህዝብ የዘመናዊ ዲሞክራሲ ባለቤት ሊያደርግ ይገባል። ለትግራይ ህዝብ የሚያወጣው ከቀሪዎቹ ኢትዮጵያዊያን እህቶቹና ወንድሞቹ ጋር እኩል መራመድ ነው፤ ወደፊት እንጂ ወደኋላ በመቀኘት ምንም የሚገኝ ነገር የለም።

**ኢትዮጲስ፡- የእርሰዎን መልቀቅ ተከትሎ አንዳንድ የህወሓት አመራሮች የትችት ሃሳቦችን ይሰነዝራሉ፡፡ ከእነዚህም መካከል፣ በአሁኑ ሰዓት በህወሓት ከፍተኛ የአመራር ኃላፊነት ላይ የሚገኙት አቶ ጌታቸው ረዳ ናቸው፡፡ አቶ ጌታቸው ስለ እርሰዎ ሲናገሩ፣ "ዛዲግ በህወሓት አባልነቱ ወቅት ያለው ሚና እምብዛም ነበር" የሚል ትችት ሰንዝረዋል፡፡ ለዚህ ምን ምላሽ አለዎት?**

**ዛዲግ፡-** እንደሚታወቀው፣ ህወሓ አባላቶቹ ሲወጡበት የማራከስና የማጥላላት ልማድ አለው፤ በእኔም ላይ የተፈጠፀመውም ተመሳሳይ ድርጊት ነው። ቅድም እንዳልኩት፣ የድርጅቱ መስራች የነበሩትን እንኳን ዓይኑን ሳያሽ ከታሪክ መዛግብት ለመሰረዝ ሞክሯል። የድርጅቱ መስራቾችን በተመለከተ፣ የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስተር አቶ መለስ ዜናዊ፣ "እነሱ ቆሻሻን አራግፎ እንደመጣል ናቸው" ብለው ገልፀዋቸው ነበር። ስለዚህ፣ አሁን ላይ ያሉ የህወሓት አመራሮች እኔን ቢያጥላሉ የሚገርም ወይንም የሚደንቅ ነገር አይደለም።

እኔ የህወሓት አባል በነበርኩበት ወቅት በሚኒስተርነት አገልግያለሁ። በህወሓት ውስጥ ከነበሩት ተፅዕኖ ፈጣሪና አንጋፋ አምስት ሚኒስትሮች መካከል አንዱ ነበርኩ። በነበረኝ የሚኒስትርነት ሹመት በርካታ ተፅዕኖዎችን በመፍጠር ድርጅቱን አገልግያለሁ። ዛሬ ላይ ሆኜ፣ በህወሓት ውስጥ በነበረኝ የኃላፊነት ዘመን፣ ተፅዕኖ ፈጣሪ ነበርኩ? ወይንስ አልነበርኩም? ብዬ እራሴን መጠየቅ አልፈልግም። ምክንያቱም፣ ድርጅቱ በስልጣን ላይ ለዓመታት ሲያስቀምጠኝ፣ ለቦታው እንደምመጥን አምኖብኝ ነው። ከዚህ ባለፈ የድርጅቱ አባላትም ሆነ የትግራይ ህዝብ ተፅዕኖ ፈጣሪነቴን ይመሰክሩልኛል።

የህወሓት አባልነቴን ለቅቄ ስወጣ፣ ዋንኛ ምክንያቴ የነበረው የህወሓት መርህን መጣስ ነው። ከዚህ ባለፈ፣ ከህወሓት ለመውጣት ምክንያት የሆነኝ፣ በራያ ውስጥ ያለው የማንነት ጥያቄ ነው። የህወሓት አመራሮች የራያ ህዝብ የማንነትን ጥያቄ በትኩረት ሊመልሱለት ሲገባ፣ ሲያጣጥሉትና በንቀት እንደሚመለከቱት ለማየት ችያለሁ፤ ይህ በግልፅ የህዝብ መብት ረገጣ ነው።

የራያ ህዝብ የማንነት ጥያቄ፣ የህወሓት ባለስልጣናት በሸራተን አሊያም በሌላ ዝነኛ ሆቴል እየተዝናኑ የሚመልሱት ጥያቄ አይደለም። ራያ መሆን በቅንጡ ሆቴሎች በሚደረግ መዝናናት የሚገኝ አይደለም። ለዚህ የማንነት ጥያቄ ብዙ ሽህ ሰዎች ሞተውበታል፣ ብዙዎቹ ቆስለውበታል። በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎችም ከለመዱት ቀዬያቸው ተፈናቅለዋል። ይህ በሆነበት ሁኔታ፣ እነዚህንና ሌሎች መሰል የመብት ጥያቄዎች በአግባቡ አለመመለሳቸው ከህወሓት አባልነት እንድለቅ ምክንያት ሆነውኛል። ህወሓትም ቢሆን፣ የእኔን ከድርጅት አባልነት መልቀቅ ከሚያጥላላ ይልቅ፣ የራያን ህዝብ የማንነት ጥያቄ ቢመልስ የተሻለ ነው።

ከህወሓት አባልነት መልቀቄ የሀገሬን ህዝብ ከማገልገል አያግደኝም። ከህወሓት አባልነት መልቀቄን በአደባባይ ስናገር፣ ህዝብ ከፍተኛ የሆነ ድጋፍ አድርጎልኛል። ኢትዮጵያ ዲሞክራሲ የሰፈነባት ሀገር እንድትሆን የሚፈልጉ በርካታ ሰዎች፣ በቀጥጣም ሆነ በተዘዋዋሪ ድጋፋቸውን ችረውኛል። ያሳለፍኩት ውሳኔ ትክክለኛ እንደነበር በተለያዩ አጋጣሚዎች ገልፀውልኛል። በቀጣይም፣ በሀገሬ ፖለቲካ ላይ በመሳተፍ፣ ከሌሎች ኢትዮጵያዊያን ወገኖቼ ጋር የሀገሬን እድገት እውን ለማድረግ እሰራለሁ። ይህንን እውን ለማድረግ እስከ ህይወት መስዋዕትነት ለመክፈል ዝግጁ ነኝ። ሀገር ቤት ስመለስ አብሬው የምሰራው የፖለቲካ ድርጅት አለ። ለጊዜው ግን፣ ይህንን የፖለቲካ ፓርቲ ይፉ ለማድረግ አልፈልግም። በቅርቡ ወደ ኢትዮጵያ ስመለስ፣ የፓርቲውን ማንነትና የእኔንም የፖለቲካ አቋም ለኢትዮጵያ ህዝብ ይፉ የማድርግ ይሆናል።

(ይቀጥላል)...



ጀምበር አብዱ
ጠበቃና የህግ አማካሪ

## ለቅፅበታዊ ግጭት የሽብርተኝነት ክስ

# "ዳኞቻችን ፣ በሥልጣን ላይ ያለው አካል ምን ይፈልግ ይሆን? ብለው ይጨነቃሉ”

የኦነግ አመራሮች ወደ ሀገር ቤት ሲገቡ በአዲስ አበባና በዙሪያዋ ባሉ ወጣቶች መካከል በተፈጠረ ግጭት በሰው ህይወትና በንብረት ላይ ጉዳት ደርሷል:: በዚህም ሳቢያ፣ እስከ 1200 የሚደርሱ ሰዎች በአዲስ አበባ ለእስር ተዳፍገዋል:: ከእነዚህ መካከል አብዛኞቹ የተለቀቁ ሲሆን፣ አንዳንዶቹ ደግሞ ክስ ተመስርቶባቸው በእስር ላይ ይገኛሉ:: ከእነሱ መካከል የተወሰኑትን በጥብቅና ቆሜ ጉዳያቸውን እየተከታተልኩ እገኛለሁ::

እነዚህ ልጆች (ደንበኞቼ) በአዲስ አበባ በተለምዶ አስኮ በምንለው ኮልፌ ቀራኒዮ ወረዳ 15 የሚኖሩ ልጆች ናቸው:: ፖሊስ በቁጥጥር ስር ባዋላቸው ሰዓት፣ “ፈፅመውታል” የተባለው ወንጀል ምን እንደሆነ መርማሪ ፖሊስ የነገራቸው ነገር የለም:: በዚህም፣ መሰረታዊ የሆነ የህገ መንግስት መርህ ተጥሷል:: አንድ ተጠርጣሪ በቁጥጥር ስር ሲውል፣ ምን መብት አለው? ለሚለው ጥያቄ በግልፅ የተቀመጡ መብቶች አሉት፤ በህገ መንግስቱ አንቀፅ 19 ተዘርዝረዋል::

ደንበኞቼ በወንጀል ተጠርጥረው በቁጥጥር ስር ከዋሉ በኋላ፣ የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አራዳ ምድብ ሁለተኛ ወንጀል ችሎት ነበር የቀረቡት:: 14 የምርመራ ቀናት ለሁለት ጊዜ እየተጠየቀባቸው ለ2 ወር ታስረው ሲከራከሩ ቆይተዋል:: የወንጀለኛ መቅጫ ህግ፣ አንቀፅ 59 ንዑስ አንቀፅ 3 ላይ፣ አንድ ሰው በምርመራ ሂደት ተጨማሪ ምርመራ ሲደረግበት ዋስትና ተከልክሎ 14 ቀን ሊጠየቅበት ይችላል ይላል:: ነገር ግን፣ 14 ቀን ስንት ጊዜ ይጠየቅበታል የሚለውን ነገር ህጉ በዝምታ አልፎታል:: የሽብር አዋጅ ጋር ስንሄድ ግን፣ 28 ቀን እንደሚፈቀድ ይገልፅና፣ ጠቅላላ የሚጠየቁ ጊዜት ከ4 ወር ማለፍ የለበትም ብሎ ገድቦታል:: እንደዚህ አይነት ገደብ በወንጀለኛ መቅጫው የለም:: በዚህ ክፍተት ነው ልጆቹ (ደንበኞቼ)ሰለባ የሆኑት::

ፍርድ ቤቶች ተደጋጋሚ 14 ቀን ሲፈቅዱ የመርማሪውን ትጋት ማየት ነበረባቸው:: ዓቃቤ ህግ ምን ያክል ተግቶ እየሰራ ነው? በዚህ 14 ቀን ውስጥ ምን ሰርቷል?፣ ምንስ ይቀረዋል? የሚለውን መገምገም ይኖርባቸዋል:: ለዓቃቤ ህግ 14 ቀን ተሰጥቶት አንድ ደብዳቤ ብቻ ከመንግስት ተቋም ቢያመጣ፣ የተሰጠውን 14 ቀን አልተጠቀማትም ማለት ነው:: ስለዚህ ፍርድ ቤቱ ቀጣይ በሚጠይቅበት ጊዜ ይሄን ማሰብን ከግምት ውስጥ ማስገባት አለበት:: ለሁለት ወር እነዚህን ልጆች አስረው አቆይተዋል:: ትልቅ ህገ መንግስታዊ ጥሰት ተፈፅሟል:: ሁለት ወር ሙሉ በአራዳ ፍርድ ቤት ሲከራከሩ ከቆዩ በኋላ፣ የሚያቀርቡትና የሚከራከሩበት ጉዳይ ስለማያዋጣና መዝገቡ ሊዘጋ ሲቃረብ ወደ ፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ አራተኛ ወንጀል ችሎት በሽብርተኝነት አቀረቧቸው::

የልደታ ፍርድ ቤት፣ ከአራዳ ፍርድ ቤት ያለአግባብ የመጣ ክስ ስለሆነ፣ መዝገቡን መዝጋት ሲኖርበት፣ ሳያደርግ ቀርቷል:: ይህንን ከማድረግ ይልቅ ግን፣ ጉዳዩን እንደ አዲስ በመመልከት፣ ተጨማሪ የ28 ቀናት ቀጠሮ በመስጠት ደንበኞቼን እንዲጉላሉ አድርጓቸዋል:: ፍርድ ቤቱ የ28 ቀን ቀጠሮ ሦስት ጊዜ ፈቅዷል:: ይህም ሆኖ ግን፣ ለሦስት ጊዜ ከተሰጡት የ28 ቀናት ቀጠሮ በኋላ፣ ፍ/ቤቱ የሰጠው ትዕዛዝ፣ “ክሱ በወጣቶቹ ላይ ሽብርን የሚያቋቁም አይደለም” በማለት ሥነ ስርዓቱን በጣሰ መልኩ የክስ መዝገቡን መዝጋት ሲኖርበት፣ “የእኔ ሥልጣን ስላልሆነ ሦስተኛ ወንጀል ችሎት ላይ ይታይ” የሚል ትዕዛዝ ሰጥቷል::

### በምን መስፈርት ሽብርተኝነት?

ደንበኞቼ ላይ የሽብር ክስ መመስረት እንደሌለበት ፍ/ቤቱ እራሱ ያመነው ጉዳይ ነው:: አንድ ግለሰብ በሽብር ወንጀል ሲጠረጠር ብዙ ነገሮች ከግምት ውስጥ ይገባሉ:: ሽብርተኝነት በራሱ ረቂቅ ጉዳይ ነው:: አንድን ግለሰብ ሽብርተኛ ለማለት ዓለም አቀፋዊ መስፈርቶች መሟላት አለባቸው:: ሽብርተኛ ለማለት መሟላት ካለባቸው ነገሮች መካከል ዝግጅት ያስፈልጋል፣ ምልመላ፣ አባልነት፣ ትጥቅ ይፈልጋል:: ደንበኞቼ ግን፣ ከእነዚህ ከተዘረዘሩት መካከል አንዱንም አልፈፀሙም:: የተያዙትም፣ በየቤታቸው ሆነው ሸመና ሲሰሩና በተለያዩ ቦታዎች ላይ ሆነው በስራ ገበታቸው ላይ እያሉ ነው:: የተመሰረተባቸው ክስ በራሱ፣ ቅፅበታዊ ግጭት እንጂ፣ ሽብርተኛ እንዳልሆኑ ያመለክታል:: በክሱ ላይ የተቀመጠው ዝርዝር ነገር፣ በወቅቱ የኦነግ አመራሮች ስለሚመጡ፣ አቀባበል የሚያደርጉላቸው ደጋፊ ወጣቶች ወደ አዲስ አበባ ለመግባት፣ የኦነግን አርማ ለመስቀል፣ አስፓልት ላይ ቀለም ለመቀባት ባደረጉት እንቅስቃሴ የተፈጠረ ግጭት እንጂ፣ የሽብር ወንጀል በግልፅ ተቀምጧል:: ወጣቶቹ ከኦነግ ደጋፊዎች ጋር የተጋጩት፣ ቀደም ብሎ ብራዩ ላይ የተፈጠረውን የዘር ጥቃት በማስታወስ፣ እራስን ለመከላከል በማሰብ ነው::

ይሁንና፣ መርማሪዎቹ ደንበኞቼን በአራዳ ምድብ ሁለተኛ የወንጀል ችሎት ለሁለት ወር እንዲቆዩ

> የምርመራውም ሆነ የክስ ሂደቱ፣ ከአራዳ ምድብ ችሎት አንስቶ እስከ ልደታ ምድብ ችሎት የነበረው ሂደት ስነ ስርዓቱንም ሆነ ህጉን የተከተለ አልነበረም



ሲያደርጉ፣ የህግ እውቀት ስለሌላቸው ሳይሆን፣ ሆን ብለው ለማንገላታት በማሰብ እንደሆነ ይገባኛል:: ከዚህ ባለፈ፣ በደንበኞቼ ላይ ሲሰጡ የነበሩ ቀጠሮዎች እርዝማኔ የህግ አግባብነት የሌለው ነው:: ምክንያቱም የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት አንቀፅ 109 የሚለው፣ “ምርመራ ተጠናቆ ሲቀርብ፣ ዐቃቤ ህግ በአካል ፍ/ቤት በመቅረብ “መዝገብ ደርሶኛል፣ ክስ ላዘጋጅ ስለሆነ፣ የክስ ማቅረቢያ ጊዜ ይሰጠኝ” ማለት እንዳለበት ያብራራል::

በእኛ ጉዳይ ላይ ግን ዐቃቤ ህግ አልቀረበም:: ዐቃቤ ህግ በሌለበት ግን፣ ፍ/ቤቱ ክስ ማቅረቢያ ብሎ የ15 ቀናት ቀጠሮ ሰጥቷል:: ይሄ ተግባር ደግሞ፣ በግልፅ ሥነ ሥርዓቱን የጣሰ ነው:: ይህ የሚያሳየው ፍርድ ቤቱ በዐቃቤ ህግ ያልተጠየቀን ዳኝነት እንደሰጠ ነው:: በሥነ ሥርዓት አንቀፅ 109 ላይ ለምርመራ ጊዜ የሚሰጠው ከፍተኛውና የመጨረሻው 15 ቀን ብቻ ነው:: ፍርድ ቤቱ ግን፣ ይህንን ወደ ጎን በመተው ተጨማሪ የ10 ቀን ቀጠሮ ሰጥቷል:: መርማሪ ፖሊስም ሆነ ዐቃቤ ህግ ደንበኞቼ በቀጠሮ እንዲጉላሉ ያደረጉት የህግ እውቀት ስላነሳቸው ሳይሆን በእኩል የመዳኘት መብታቸውን ለመጋፋት በማሰብ ነው::

### በክስ ሂደቱ ላይ የነበሩ ክፍተቶች

ታህሳስ 11 ቀን 2011 ዓ.ም ወጪ የተደረገ ክስ ቀርቦልናል:: ይህ ክስ የቀረበው በፌደራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ልደታ ምድብ ሦስተኛ ወንጀል ችሎት ነው:: ክሱ በችሎት ከደረሰን በኋላ ስንመለከተው፣ የወንጀል ህግ አንቀፅ 240 ንዑስ አንቀፅ 3 የሚያጣቅስ ነው:: የወንጀለኛ መቅጫ ህጉ ባስቀመጠው ድንጋጌ፣ ዋስትና ተከልክሎ ክርክር የሚደረግበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል:: ዋስትና ተፈቅዶለት የሚታይበትም ሂደትም ይኖራል:: የወንጀል ህግ አንቀፅ 240 ንዑስ አንቀፅ 3 ከባድ ስለሆነ የዋስትና መብትን የሚከለክል ነው::

ይህንን ክስ በተመለከተ ለፍ/ቤቱ መቃወሚያችንን አቅርበን ነበር:: በመቃወሚያችን፣ ደንበኞቼ ከላይ በተጠቀሰው አንቀፅ እንዲከሰሱ የሚያደርግ ምንም ዓይነት ወንጀልም ሆነ አግባብ እንደሌለ አስረድተናል:: በዚህ አንቀፅ ደንበኞቼን ለመክሰስ መሟላት ያለባቸው በርካታ ነጥቦች አሉ:: ዐቃቤ ህግ ግን፣ ደንበኞቼን በዚህ አንቀፅ ለመክሰስ የሚያስችለው ምንም ዓይነት ማስረጃ የለውም:: በወቅቱ በወጣቶቹ መካከል የተፈጠረው ግጭት፣ “የኦነግን አርማ አትሰቅሉም፣ ቀለምም አትቀቡም” በሚል ነበር:: በዚህ አንቀፅ ግን፣ (240 ንዑስ አንቀፅ 3) ህዝብ ላይ ጦርነት ማነሳሳት ወይንም መንግስት ላይ ጦርነት ማነሳሳትን የሚጠቅስ ነው::

ለፍ/ቤቱ ባቀረብነው መቃወሚያ፣ ኦነግ አንድ ድርጅት እንጂ መንግስት እንዳልሆነ አስረድተን፣ የአንቀፁ ድንጋጌም በእኛ ላይ ተፈፃሚ መሆን እንደሌለበት ገልፀናል:: ፍርድ ቤቱም የእኛን የክስ መቃወሚያ ከተቀበለ በኋላ፣ ዐቃቤ ህግ በክሱ ያስቀመጠው አንቀፅና የወጣቶቹ ወንጀል ስላልተጣጣመ ክሱን እንዲያሻሽል ትዕዛዝ በማስተላለፍ የ10 ቀን ቀጠሮ ሰጥቶ ነበር:: በተሰጠው ቀጠሮ ተመልሰን ስንገናኝ ግን፣ ዐቃቤ ህግ ፍርድ ቤቱን እንዲያሻሽል የሰጠውን ትዕዛዝ ሳይፈፅም ቀርቷል::

ከዚህ በኋላ ፍትህ የማግኘት መብታችንን በግልፅ ተነፍገናል:: ምክንያቱም፣ የተሻሻለ ክስ ካልቀረበ፣ ክስ እንደሌለ ተቆጥሮ ተጠርጣሪዎቹ ዋስትና ማቅረብ ሳይጠበቅባቸው በነፃ መለቀቅ ነበረባቸው:: ለፍ/ቤቱ ይህንን መከራከሪያ ስናቀርብ፣ ፍ/ቤቱ የሰጠን ምላሽ ግን፣ “ዐቃቤ ህግ የተሰጠውን ትዕዛዝ ተቀብሎ ክሱን አሻሽሏል ኣላሻሻለም የሚለውን ለመለየት ጊዜ ያስፈልገናል” ብሎ የ7 ቀን ቀጠሮ ሰጥቶ ነበር:: ከ7 ቀን ቀጠሮ በኋላ፣ የካቲት 11 ቀን 2011 ዓ.ም፣ ዐቃቤ ህግ የክስ ማሻሻያ ሳያደርግ ቀርቷል:: ነገር ግን፣ ፍርድ ቤቱ ተጠርጣሪዎቹ ዋስትና ሳያቀርቡ በነፃ እንዲሰናበቱ አላደረገም:: ይልቁንም ፍ/ቤቱ ያስተላለፈው ትዕዛዝ፣ “ይህንን ጉዳይ በተገቢው ሁኔታ ለመከታተል እኛ ስልጣን ስለሌለን፣ ወደ አራተኛ ወንጀል ችልት ይዘዋወር” በማለት የ3 ቀን ቀጠሮ ሰጥቷል:: ባለው የህግ አግባብ መሰረት ጉዳያችን ከሦስተኛ የወንጀል ችሎት ወደ አራተኛ የወንጀል ችሎት የሚዘዋወርበት አግባብ የለም:: በዚህ ፍትህን ተነፍገናል::

### የፍርድ ሂደቱ ገለልተኝነት

የፍርድ ሂደቱ ገለልተኛ ነው ለማለት በጣም ያስቸግራል:: ተጠርጣሪዎቹን በነፃ የሚሰናበቱበት ሁኔታ በግልፅ ተፈጥሮ ተግባራዊ ሳይሆን ቀርቷል፤ ይህ ደግሞ፣ በግልፅ ህግን መተላለፍ ነው:: የምርመራውም ሆነ የክስ ሂደቱ፣ ከአራዳ ምድብ ችሎት አንስቶ እስከ ልደታ ምድብ ችሎት የነበረው ሂደት ስነ ስርዓቱንም ሆነ ህጉን የተከተለ አልነበረም:: ይህ ማለት ደግሞ፣ ደንበኞቼ በኩል አልተዳኙም፣ ወይንም ደግሞ፣ በእኩል የመዳኘት መብታቸው ተነፍጓል ማለት ነው:: እንደዚህ ዓይነቱ ነገር መፈጠሩ፣ እኔን ጨምሮ ሌሎች የሙያው አጋሮቼ ህግን መሰረት ያደረገ የማማከር አገልግሎት ለመስጠት ችግር ፈጥሮብናል:: በፍትህ ሥርዓታችን ላይ አሁን ሥልጣን ላይ ያለው አካል በቀጥታ ተፅዕኖ ያሳድራል የሚል እምነት የለኝም:: ነገር ግን፣ ዳኞቻችን “በሥልጣን ላይ ያለው አካል ምን ይፈልግ ይሆን?” ብለው የሚጨነቁ ይመስለኛል::



## የተከሰከሰው አውሮፕላን ጉዳይ በህግ በለሙያው እይታ

# “ቦይንግ በፍርድ ቤት ሙሉ ኃላፊነት እንዲወስድ መደረግ አለበት”

## ዶክተር ሼክስፒር ፈይሳ

### በሲያትል፣ አሜሪካ፣ የሕግ አማካሪና ጠበቃ

**ዶክተር ሼክስፒር ፈይሳ የህግ ባለሙያና በአሜሪካን ውስጥ በጥብቅና ሥራ ከ17 ዓመታት በላይ የሠሩ ኢትዮጲያዊ ናቸው፣ በልጅነት ዕድሜያቸው ወደ ኬኒያ ተጉዘው፣ በዚያው ወደ አሜሪካ እንዳመሩ ይናገራሉ፣ በሲያትል ፓሲፊክ ዩኒቨርሲቲ እና በሴንትራል ዋሽንግተን ዩኒቨርስቲ በዋናነት በፓለቲካል ሳይንስና ሶሻል ሳይንስ፣ እንዲሁም፣ የታሪክ ትምህርትን ማይነር በማድረግ ተምረዋል፡፡ ከዚያም ወደ ህግ ትምህርት ቤት በመሄድ በ2002 ዓም የህግ ዲግሪያቸውን አገኙ፣ ኑሮዋቸውን እዚያው አሜሪካ ሲያትል በማድረግም፣ በጥብቅና ሥራ ላይ ተሰማርተው ለ17 ዓመታት ይህንኑ ሥራ ሲሠሩ ቆይተዋል፣ ትልልቅ የፍታብሄር፣ የወንጀልና፣ በተለይም ከሰብዓዊ መብቶች ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን በመያዝ ውጤታማ መሆናቸውን ብዙዎች ይመሰክሩላቸዋል፡፡**

**በብዙ ኢትዮጲያዊያን ከሚታወሱበት ጉዳይ አንዱ፣ በአቶ መለስ ዜናዊና በባለስልጣኖቻቸው አማካኝነት በትንሳኤ ሬዲዮ ላይ የቀረበውን ክስና የተጠየቀውን ከፍተኛ ካሳ ውድቅ ያደረጉበት ሂደት ነው። በአሁኑ ጊዜ አዲስ አበባ የሚገኙትን ዶክተር ሼክስፒር ፈይሳን፣ በቅርቡ ከተከሰከሰው ቦይንግ 737 ማክስ 8 አውሮፕላን ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ከህግ አንፃር እንዴት እንደሚታዩ ጠይቀናቸዋል፡፡**

**ኢትዮጲስ፣- በቅድሚያ ስለ ጥብቅና ሥራዎት አጀማመርና በዘርፉ ስላለዎት ልምድ ቢነግሩን?**

**ዶ/ር ሼክስፒር፣-** በሙያው ከተመረቅሁ በኋላ ባር ኤግዛም (የጠበቆች ፈተና) የሚባለውን ፈተና ወስጄ ካለፍኩ በኋላ ሥራ ጀመርኩ:: ሥራ የጀመርኩት የቢል ጌትስ አባት ድርጅት ውስጥ ነበር:: እዚያ እየሠራሁ በጎን ደግሞ ቢሮ ተከራይቼ የራሴን የጥብቅና ሥራ መሥራት ቀጠልኩ:: ምናልባትም በዚያን ጊዜ በሲያትል ሌላ ኢትዮጲያዊ ጠበቃ የነበረ አይመስለኝም:: በየቦታው እየተንቀሳቀስኩ ወገኖቼን በጥብቅና ሥራ እረዳ ነበር:: የብዙዎችን ጉዳይም በስኬት አጠናቅቄአለሁ፤ ብዙዎችም እርካታቸውን በመግለፅ ምስጋናቸውን ያቀርቡልኝ ነበር::

ለእኔ ሥራዬ ወገኖቼን ተጠቃሚ ያደረገና እርካታን ያስገኘ ሆኖ ከማየት በላይ የሚያረካኝ ጉዳይ የለም:: በሂደትም፣ "ሼክስፒር ፈይሳ የህግ ቢሮ" የሚል ድርጅት ከፍቼ፣ ሌሎች በመስኩ ጥሩ የትምህርት ዝግጅትና ልምድ ያላቸውን ሙያተኞች አብረውኝ እንዲሠሩ በማድረግ ሥራዬን አጠናከርኩ። ሥራዬን በተመለከተ በአብዛኛው የፍትሀብሄር ጉዳዮችን እይዛለሁ፣ የወንጀል ጉዳዮች ላይም እንሠራለን፣ ከሰብአዊ መብቶች ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ላይ ግን፣ ከሁሉም በላይ ትኩረት አደርግባቸዋለሁ። በፖሊሶችና በሌሎች አካላት የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ሲፈፀሙ ለብዙ ተጠቂዎች ጥብቅና ቆመናል::

በአብዛኛው በፓሊስ የሰብዓዊ መብት ረገጣ የሚደረግባቸው ጥቁር አሜሪካዊያን ናቸው:: የእነሱን ኬዝ እየያዝን የበዙትን በአሸናፊነት ተወጥተናል:: ትልልቅ የአካል ጉዳት እና የሞት አደጋ ያስከተሉ ክስተቶች ላይ ክስ በመመስረት ተሟግተን ተጎጂዎች እና የተጎጂ ቤተሰቦች ጠቀም ያለ ካሣ እንዲያገኙና፣ በደል አድራሾችም በሕግ እንዲጠየቁ አድርገናል።

**ኢትዮጲስ፣- በቅርቡ በሀገራችን አንድ የአውሮፕላን አደጋ ደርሷል፡፡ ንብረትነቱ ኢትዮጲያ አየር መንገድ የሆነ ቦይንግ 737 ማክስ 8 የተሰኘ አውሮፕላን ተከስክሶ ሰዎች ሞተዋል፡፡ ይህን እንዴት ያዩታል?**

**ዶ/ር ሼክስፒር፣-** ቦይንግ የተሰኘው ትልቅ የአውሮፕላን ኩባንያ አውሮፕላን የሚያመርተው ሲያትል ውስጥ ነው:: ቦይንግ 737 ማክስ 8 አውሮፕላንም፣ ሲያትል ሬንተል የሚባል አካባቢ ነዉ የሚመረተው:: ከእኔ መኖሪያ ቤት ብዙ አይርቅም፤ ስወጣ ስገባ በየቀኑ በሚባል ደረጃ አየዋለሁ:: የሚሠሩትን ሰዎች፣ ኢንጂነሮቹን በቅርበት አውቃቸዋለሁ::

እንደገና ወገኖቼ በዚህ አውሮፕላን መከስከስ አደጋ ተጎድተዋል፣ አየር መንገዳችን ኪሳራ ደርሶበታል፣ ይህ ሁሉ ጉዳይ ትኩረቴን በእጅጉ እንዲሳብ አድርጎታል፣የቦይንግ ካምፓኒን ከዚህ በፊት ከስሼ ስለማውቅም፣ በጥናት ላይ የተመሰረቱ መረጃዎች አሉኝ::

**ኢትዮጲስ፣- ይህ ማለት አሁን በኢትዮጵያ አየር መነገድና በቦይንግ ኩባንያ መካከል የተከሰተውን ጉዳይ ለመያዝ ይፈልጋሉ ማለት ነው ?**

**ዶ/ር ሼክስፒር፣-** በጣም እፈልጋለሁ:: ይህን ጉዳይ ብይዘውና ወገኖቼንና ሀገሬን ብርዳ ደስ ይለኛል:: መጀመሪያ፣ በደረሰው አደጋ ልቤ ክፉኛ መሰበሩን መግለጽ እፈልጋለሁ:: የደረሰው ነገር በጣም የሚያሳዝንና ሁላችንንም የሚነካ ነው:: አውሮፕላን የህወታችን አካል እየሆነ ነው፤ ከሀገር አቋርጠን የምንሄደው በአብዛኛው በአውሮፕላን ነው::

ያኔ እኔ እዚያ ውስጥ ብሆን ኖሮስ? ያሰኛል:: በሌላ በኩል፣ ነገ እኔ የምጓዝበት አውሮፕላን ተመሳሳይ አደጋ ቢደርስበትስ? ብለን ለደህንነታችን እንሰጋለን:: እኔ እንደዛ ነው የተሰማኝ:: የሰዎች ሞትና የቤተሰቦቻቸው ሀዘንም ያሳምማል:: አደጋው ደግሞ፣ በቸልተኝነት ደረሰ ብዬ ነው የማስበው:: በዚህ የግዴለሽነት ተግባር ወገኖቼ ላይ ጉዳት እንዲደርስ ያደረገውን ኪባንያ ብፋረደው ደስ ይለኛል::

**ኢትዮጲስ፣- ይህ ዓይነቱ አውሮፕላን ሲከሰከስ የመጀመሪያው አይደለም፤ ይህ የኩባንያውን ግዴለሽነት ይበልጥ አያጎላውም?**

**ዶ/ር ሼክስፒር፣-** በጣም ጥሩ ጥያቄ ነው:: የመጀመሪያው አውሮፕላን ሲወድቅም ኩባንያው ችግሩን ያውቅ ነበር:: ከዚያ በመነሳት መስተካከል የነበረባቸው ፣መጨመር የሚገባቸው ሶፍት ዌሮች እንደነበሩ ኩባንያው ያውቅ ነበር:: ከዚያ በመነሳት እነዚያ ሶፍት ዌሮች ለእኛ ሀገሩ አውሮፕላን ለምን አልተጨመሩም? የሚለው ብዙ እያነጋገረ ነው::

የአሜሪካ የፍትህ ሚኒስትር በጉዳዩ ላይ ምርመራ እያደረገ ነው:: እኔና የሥራ ባልደረቦቼ በጉዳዩ ላይ ብዙ ጥናት አድርገን የደረስንባቸው ብዙ ነገሮች አሉ:: ስለ አውሮፕላኑ፣ ስለአመራረቱ፣ ስለ ቴክኖሎጂው፣ ስለ ሶፍት ዌሮቹ በጥልቀት ከሚያውቁ ሰዎች ጋር ተወያይተናል::

**ኢትዮጲስ፣- ብዙ ወገኖች የኩባንያውን ይቅርታ መጠየቅና “ኃላፊነቱን እወስዳለሁ” ማለት እንደ መልካም ውጤትና ጉዳዩን እንዳለቀለት አድርገው በመውሰድ ላይ ናቸው፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ፣ ቀጣይ የሚያከራክር ጉዳይ አይኖርም ሊባል ይችላል፡፡ እርሶ እዚህ ላይ ምን ይላሉ ? ኩባንያው የጠየቀው ይቅርታ የተሟላ ነው ማለት ይቻላል?**

**ዶ/ር ሼክስፒር፣-** በጣም ጥሩ ነጥብ ነው የተነሳው:: እንደተባለው የኩባንያው ይቅርታ መጠየቅ ለጉዳዩ ዕልባት የሚያስገኝና ነገሩንም ያለቀለት አድርጎ ሊያሳይ ይችላል:: በኩባንያው ይቅርታ መጠየቅም እርካታ የተሰማቸው ብዙ ናቸው:: እውነታው ግን ያ አይደለም:: ይቅርታው ሙሉ አይደለም፤ ኃላፊነቱንም ጠቅልሎ አልወሰደም::

በጥንቃቄ ከመረመርነው፣ የቦይንግ ኩባንያ ኃላፊ የተናገሩት ምን ይላል? "ቼን ኦፍ ኢቨንትስ" (የተያያዙ ነገሮች) የሚል ነገር አንስተዋል:: አውሮፕላን የሚሰራው ብዙ ነገሮች ተቀጣጥለው ነው:: አንዱ ከሌላው ጋር ባለው መስተጋብር ነው የሚሰራው፤ ችግር ሲከሰትም እንደዛው::

ይህን መሰረት በማድረግ የተናገሩት ነገር አለ፤ አሜሪካኖችን አውቃቸዋለሁ:: ከብዙ ኩባንያዎቻቸው ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ላይ ሠርቻለሁ:: 17 ዓመታት ቀላል ጊዜ አይደለም:: ጥፋተኛ መሆናቸውን ሲያውቁ፣ ነገሩ እንዳይራገብ ይቅርታ ይሉና ለጊዜው ያቀዘቅዙታል:: ከዚያ፣ "ብናጠፋም ጥፋታችን ያን ያህል የጎላ አይደለም" ወደ ማለት ይሄዳሉ:: ይቅርታ ማለታቸው ግፊቶችን ያበርድላቸዋል:: በቢዝነሳቸው ላይ የሚደርሰውንም ጉዳት ይቀንስላቸዋል::

"ቼን ኦፍ ኢቨንትስ"(የተያያዙ ነገሮች) ሲሉ፣ ኃላፊነቱን ወደ ብዙ ክፍሎች፣ የኢትዮጲያ አየር መንገድን ጨምሮ፣ ለመከፋፈል መዘጋጀታቸውን ያሳያል:: ለምሳሌ፣ አውሮፕላኑ "ሴንሰር" የሆነ ነገር ሲመታው (ወፍና የመሳሰለው) ሶፍትዌሩ አይሰራም:: ይህ ሲሆን ነው አደጋ የሚያስከትለው የሚሉት ነገር አላቸው::

ወደ 21 ዞሯል



**አማንዳ ስፐርበር**
**ለንደን ስኩል ኦፍ ኢኮኖሚክስ አንድ ፖሊቲካል ሳይንስ**
**እንግሊዝ**

# አሜሪካ የአፍሪቃ ቀንድ ወታደራዊ ይዞታዋን እያጠናከረች ነው



## እንደመግቢያ

በግንባታ ፕሮጄክቱ የተሳተፉ እና ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸው ባለሥልጣናት እንደሚሉት፣ የዩ.ኤስ. አሜሪካ መከላከያ ሚኒስቴር መነሻውን በአፍሪቃ፣ ጂቡቲ የሚገኘውን ትልቁ የአሜሪካ ወታደራዊ የጦር ሰፈር፣ ሌሞኒዬር ካምፕ፣ ያደረገ በአህጉሪቷ ምሥራቃዊ ክፍል የሚዘረጋ የሎጂስቲክስ አቅርቦት መሥመር ለመዘርጋት የሚያስችለውን የመጀመሪያ ደረጃ ሥራ እያከናወነ ይገኛል:: በየብስ ላይ የሚዘረጋው ይኸው የሎጂስቲክስ አቅርቦት መሥመር፣ የመጀመሪያው እርከን፣ ሌሞኒዬር ካምፕን በሶማሊያ ከሚገኘው የዩ.ኤስ. አሜሪካ ባሌዶግሌ ወታደራዊ የጦር ሰፈር ጋር የሚያገናኝ ነው:: የሚገነባው መንገድ ከአል-ቃይዳ ጋር ግንኙነት ያለው አል-ሸባብ በሚቆጣጠራቸው አካባቢዎች በኩል የሚያልፍ ነው:: ከዚህ በተጨማሪም፣ አካባቢው የግል ሚሊሺያ ያላቸው የጦር አበጋዞች የሚንቀሳቀሱበት፣ እንዲሁም ሶማሊያን ከኢትዮጵያ ጋር የሚያዋስናት ውጥረት የሰፈነበትን ድንበር ታክኮ የሚያልፍ ነው::

## የፕሮጀክቱ ዕንቅፋቶች

ከዩ.ኤስ. አሜሪካ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ቅፍለቶች የሎጂስቲክስ አቅርቦት መሥመሩ በሚዘረጋበት ክልል በኩል መላኩ፣ አደጋን የሚጋብዝ እንደሆነ የታወቀ ነው:: በሶማሊያ ርዕሰ-ከተማ፣ ሞቃዲሾ፣ የሚገኙ የውጭ ዜጎች እንኳን ከቦታ ቦታ የሚንቀሳቀሱት የጦር መሣሪያ በታጠቁ ዐጀቢዎች ታጅበው እና በብረት ለበስ ተሽከርካሪዎች ነው:: ከርዕሰ-ከተማዋ ለቅቀው አጭር ርቀት እንኳን የሚጓዙት በዓየር ነው:: የዩ.ኤስ. አሜሪካ ወታደሮች ብዙውን ጊዜ በርካታ የውጭ ዜጎች ከሚገኙበት ሞቃዲሾ ዓለም ዓቀፍ አውሮፕላን ተነሥተው 100 ኪሎ ሜትሮችን ርቆ ወደሚገኘው ባሌዶግሌ የጦር ሰፈራቸው የሚጓዙት በሄሊኮፕተር ነው::

ስለዚህም፣ ከሶማሊያ የቆዳ ስፋት ሦስት-አራተኛውን በሚወክለው ግዛት በኩል የሚያልፍ የሎጂስቲክስ አቅርቦት መሥመር መዘርጋቱ፣ ከፍተኛ ወጪን ብቻ ሳይሆን፣ ቆራጥነትን ጭምር የሚጠይቅ ፕሮጀክት ነው:: የውስጥ ዐዋቂ ምንጮች እንደሚሉት፣ የሎጂስቲክስ አቅርቦት መሥመሩ ሶማሊያ ውስጥ የሚያልፍበትን መንገድ የዲዛይን ሥራ ብቻ 75 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ወጪን ይጠይቃል::

## የፕሮጀክቱ ኃላፊነት

የፕሮጀክቱን ኃላፊነት የወሰደው በሶማሊያ የሚገኘውን የዩ.ኤስ. አሜሪካ የአፍሪቃ እዝን (አፍሪኮም) ከሚደግፉት ጥቂት ድርጅቶች መካከል አንዱ የሆነውና፣ ዋና መሥሪያ ቤቱ በቨርጂኒያ ግዛት የሚገኘው ፓሲፊክ አርኪቴክቶች እና ኢንጂኔሮች ኩባንያ ነው:: “አፍሪኮም” በሚል መጠሪያ የሚታወቀው የዩ.ኤስ. አሜሪካ ወታደራዊ የአፍሪቃ እዝም ሆነ የመከላከያ ኮንትራክተሩ፣ ከደኅንነት ጋር የተያያዘ እንደሆነ በመጠቆም፣ ስለፕሮጀክቱ ምንም ዓይነት መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ አልሆኑም::

ፓሲፊክ አርኪቴክቶች እና ኢንጂኔሮች ኩባንያ፣ የዩ.ኤስ. አሜሪካ የአፍሪቃ እዝ በሶማሊያ ካለው እንቅስቃሴ ጋር ያለው ቁርኝት ከጊዜ ወደጊዜ እየተጠናከረ በመምጣቱ፣ ባለፈው ጥር ወር በሞቃዲሾ ከተማ Africa Expeditionary Services የተሰኘ አንድ ተጨማሪ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ከፍቷል:: ኩባንያው ለፕሮጀክቱ እገዛ እንዲያደርግ የጠየቀው አንድ ሌላ ድርጅት፣ ሥራው እጅግ በጣም አስቸጋሪ እንደሚሆን በመጠቆም፣ ፈቃደኛ ሳይሆን ቀርቷል::

## የፕሮጀክቱ ዓላማ

አንዳንድ ሶማሊያውያን እና አሜሪካውያን ባለድርሻ አካላትም ቢሆኑ፣ ከፍተኛ መጠን ያለው መዋዕለ-ንዋይ በዚህ መሰሉ አደገኛ ፕሮጀክት ላይ ማፍሰሱ እንደማይዋጥላቸው ከመግለጽ ወደኋላ አላሉም:: ለአሁኑ እና ለቀድሞው የሶማሊያ ፕሬዚዳንቶች የፀረ-ሽብር እና የደኅንነት አማካሪው፣ ሁሴን ሼኽ-አሊ፣ ፕሮጀክቱ ከከባድ የጸጥታ እና የሎጂስቲክስ ተግዳሮቶች ጋር መፋጠጡ የማይቀር በመሆኑ፣ በሁለት የዩ.ኤስ. አሜሪካ ወታደራዊ የጦር ሰፈሮች መካከል የአቅርቦት መሥመር መዘርጋቱ ጊዜን እና ገንዘብን ከማባከን ባለፈ የሚፈይደው ነገር እንደሌለ ገልጸዋል::

ሂራል ኢንስቲትዩት የተሰኘው የደኅንነት ጥናት ተቋም መሥራቹ፣ ሼኽ-አሊ፣ "አሜሪካውያኑ ትኩረት ማድረግ ያለባቸው የአካባቢውን ኃይሎች በፀረ-ሽብር ውጊያ ስልቶች የበለጠ ለማብቃቱ እና የአካባቢውን ባለሥልጣናት በመልካም አስተዳደር ዙሪያ ለማገዙ ነው" ብለዋል::

አንድ የሶማሊያ የደኅንነት ባለሥልጣን በበኩላቸው፣ ፕሮጄክቱን "ጅብደኝነት" ሲሉ ገልጸውታል:: ያም ሆኖ፣ እኚሁ ባለሥልጣን ፈገግ ብለው፣ "ማንኛውም የዩ.ኤስ. አሜሪካ ኢንቬስትመንት" በሀገራቸው ሕዝን ዘንድ ተቀባይነት እንዳለው ተናግረዋል::

ይሁን እንጂ፣ የደኅንነት ሹሙ የሎጂስቲክስ አቅርቦት መሥመሩ ግንባታ ሌላ ዓላማም ያነገበ ሊሆን እንደሚችል አልሸሸጉም:: በዚሁም መሠረት፣ የሶማሊያ መንግሥት የውጭ መንግሥታት እና ድንበር ዘለል ኩባንያዎች በሀገሪቷ ማንኛውም አካባቢ ተንቀሳቅሰው መሥራት እንደሚችሉ ማሳየት ይፈልጋል:: እንደደኅንነት ሹሙ አባባል ከሆነ፣ የሎጂስቲክስ አቅርቦት መሥመሩ ግንባታ፣ ሶማሊያ በግንቦት 2017 (እ.አ.አ.) በዓለም ዓቀፍ አጋሮች እና በተባበሩት መንግሥታት ድጋፍ ተግባራዊ ለማድረግ የተስማማችው የጸጥታ ስምምነት አንድ አካል ነው::

## የዩ.ኤስ. አሜሪካ እና የቻይና ፉክክር

ቻይና በአፍሪቃ ቀንድ እያደረገች ያለችው እንቅስቃሴ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የዩ.ኤስ. አሜሪካ መንግሥትን ምቾት እየነሣው ነው:: በአፍሪቃ የሚገኘው የዩ.ኤስ. አሜሪካ ጦር ጄነራሉ፣ ቶማስ ዋልድሆውሰር እንደገለጹት፣ ቻይና በ2017 (እ.አ.አ.) በጂቡቲ የገነባችው የባሕር ኃይል መደብ በሀገራቸው ብሔራዊ ጥቅም ላይ "ትልቅ ተጽዕኖ" ይኖረዋል:: ጄነራል ዋልድሆውሰር ይህን የተናገሩት፣ ቻይና በአፍሪቃ አህጉር ያላትን ይዞታ በማጠናከሯ ዙሪያ ባለፈው የፈረንጆች ዓመት ከዩ.ኤስ. አሜሪካ ኮንግረስ ፊት ቀርበው ባደረጉት ንግግር ነው:: ከዚህ በተጨማሪም፣ ጄነራሉ ከሴኔቱ የጦር ኃይሎች ጉዳይ ኮሚቴ ፊት ቀርበው ባደረጉት ንግግር፣ "ቻይና በአፍሪቃ ቀንድ እያደረገች ያለችውን እንቅስቃሴ እና ወታደራዊ ይዞታዋን በጥንቃቄ እየተከታተልነው ነው" ብለዋል::

የዩ.ኤስ. አሜሪካ ሴኔት በጥቅምት 2018 (እ.አ.አ.) በሁለቱም ተፎካካሪ ፓርቲዎች (ሪፐብሊካን እና ዴሞክራቶች) ድጋፍ ለአፍሪቃ፣ ለእስያ እና ለመካከለኛው ምሥራቅ ሀገራት መንግሥታት ለመሠረተ-ልማት ፕሮጀክቶች ግንባታ የሚውል 60 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ብድር መድቧል:: "የዩ.ኤስ. አሜሪካ ዓለም ዓቀፍ ልማት ፋይናንስ ኮርፖሬሽን" በተሰኘ በቅርቡ በተቋቋመ አዲስ የመንግሥት ተቋም ቁጥጥር ሥር ያለው ይኸው ገንዘብ፣ ቻይና Belt and Road Initiative በሚል ውጥን ለማንቀሳቀስ ያለመችው በትሪሊዮን የሚቆጠር የአሜሪካ ዶላርን ለመቋቋም ያለመ ነው:: ቻይና በዚሁ ውጥኗ አማካኝነት በእስያ፣ በአፍሪቃ እና በመካከለኛው

ወደ 20 ዞሯል



ዶክተር ሉክ ፓቲ
አክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ፣ እንግሊዝ
የኃይል አቅርቦት ጥናቶች ከፍተኛ ተመራማሪ

# በአፍሪቃ የሕንድ እና የቻይና ፉክክር

## እንደመግቢያ

ቻይና ባትኖር ኖሮ፣ የአፍሪቃ ትልቋ የንግድ አጋር ሕንድ በሆነች ነበር:: ያም ሆኖ፣ ቻይና እና ሕንድ በንግድ ዙሪያ አፍሪቃ ውስጥ የሚከተሉት አካሄድ የተለያየ ነው::

ቻይና በየዓመቱ የአፍሪቃ ሀገራትን ያሳተፈ የአፍሪቃ ፎረም ታካሂዳለች:: ታዲያ፣ በፎረሙ እንዲገኙ ያልታደሙ የውጭ ኃይሎች፣ ስብሰባውን በቅርበት መከታተላቸው የአደባባይ ምሥጢር ነው:: ከእነኝህ የውጭ ኃይሎች መካከልም አንዷ፣ የቻይና አጐራባች እና ተፎካካሪ የሆነችው ሕንድ ናት::

ሕንድም ብትሆን በየሦስት ዓመቱ የምታዘጋጀው የራሷ የአፍሪቃ ፎረም አላት:: ሕንድ ልክ እንደቻይና ከአፍሪቃ ሀገራት ያላት የንግድ ግንኙነት ባለፉት ዐሥር ዓመታት በከፍተኛ ሁኔታ ተመንድጓል:: ይሁን እንጂ፣ የኒው ዴልሂ አስተዳደር ለአፍሪቃ የሚሰጠው ትኩረት ከኦፊሴላዊ የመንግሥት ባለሥልጣናት ጉብኝት በኋላ በተደጋጋሚ ሲደበዝዝ ተስተውሏል::

በአሁኑ ወቅት ግን፣ ሕንድ ለአፍሪቃ የምትሰጠውን ትኩረት ቸላ ማለት የለባትም:: አፍሪቃ በአሁኑ ወቅት አልፎ አልፎ ወይም እንደነገሩ የምትታይ አህጉር አይደለችም:: ይልቁንም፣ የኒው ዴልሂ አስተዳደር፣ የቤይጂንግ መንግሥት ባለፉት ጥቂት ዐሥርተ-ዓመታት በአፍሪቃ ነድፎ በተንቀሳቀሰበት ጂኦስትራቴጂያዊ ዕቅድ ከአህጉሪቷ ያጣውን ጥቅም መልሶ ለማግኘት ቆርጦ መነሣት ይኖርበታል:: የቻይና Belt and Road Initiative ውጥን እና ቤይጂንግ በሕንድ ውቅያኖስ እና በቀይ ባሕር አካባቢ ያላት ወታደራዊ እንቅስቃሴ፣ ሕንድ ከአፍሪቃ ጋር ባላት ግንኙነት ላይ ተጽዕኖ እያሳደሩ ነው::

## የሕንድ እና የአፍሪቃ ግንኙነት

ሕንድ ከአፍሪቃ ጋር ረዥም ዘመን ያስቆጠረ ግንኙነት ያላት ሀገር ናት:: ከበርካታ ዓመታት በፊት ወደአፍሪቃ ያመሩ ሕንዳውያን ዲያስፖራዎች፣ በተለያዩ የአህጉሪቷ ሀገሮች ጠንካራ እና ሥር የሰደደ መሠረት ገንብተዋል:: የአፍሪቃ ሀገራት ከቅኝ አገዛዝ እና ከአፓርታይድ ቀንበር ለመላቀቅ ባደረጓቸው ትግሎች፣ የሕንድ መሥራች አባቶች ድጋፍ አልተለያቸውም:: በቀዝቃዛው ጦርነት ወቅት፣ በርካታ የአፍሪቃ ሀገራት ከሕንድ ጋር በገለልተኛ ሀገራት ንቅናቄ ሥር ታቅፈው የሁለቱን፣ ማለትም የዩ.ኤስ. አሜሪካ እና የቀድሞዋ ሶቪዬት ኅብረት ካምፖች፣ የበላይነት ለመቋቋም ታግለዋል::

## የአፍሪቃ እና የሕንድ የንግድ ልውውጥ

በአሁኑ ዘመን ግን፣ ሕንድ ከአፍሪቃ ጋር ያላት ግንኙነት በዋነኝነት ከንግድ ጋር የተሳሰረ ነው:: በ2002-03 (እ.አ.አ.) በሁለቱ ወገኖች መካከል የነበረው የንግድ እንቅስቃሴ 6.5 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ብቻ ነበር:: ይሁን እንጂ፣ የሕንድ የሀገር ውስጥ ኢኮኖሚ ለ50 ዓመታት ባስመዘገበው እድገት በመታገዝ፣ በ2012-13 (እ.አ.አ.) በሁለቱ ወገኖች መካከል ያለው የንግድ ልውውጥ ከ70 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር በላይ ሆኗል::

ይኸው የንግድ እንቅስቃሴ እድገት በጣም ፈጣን ከመሆኑ የተነሣ፣ ቻይና ባትኖር ኖሮ፣ ሕንድ የአፍሪቃ ትልቋ የንግድ አጋር በሆነች ነበር:: በ2017-18 (እ.አ.አ.) 63 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር የደረሰው የሁለቱ ወገኖች የንግድ እንቅስቃሴ፣ ሕንድ ከአፍሪቃ ጋር ያላት የንግድ ልውውጥ፣ ከዩ.ኤስ. አሜሪካ እና ከአውሮጳ ኅብረት ጋር ካላት እንደሚበልጥ ጠቋሚ ነው:: ዳሩ ግን፣ ቻይና አፍሪቃ ውስጥ በስፋት እየተንቀሳቀሰች ትገኛለች:: በ2017 (እ.አ.አ.) ቻይና ከአፍሪቃ ሀገራት ጋር የነበራት የንግድ ልውውጥ 172 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ደርሷል፤ ይህም አኃዝ ሕንድ ከአፍሪቃ ሀገራት ያላትን የንግድ ልውውጥ በሦስት እጥፍ ያህል ይበልጣል::

## ሕንድ በአፍሪቃ

የሕንድ መሪዎች ሁለቱ የእስያ ሀገራት፣ ሕንድ እና ቻይና፣ ከአፍሪቃ ጋር ያላቸውን ያልተመጣጠነ የንግድ ልውውጥ በተመለከተ፣ ሀገራቸው በአህጉሪቷ የምትከተለው አካሄድ 'ከቻይና የተለየ ነው' ሲሉ ይከራከራሉ:: የሕንድ ባለሥልጣናት እንደሚሉት፣ ሕንድ ከአፍሪቃ ጋር ያላት የንግድ ግንኙነት እንደቻይና ከመንግሥት ተቋማት ጋር የተሳሰረ ሳይሆን፣ በግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ የሚመራ ነው:: እውነታው ግን፣ ሕንድ በአፍሪቃ የምትከተለው አካሄድ ከቻይና እምብዛም የተለየ ካለመሆኑም ባሻገር፣ ተጽዕኖውም ተመሳሳይ ነው::

"የሕንድ የነጻነት አባት" የሆኑት ማሕተማ ጋንዲ፣ በአንድ ወቅት "በሕንድ እና በቻይና መካከል የሚኖረው የንግድ ልውውጥ ምዕራባውያን በዝባዦች እንደሚፈልጉት ከጥሬ ዕቃዎች በተመረቱ የፋብሪካ ምርቶች ሳይሆን፣ በሐሳቦች እና በአገልግሎቶች ላይ የተመሠረተ ይሆናል" ሲሉ ተናግረው ነበር:: በአሁኑ ዘመን ግን፣ ሕንድ ከአፍሪቃ ጋር ያላት የንግድ ግንኙነት ማሕተማ ጋንዲ እንዳሰቡት አይደለም::

በፍጥነት እያደገ ያለው የሕንድ ኢኮኖሚ የኃይል አቅርቦት ፍላጎቱ ከፍተኛ በመሆኑ፣ ሀገሪቷ ከአፍሪቃ በዋነኝነት የምታስመጣው ነዳጅ ዘይት ነው፤ ሕንድ ነዳጅ ዘይቷን በአብዛኛው የምትገዛውም ከናይጄሪያ ነው:: ሕንድ ከአፍሪቃ ጋር ባላት የንግድ ግንኙነት በቀጣይነት በብዛት ወደሀገሯ የምታስገባው፣ በአብዛኛው የደቡብ አፍሪቃን ወርቅ እና አልማዝ ጨምሮ፣ ማዕድንን የመሰሉ የተፈጥሮ ሀብቶችን ነው:: በሁለቱ ወገኖች መካከል ያለውን የንግድ ግንኙነት አስቂኝ የሚያደርገው ደግሞ፣ ሕንድ ወደአፍሪቃ ከምትልካቸው ሸቀጦች መካከል ከአህጉሪቷ ከገዛችው ድፍድፍ ነዳጅ ዘይት በማላያላም እና በሌሎች የሀገሪቷ አካባቢዎች በሚገኙ ማጣሪያዎች የተመረተ ናፍጣ እና ቤንዚን መሆኑ ነው::

በርካት የሕንድ መሪዎች እንደሚሉት ሳይሆን፣ ሀገራቸው ከአፍሪቃ ጋር ያላት የንግድ ግንኙነት፣ ያን ያህል አመርቂ አይደለም:: ሕንድ በ2016 (እ.አ.አ.) በአፍሪቃ ኢንቬስት ያደረገችው መዋዕለ-ንዋይ 14 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ብቻ ነበር፤ ይህም አኃዝ ሕንድን ከሲንጋፖር እና ከስዊዘርላድ መካከል፣ እንዲሁም ከዩ.ኤስ. አሜሪካ፣ ከዩናይትድ ኪንግደም፣ ከፈረንሳይ እና ከቻይና በታች አስቀምጧታል:: የኦብዘርቨር ሪሰርች ፋውንዴሽን ባልደረባው፣ ማላንቻ ቻክራባርቲ፣ እንደሚሉት፣ የሕንድ ባለሀብቶች በሞሪሽስ ያለውን የግብር ክፍያ ከለላን በ2008 (እ.አ.አ.) መጠቀም ከጀመሩ ወዲህ፣ ሀገሪቷ በአፍሪቃ ያላት የኢንቬስትመንት መጠን ከ47 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር እንደሚበልጥ ተደርጎ መነገሩ ስሕተት ነው::

ጠቅላይ ሚኒስትር ናሬንድራ ሞዲ በ2015 (እ.አ.አ.) የሕንድ-አፍሪቃ ፎረም ለአህጉሪቷ የሰጡት የ10 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ብድር፣ ቻይና ለአፍሪቃ




ወደ 21 ዞሯል

*አዘጋጅ፡- ማውሮ*

# የሥራ እና የግል ሕይወታችንን እናመጣጥን

የሥራ እና የግል ሕይወታችን ሚዛናዊነት ሲዛባ፣ ውጥረት ጤናችንን ማወኩ አይቀርም፡፡ በእርግጥ፣ በሥራ እና በግል ሕይወታችን መካከል ያለው ወሰን በአመዛኙ ግልጽ የነበረበት ዘመን በአንድ ወቅት ነበር፡፡ በአሁኑ ዘመን ግን፣ ሥራችን በግል ሕይወታችን ውስጥ ጣልቃ የመግባት ዕድሉ በጣም ሰፊ ነው፡፡ ስለዚህም፣ የሥራ እና የግል ሕይወታችንን ማመጣጠኑ በጣሙን ሊቸግረን ይችላል፡፡

ይህ እውነታ ፍንትው ብሎ የሚወጣው ደግሞ፣ በመዋቅር ለውጥ፣ በሰው ኃይል ቅነሳ፣ አሊያም በሌሎች ምክንያቶች 'ሥራችንን ልናጣ እንችላለን' የሚል ሥጋት ሲኖርብን ነው፡፡ ከሥራ ሕይወታችን በአብዛኛው እንዳንነጠል የሚያደርጉ ዘመን አመጣሽ የቴክኖሎጂ ውጤቶች ደግሞ፣ የግል ሕይወታችንን ሊያዘቡት ይችላሉ፡፡ የሥራ እና የግል ሕይወት ሚዛናዊነትን ማስተካከሉ፣ በተለይ ሕፃናት ልጆች ላሏቸው ወላጆች፣ በጣም አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል፤ ለምሳሌ ያህል፣ በዩ.ኤስ. አሜሪካ ለመጀመሪያ ጊዜ እናት ከሆኑ ሠራተኛ ሴቶች መካከል 60% የሚሆኑት ልጃቸውን በወለዱ በ12 ሳምንታት ውስጥ ወደሥራ ገበታቸው ይመለሳሉ፡፡

ያም ሆኖ፣ የሥራ እና የግል ሕይወት ሚዛናዊነትን ማመጣጠኑ ብዙም አስቸጋሪ አይደለም፡፡ በዚህ ረገድ በቀዳሚነት ማድረግ የሚኖርብን፣ ከሥራችን ጋር ያለንን ግንኙነት መገምገም ነው፡፡ በቀጣይነትም፣ ጤናማ እና ከውጥረት የጸዳ የተመጣጠነ የሥራ እና የግል ሕይወት መምራት የምንችልበትን እስትራቴጂ መንደፍ እና ይህንኑ ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅብናል፡፡

## ለሥራችን ቅድሚያ እንሰጣለን?

እድገት ለማግኘት፣ በየጊዜው እየጨመረ የሚመጣውን የሥራ ጫና ለመቋቋም፣ አሊያም ተጨማሪ ገንዘብ ለማግኘት ከፈለግን፣ ለሥራችን የምንሰጠው ትኩረት ወይም በዚሁ ላይ የምናሳልፈው ጊዜ ሊጨምር ይችላል፡፡ ይሁን እንጂ፣ አብዛኛውን ጊዜያችንን በሥራ የምናሳልፍ ከሆነ፣ የግል ሕይወታችን ሊጐዳ ይችላል፡፡

የሥራ እና የግል ሕይወታችን ሚዛናዊነት የተመጣጠነ ካልሆነ፣ ለቀጣዮቹ ችግሮች ልንጋለጥ እንችላለን፡-

**•አካላዊ ዝለት፡-** የድካም ስሜት ሲሰማን ምርታማ የመሆን እና በግልጽ የማሰብ ችሎታችን ችግር ሊገጥመው ይችላል፡፡ ይህም በተራው፣ የሙያችንን ክህሎት ሊያዛየ፣ አሊያም አደገኛ ወይም ከባድ ዋጋ የሚያስከፍሉ ስሕተቶችን እንድንሠራ ሊያደርግ ይችላል፡፡

**•ደካማ ጤንነት፡-** ውጥረት በቅስመ-ተፈጥሮ መከላከያ ሥርዓታችንን (በሽታ የመከላከል ዓቅማችንን) የሚጐዳ ከመሆኑም ባሻገር፣ በጤና እክል ሳቢያ ያሉብንን የበሽታ ምልክቶች ሊያባብስ ይችላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም፣ ውጥረት ለሱሰኝነት ሊያጋልጠን ይችላል፡፡

**•ለወዳጅ ዘመዶቻችን የምንሰጠው ጊዜ መቀነስ፡** - ከተለመደው በላይ ለሥራችን ትኩረት የምንሰጥ ከሆነ፣ በተለያዩ የቤተሰባችን ወይም የወዳጆቻችን ዝግጅቶች ወይም ታሪካዊ አጋጣሚዎች ላይ የመገኘት ዕድላችን በጣሙን ይቀንሳል፡፡ ይህም በተራው፣ የብቸኝነት ወይም የመገለል ስሜት በመፍጠር፣ ከወዳጅ ዘመዶቻችን ጋር ያለንን ግንኙነት ሊጐዳው ይችላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም፣ ሁሌ በሥራ የምንወጠር ከሆነ፣ ከሰዎች ጋር ያለንን ግንኙነት ለማዳበር እንቸገራለን፡፡

**•ከዓቅማችን በላይ ሥራ ይጠበቅብናል፡** - በመደበኛነት ከወትሮው የበለጠ ጊዜ ለሥራችን የምናውል ከሆነ፣ ተጨማሪ ኃላፊነት ሊጣልብን ይችላል፡፡ ይህን ጊዜም መጋፈጥ ያሉብን ጭንቀቶች እና ተግዳሮቶች በዚያው መጠን ይጨምራሉ፡፡

በሥራ ዓለም ውስጥ እስከተሰማራን ድረስ የሥራ እና የግል ሕይወታችንን ሚዛናዊነት ማስተካከሉ ሁሌም የሚፈታተነን ጉዳይ መሆኑ አይቀርም፡፡ ይሁን እንጂ፣ ገደብ ማበጀት እና ራሳችንን ይበልጥ መንከባከብ ከቻልን፣ የሚመቸንን የተመጣጠነ የሥራ እና የግል ሕይወት ማበጀት አያቅተንም፡፡

## ገደብ ማበጀት

ጊዜን ፈጽሞ መፍጠርም ሆነ ማምረት አንችልም፡፡ በሕይወታችን ዙሪያ ገደብ ካላበጀን ደግሞ፣ ሥራችን ወይም ሌሎች የማይታለፉ ግዴታዎችን እና የሚያስደስቱንን ነገሮች የምናከናውንበትን ወይም ከሰዎች ጋር ለሚኖረን ግንኙነት ጊዜ እናጣለን፡፡

**•ጊዜያችንን መቆጣጠር፡-** የማያስደስቱንን ወይም ከዓቅማችን በላይ የሆኑ ሥራዎችን ለሌሎች ሰዎች ለማስተላለፍ፣ አሊያም ጭንቀታችንን እና ለችግሮች የምናስቀምጣቸውን መፍትሔዎች ለአሠሪዎቻችን ወይም ለሌሎች ሰዎች ለማካፈል ማቅማማት የለብንም፡፡ ገበያ መውጣትን እና ልብስ ማጠብን የመሰሉ ቤተሰባዊ ሥራዎችን የምናከናውንበት ፕሮግራም መቅረጽ ይኖርብናል፤ ለምሳሌ፣ በየቀኑ ልብስ ማጠብ የለብንም፡፡ የግድ መሠራት ላለባቸው ሥራዎች ቅድሚያ በመስጠት፣ ቀሪዎቹን ለሌላ ጊዜ ማስተላለፍ እንችላለን፡፡

**•ዝርዝር ማዘጋጀት፡-** ከቤተሰባችን ጋር በጋራ ማከናወን ላለብን ነገር ሳምንታዊ፣ በሥራ ቦታችን እና መኖሪያ ቤታችን ውስጥ ለምንሠራው ሥራም ዕለታዊ መርሃ-ግብር ማጀጀት ይኖርብናል፡፡ በዕቅድ መመራት በነገሮች ላይ ትኩረት ለማድረግ ያግዘናል፡፡ በዕቅድ የማንመራ ከሆነ፣ በቀላሉ የሌሎች ሰዎች ዕቅድ ተገዢ እንሆናለን፡፡

**•'እምቢ' ማለትን መማር፡-** አንድ የሥራ ባልደረባችን ተጨማሪ ፕሮጀክት እንድንመራለት፣ አሊያም የልጃችን ትምህርት ቤት ርዕሰ-መምህር በአንድ ኮሚቴ ውስጥ እንድንታቀፍ ቢጠይቁን፣ በትሕትና 'የለም፣ አልችልም' የሚል ምላሽ መስጠቱ ችግር እንደሌለው ማወቅ ይኖርብናል፡፡ በይሉኝታ ወይም ለግዴታ ባለን የተሳሳተ ግንዛቤ ተሸብበን የተለያዩ ኃላፊነቶችን መቀበል ካቆምን፣ ለራሳችን ትርጉም በሚሰጡን ድርጊቶች የምናሳልፈው ተጨማሪ ጊዜ ይኖረናል፡፡

**•ሥራችንን አሥራ ቦታችን መተው፡-** በማንኛውም ቦታ ሆነን ከማንኛውም ሰው ጋር መገናኘት የሚያስችሉን ዘመናዊ ቴክኖሎጂ በእጃችን ውስጥ ባለበት በአሁኑ ዘመን፣ በሥራ እና በግል ሕይወት መካከል ያለው ወሰን ፍጹም ላይታወቅ ይችላል፤ ስለዚህም፣ ይህንኑ ወሰን ማበጀት ያለብን እኛው ራሳችን ነን፡፡ ሥራችን ከጊዜ አንጻር የግል ሕይወታችንን እንዳይሻማ ማድረግ ይኖርብናል፡፡

**•ለኢ-ሜይል አጠቃቀማችን ገደብ ማበጀት፡** - ኢ-ሜይላችንን መመልከት ያለብን በቀን ሦስት ጊዜ ብቻ፣ ማለትም ጠዋት፣ ከቀትር በኋላ እና አመሻሹ ላይ፣ ነው፡፡ ጠዋት ቁርሳችንን እንደበላን የኢ-ሜይል መልዕክቶቻችንን ከተመለከትን፣ ስለራሳችን ፍላጎት ከመጨነቅ ይልቅ የሌሎች ሰዎችን ጉዳይ ለመፍታት የመጣር አዝማሚያችን ከፍተኛ ይሆናል፡፡

**•አማራጮችን መጠቀም፡-** ከአሠሪያችን ጋር ስለተለዋዋጭ የሥራ ሰዓታት፣ ስለሥራ መጋራት፣ ስለተጨናነቀ የሥራ ሳምንት፣ ቴክኖሎጂ በመጠቀም ሥራን ስለማሳለጥ፣ እንዲሁም ስለሌሎች አማራጮች መነጋገሩ ጠቃሚ ነው፡፡ የሥራ ሰዓታችንን ይበልጥ በተቆጣጠርን ቁጥር፣ ለውጥረት ያለን ተጋላጭነት በዚያው መጠን ይቀንሳል፡፡

**•ብዙም አለመጨናነቅ እና ሥራን ሳያቋርጡ ማከናወን፡-** አብዛኞቻችን ከ90 ደቂቃዎች በላይ በአንድ ነገር ላይ ማተኮር አንችልም፡፡ ከዚህን ጊዜ በኋላ አንጎላችን መረጃ ይዞ የማስቀመጥ ዓቅሙ በከፍተኛ ሁኔታ ይቀንሳል፡፡ አንድን ሥራ እየሠራን እያለ በሆነ ምክንያት ለማቋረጥ ከተገደድን፣ ትኩረታችንን መልሰን በሥራው ላይ ለማድረግ ያቋረጥንበትን ያህል በሁለት ወይም በአራት እጥፍ የሚበልጥ ጊዜ ያስፈልገናል፡፡

ራስን መንከባከብ


ጤናማ የአኗኗር ዘይቤ ውጥረትን ለመቋቋም እና ሥራችንን ከግል ሕይወታችን ጋር ለማመጣጠን እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ ይህንንም ለማሳካት ቀጣዮቹን እርምጃዎች መውሰዱ ይመከራል፡-

**•ጤናማ የአመጋገብ ሥርዓት መከተል፡** - ለፍራፍሬ፣ ለአትክልት እና ለቀይ ሥጋ አጽንኦት የሚሰጠው የሜዲተራኒያን አካባቢ ሀገራት የአመጋገብ ሥርዓት፣ አንጎላችን በየጊዜው የሚቀርመውን መረጃ እንደያዘ እንዲዘልቅ፣ እንዲሁም ብርታት እና ጤንነት እንዲሰማን እጅጉን ያግዛል፡፡

**•በቂ እንቅልፍ መተኛት፡-** የእንቅልፍ እጦረት ውጥረትን ከፍ ያደርጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም፣ ኮምፒዩተር እና ተንቀሳቃሽ ስልክ የመሰሉ የኤሌክትሮኒክ መሣሪያዎችን ወደአልጋችን ከማምራታችን በፊት መጠቀም የለብንም፡፡ ከእነኝህ መሣሪያዎች የሚመነጨው ሰማያዊ ብርሃን ከእንቅልፍ ጋር ተያያዥነት ያለው ሜላቶኒን የተባለው ሆርሞን መጠን እንዲቀንስ ያደርጋል፡፡

**•ለመደሰት እና ለመዝናናት በቂ ጊዜ መመደብ፡** - በየቀኑ መጽሐፍ ማንበብ ወይም ፊልም መመልከት የመሰሉ የሚያስደስቱንን ነገሮች የምናከናውንበት በቂ ጊዜ እንዳለን ማረጋገጥ ይገባናል፡፡ ከዚህ በበለጠ ደግሞ፣

ወደ 21 ዞሯል




## ሙያዊ እገዛ የሚያስፈልገን መቼ ነው?

ማንኛችንም ብንሆን አልፎ አልፎ የሌሎች ሰዎች እገዛ ያስፈልገናል፡፡ አኗኗራችንን መቆጣጠሩ አስቸጋሪ ከሆነብን እና ስለዚሁ ጉዳይ በየጊዜው የምንጨነቅ ከሆነ፣ የሥነ-ልቦና አማካሪ ወይም ሌላ መሰል የጤና ባለሙያ ማነጋገር ይኖርብናል፡፡ አሠሪያችንን በዚህ ረገድ እገዛ የሚያደርግልን ከሆነ ደግሞ፣ ይህንኑ ለመቀበል ማቅማማት የለብንም፡፡

ያም ሆኖ፣ የሥራ እና የግል ጤንነታችንን ማመጣጠኑ እንዲሁ በቀላሉ የሚሳካ ውጥን አይደለም፡፡ ቤተሰባችን፣ ፍላጎታችን፣ እንዲሁም የሥራ ሕይወታችን በተለወጠ ቁጥር፣ የሥራ እና የግል ሕይወታችንን የማመጣጠኑ ተልዕኮም ቀጣይነት ያለው ሂደት መሆኑ አይቀርም፡፡ ስለዚህም፣ በሕይወታችን ቅድሚያ የምንሰጣቸውን ጉዳዮች በመመርመር ወይም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በመለወጥ፣ ከጭንቀት እና ከውጥረት የጸዳ ሕይወት ለመኖር መጣር አለብን፡፡

## ይህን ያውቁ ኖሯል?

- ከስንፈተ-ወሲብ መንሥኤዎች መካከል አንዱ አልኮል መጠጥ ማዘውተር ነው፡፡
- በየዕለቱ ከወገብ በታች በቀዝቃዛ ውኃ ውስጥ መዘፍዘፍ፣ በተለይ ለወንዶች፣ ለስንፈተ-ወሲብ ችግር መፍትሔ ሊያስገኝ ይችላል፡፡
- የሰው ልጅ አንገቱ ተቆርጦ ጭንቅላቱ ከወደቀ በኋላ ለ20 ሴኮንዶች ያህል አእምሮው በትክክል ይሠራል፡፡
- ዕርድ የተጨመረበትን ምግብ መመገብ ለካንሰር የሚኖረንን ተጋላጭነት ይቀንሳል፡፡
- ነጭ ሽንኩርት ለ200 ያህል ሕመሞች ፈውስ የሚሆኑ ቅመሞችን በውስጡ ይዟል፤ በሌላ በኩል፣ ማር፣ ወተት፣ አቮካዶ እና ጥቁር አዝሙድ ከፍተኛ የጤና ጠቀሜታ ካላቸው ተፈጥሯዊ የምግብ ዓይነቶች መካከል ይመደባሉ፡፡
- ቡና፣ ሽምብራ እና ሙዝ የነጭ ሽንኩርት ጠረንን ለመቀነስ የሚያግዙ የምግብ ዓይነቶች ናቸው፡፡
- ማር የድምፅ ውበትን ያስተካክላል፡፡
- ረኸም ተረከዝ ያለው ጫማ መጫማት የሴቶችን የወሲብ ሕይወት ያስተካክላል፡፡
- ሩሲያውያን ጥሬ ድንችን ቆራርጠው በማዘጋጀት፣ ለአህያ ኪንታሮት (ሄሞሮይድ) ፍቱን መድኃኒት ይቀምማሉ፡፡
- ከዐሥር ዓመታት በኋላ የዓለማችን ዋነኛ የጤና ችግር ይሆናሉ ተብለው በሳይንስ የተገመቱት ከትምባሆ ጋር ተያያዥነት ያላቸው የልብ፣ የሳምባ እና የደም ሥር ሕመሞች ናቸው፡፡

## የሸለብታ ጠቀሜታ

በእንቅልፍ ዙሪያ በርካታ ጥናቶች ያካሄዱት እንግሊዛዊው የላፍባሮው ዩኒቨርሲቲ ባልደረባ፣ ፕሮፌሰር ጂም ሆርንስ፣ ከሰዓታት በኋላ የሚሰማንን የመደበት ስሜት (ድባቴ) ለማጥፋት "ከዐሥር ደቂቃዎች ሸለብታ የሚበልጥ መድኃኒት እንደማይኖር" ተናግረዋል፡፡ ሆርንስ አያይዘውም፣ "ሸለብታ እንደማንኛውም ሕክምና ጥሩ ውጤት የሚያስገኘው ገና ችግሩ እንደጀመረ ሲወሰድ ነው" ብለዋል፡፡ በዩ.ኤስ. አሜሪካ የሚገኙ አንዳንድ ትላልቅ የንግድ ኩባንያዎች ሠራተኞቻቸው የሚያሸልቡባቸው አልጋዎች፣ ብርድ ልብሶች እና ትራሶች የተዘጋጁባቸው፣ እንዲሁም እንቅልፍ የሚያስወስዱ ሙዚቃዎች እና በየ20 ደቂቃዎች የማንቂያ ደወል ድምፅ የሚሰማባቸው ክፍሎች አዘጋጅተዋል፡፡ ይሁን እንጂ፣ ፕሮፌሰር ሆርንስ የእንቅልፉ ጊዜ ከረዘመ፣ ለምሳሌ ያህል፣ ለ25 ደቂቃዎች ከቆየ፣ ከእንቅልፋችን ስንነቃ የመጫጫን ስሜት ሊሰማን እንደሚችል አስጠንቅቀዋል፡፡ ከዐሥር ደቂቃዎች በላይ ከተኛን፣ ሰውነታችን የመሻሽ ይመስለው እና ሙሉው የእንቅልፍ ሂደት እንዲጀመር ያደርጋል፡፡

አዘጋጅ:- ማውሮ

## የዓለማችን አስገራሚ ሕጎች

- በዩ.ኤስ. አሜሪካ፣ ሮድ ዓይላንድ ደሴት በምትገኘው ፕሮቪደንስ ከተማ አንድም መደብር በቅዳሜ ዕለት የጥርስ ብሩሽ መሸጥ አይችልም፤ ይሁንና፣ እሑድ ቀን መሸጥ ይችላል::
- ከ1916 (እ.አ.አ.) ወዲህ በዩ.ኤስ. አሜሪካ ውስጥ አንድን ሙሉ ሕንጻ በፖስታ ቤት በኩል መላክ በሕግ የተከለከለ ሆኗል፤ በዚሁ ዓመት አንድ የዩታህ ግዛት ነዋሪ ለጭነት ተሸከርካሪ የሚያወጣውን ውድ ክፍያ ለማቀረት ሲል 40,000 ቶን የሚመዝን አንድ ከጡብ የተሠራ ቤት በፖስታ ቤት በኩል ወደሚፈልገው አድራሻ ልኮ ነበር::
- በሆንግ ኮንግ ሕግ መሠረት፣ ሚስት ባሏን ሲማግጥ ከያዘችው የመግደል መብት አላት፤ ግድያውን መፈጸም የምትችለው ግን፣ ምንም ዓይነት መሣሪያ ሳትጠቀም በእጇቿ ብቻ ነው::
- የሩሲያው ንጉሠ-ነገሥት፣ ታላቁ ጴጥሮስ፣ ወንዶችን የጺም ቀረጥ ያስከፍል ነበር::
- በዩ.ኤስ. አሜሪካ፣ ኔብራስካ ግዛት ማንኛውም ሰው ቤተ-ክርስቲያን ውስጥ እንዳያስነጥስ በሕግ የተከለከለ ነው::
- የጥንታዊት ሮም ዜጎች ፍርድ ቤት ቀርበው ቃል የሚሰጡት ወይም ቃለ-መሐላ የሚፈጽሙት የብልታቸውን ፍሬዎች በእጆቻቸው ይዘው ነበር::
- በ1386 (እ.አ.አ.) አንድ አሳማ የአንድን ሕፃን ልጅ ሕይወት በማጥፋቱ፣ በሕዝብ ፊት በስቅላት ተቀጥቷል::
- በሰሜን ኮሪያ ማንኛውም ዓይነት ሃይማኖት በመንግሥት የተከለከለ ነው::
- በሳውዲ ዐረቢያ ሕግ መሠረት፣ ሴቶች ከቤታቸው ውጭ በሆቴሎች ወይም በመዝናኛ ስፍራዎች ተገኝተው መዋኘት አይችሉም::
- በዩ.ኤስ. አሜሪካ፣ ኢሊኖይ ግዛት ጸጉር አስተካካዮች ጣቶቻቸውን ተጠቅመው የደንበኞቻቸውን ፊት የጺም ሳሙና መቀባት አይችሉም::

## የታወቀ የተፈጥሮ ጋዝ ክምችት (በሚሊዮን ሜትር ኩብ)

- ሩሲያ - 47,800,000
- ኢራን - 34,020,000
- ኳታር - 24530,000
- ዩ.ኤስ. አሜሪካ - 9,659,000
- ቬኔዙዌላ - 9,617,000
- ሳውዲ ዐረቢያ - 8,489,000
- የተባበሩት ዐረብ ኤሚሬቶች - 6,091,000
- ናይጄሪያ - 5,111,000
- አልጄሪያ - 4,504,000
- አውስትራሊያ - 3,500,000
- ኢራቅ - 3,158,000

(ምንጭ:- ስፔክታተር ኢንዴክስ)

## አስገራሚ አሟሟት

የስኮትላንድ ንጉሣዊ ቤተሰብ አባል የሆነው ምሁር፣ ቶማስ ኡርክ ኡሃርት፣ በ1660 (እ.አ.አ.) በጣም ያስገረመውን አንድ ዜና ይሰማል:: ዜናውም፣ "ዳግማዊ ቻርልስ የታላቋ ብሪታኒያ ንጉሥ ሆኑ" የሚል ነበር:: መስፍኑ ቶማስ ግን፣ በሁኔታው እጅጉን ከመገረሙ የተነሣ ለረዥም ሰዓታት እየተንተከተከ ሲስቅ ቆይቶ ድንገት ዓየር አጥሮ እስከወዲያኛው አሸለበ::

## ጥቂት ስለዩ.ኤስ. አሜሪካ ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ



- በ1789 (እ.አ.አ.) በዩ.ኤስ. አሜሪካ በተካሄደው የመጀመሪያው ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ ያሸነፉት ጆርጅ ዋሽንግተን ነበሩ፤ ይሁንና፣ ከ13ቱ ግዛቶች በምርጫው የተሳተፉት 10 ብቻ ነበሩ:: ኒው ዮርክ፣ ሰሜን ካሮላይና እና ሮድ ዓይላንድ ግዛቶች በምርጫው አልተሳተፉም::
- በዕድሜ አናጋፋው ፕሬዚዳንት በ69 ዓመት ዕድሜያቸው የተመረጡት ሮናልድ ሬገን ናቸው፤ በዕድሜ ትንሹ ፕሬዚዳንት ደግሞ፣ በ43 ዓመታቸው የተመረጡት ጆን ኤፍ፣ ኬኔዲ ናቸው::
- በመጀመሪያው ምርጫ አሸንፈው፣ በቀጣዩ ከተሸነፉ ከአራት ዓመታት በኋላ የተመረጡ ብቸኛው ፕሬዚዳንት፣ ግሮቨር ክሊቭላንድ ናቸው፤ በዚህም መሠረት፣ ክሊቭላንድ የዩ.ኤስ. አሜሪካ 22ኛው እና 24ኛው ፕሬዚዳንት ሆነዋል::
- ስድስት ጊዜ ለፕሬዚዳንትነት የተወዳደሩት ብቸኛው ዕጩ፣ የሶሻሊስት ፓርቲው ኖርማን ቶማስ ናቸው፤ ይሁንና፣ አንድም ጊዜ የመመረጥ ዕድል አላገኙም::
- በዩ.ኤስ. አሜሪካ ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ በዕጩዎቹ መካከል ለመጀመሪያው ጊዜ በቀጥታ የቴሌቪዥን ስርጭት የታየ ክርክር የተካሄደው መስከረም 26/1960 (እ.አ.አ.) በዴሞክራቲክ ፓርቲው ጆን ኤፍ. ኬኔዲ እና በሪፑብሊካን ፓርቲው ሪቻርድ ኤም. ኒክሰን መካከል ነበር::
- አንድ ዕጩ በፕሬዚዳንትነት ለመመረጥ ዕድሜው ቢያንስ 35 ዓመት፣ የዩ.ኤስ. አሜሪካ ዜግነት ያለው፣ እንዲሁም ቢያንስ ለ14 ዓመታት በዩ.ኤስ. አሜሪካ ውስጥ የኖረ መሆን አለበት::
- ፕሬዚዳንታዊው ምርጫ የሚካሄደው በኖቬምበር ወር ከመጀመሪያው ሰኞ ቀጥሎ በሚውለው ማክሰኞ ነው::
- ባለፉት አራት ዐሥርተ-ዓመታት የመራጮች ቁጥር ቀንሷል፤ በ1960ዎቹ ዓመታት ለመምረጥ ከተመዘገበው ሕዝብ 62% በምርጫው ሲሳተፍ፣ በ2000ዎቹ ዓመታት ይኸው አኃዝ ወደ 54% ዝቅ ብሏል::
- የ2008 (እ.አ.አ.) ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ ከ1928 (እ.አ.አ.) ወዲህ በሥልጣን ላይ ያሉት ፕሬዚዳንት እና ምክትል ፕሬዚዳንት ዳግም ያልተወዳደሩበት የመጀመሪያው ምርጫ ነው::
- አዲሱ ተመራጭ ፕሬዚዳንት ሥልጣናቸውን በይፋ የሚረከቡት ጃንዋሪ 20 ቀን በሚካሄድ በዓለ-ሲመት ነው፤ ከ1933 (እ.አ.አ.) በፊት ግን፣ በዓለ-ሲመቱ የሚካሄደው ማርች 4 ቀን ነበር::

## ለፈገግታ ያህል

በሥራ ምክንያት ራቅ ወዳለ ስፍራ የሚሄድ ባል ሚስቱን እየተሰናበታት እያለ፣ "የእኔ ውድ፣ ምናልባት ሥራው አላልቅ ብሎኝ ለዘመን መለወጫ በዓል ካልደረስኩ፣ 'የእንኳን አደረሰሽ' መልዕክት በቴሌግራም እልክልሻለሁ" ይላታል:: ሚስቱም ቀበል አድርጋ፣ "ግድ የለም፣ አትቸገር! በቴሌግራም ለመላክ ያሰብከውን መልዕክት ልብሶችህን ሳዘጋጅ ካፖርትህ ኪስ ውስጥ አግኝቼ አንብቤዋለሁ" አለችው::

***

ወጣቱ አፍቃሪ ፍቅረኛውን ጠልፎ አብረው ሊኰበልሉ ይስማማሉ:: ወጣቱ ጨለምለም ሲል መሰላል ቢጤ እልጅቷ መኝታ ክፍል መስኮት ሥር አስደግፎ ወጥቶ መስኮቷን ማንኳኳት ይጀምራል:: ፍቅረኛውም መስኮቷን ቀስ ብላ ስትከፍት፣ "ተዘጋጅተሻል?" ብሎ ጠየቃት:: ፍቅረኛውም፣ "ሽ...ሽ...ሽ... አትጮኽ! አባዬ ከሰማ፣ ተያዝን ማለት ነው" ብላ ታንሾካሹካለች:: ይህን ጊዜ ወጣቱ አፍቃሪዋ፣ "ግድ የለሽም፣ መሰላሉን ከታች የያዙልኝ እሳቸው ናቸው'ኮ" አላት::

***

ቶም:- ባለትዳር ወንድ እንዴት ያለ ጉበዝ የሸያጭ ሠራተኛ ይወጣዋል መሰለህ::
ጆን:- እንዴት እባክህ?
ቶም:- ትእዛዝ መቀበልን ለምዶታላ!

## ይህን ያውቁ ኖሯል?

- አንዲት ሴት በቀን 7,000 ያህል ቃላትን ስትናገር፣ አንድ አማካይ ወንድ በቀን ውስጥ ከአንደበቱ የሚያወጣው 2,000 ያህል ቃላትን ነው::
- የዩ.ኤስ. አሜሪካ የሕዝብ ቆጠራ ቢሮ ባወጣው መረጃ መሠረት፣ በሰሜን ዳኮታ ግዛት ውስጥ ከ1 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር በላይ የሚያወጣ መኖሪያ ቤት የለም::
- የሚኔሶታ ዩኒቨርሲቲ ከሚኔሶታ ግዛት በዕድሜ ያበልጣል::
- አንድን ሮልስ ሮይስ መኪና ለመሥራት ስድስት ወራትን ይወስዳል፤ በአንጻሩ፣ አንድ ቶዮታ መኪና የሚመረተው በ13 ሰዓታት ውስጥ ነው::
- ጠፈርተኞች ሕዋ ውስጥ ማግሣት አይችሉም::
- ብራዚል ውስጥ 5 ሚሊዮን ሕዝብ በቡና ኢንዱስትሪው ዘርፍ ተቀጥሮ ይሠራል::
- አንድ አባጨጓሬ ጭንቅላቱ ውስጥ 248 ጡንቻዎች አሉት::
- በፈረንሳይ ርዕሰ-ከተማ፣ ፓሪስ፣ የሚገኘው ኤፌል ማማ ቁመት ወይም ከፍታ ከ300 ሜትር (984 ጫማ) ይበልጣል::
- ፕሮፌሽናል የባሌ ዳንሰኞች በሳምንት 12 ያህል ጥንድ የዳንስ ጫማዎችን ይጨርሳሉ::
- የማሌዢያ ርዕሰ-ከተማ፣ ኩዋላ ላምፑር፣ ትርጉም "ጭቃማ ወንዝ" ማለት ነው::

## ቃላት አልባ የደብዳቤ ልውውጥ

የፈረንሳይ "የሮማንቲሲዝም የሥነ-ጽሑፍ ዘርፍ አባት" ተደርጎ የሚወሰደው ቪክቶር ሁጎ (1802-1885 እ.አ.አ.)፣ ግጥሞችን፣ ተውኔቶችን፣ ፖቲካዊ ምጸቶችን፣ እንዲሁም ልብ ወለዶችን ጨምሮ የተለያዩ የሥነ-ጽሑፍ ሥራዎችን ለአንባቢያን አበርክቷል:: ከትላልቆቹ ሥራዎች መካከል 'ኖትር ዳም ደ ፓሪ' እና 'ሌ ሚሴራብል' የተባሉት ልብ ወለዶቹ ተጠቃሾች ናቸው:: ታዲያ፣ የኋለኛ ሥራውን በተመለከተ፣ ደራሲው መጽሐፉ ከታተመ በኋላ በአንባቢያን ዘንድ ያለውን ተቀባይነት ለማወቅ ይጓጓል:: ስለዚህም፣ ለመጽሐፉ አርታኢ የጥያቄ ምልክት ብቻ የሰፈረበትን ደብዳቤ ይልክለታል:: አርታኢውም መጽሐፉ ከስኬታሞቹ ተርታ እንደሚመደብ ሲገልጽለት፣ የቃለ-አጋኖ ምልክት ብቻ የያዘ ደብዳቤ መልሶ ላከለት::

## የአምባገነንነት ጫፍ

ከአፍሪቃ አምባገነን መሪዎች መካከል አንዱ በ1970 ዓመታት የኮሞሮ ደሴቶች ወጣቱ ርዕሰ-ብሔር፣ አሊ ሶሊህ፣ ነበር:: አሊ ሶሊህ ምሽቱን በአብዛኛው የሚያሳልፈው በሀገሪቱ ምርጥ ቆነጃጅት እንደታጀበ በየጭፈራ ቤቶች በመዘዋወር ነበር:: ከአምባነገኑ መሪ በርካታ አስገራሚ ታሪኮች መካከል በብዙዎች ዘንድ ትኩረትን የሳበው ቀጣዩ ገጠመኝ ነው::

አሊ ሶሊህ አንድ ሌሊት በሕልሙ አንድ ውሻ እያሳደደ ሲነክሰው ያያል:: በነጋታው ከእንቅልፉ ሲነቃ ሌሊት ባየው ሕልም ሳቢያ በሀገሪቷ የሚገኙ ውሾች በሙሉ እንዲገደሉ ትእዛዝ ይሰጣል:: አብዛኛው የሀገሪቱ ሕዝብም ይፈራው ስለነበር፣ እንደታዘዘው ውሾቹን ጨክኖ ገደላቸው::

ታዲያ፣ አሊ ሶሊህ ቃሉ ምን ያህል እንደተከበረ ለማረጋገጥ በርዕሰ-ከተማው አውራ ጐዳናዎች ሲዘዋወር፣ አንዲት ባልቴት ግቢ ውስጥ አንድ ውሻ ታስሮ ይመለከታል:: በዚህን ጊዜ፣ አሊ ሶሊህ የታጠቀውን ሽጉጥ ይመዝና ውሻውን ተኩሶ ከገደለው በኋላ ባልቴቷን ወደዘብጥያ በመላክ፣ የለየለት አምባገነን እንደሆነ አስመሰከሯል::

## የመዝገበ-ቃላት ዝግጅት

በብዙዎች ዘንድ የሚታወቀውን የእንግሊዝኛ ቋንቋ መዝገበ-ቃላት ያዘጋጀው እንግሊዛዊው ደራሲ፣ ሳሙኤል ጆንሰን፣ በአንድ ወቅት አንድ ግለሰብ ይህንኑ መዝገበ-ቃላት እንዴት ሊያዘጋጀው እንደቻለ ይጠይቀዋል:: ጆንሰንም ፈገግ ብሎ፣ "ምን መሰለህ፣ ከሚስቴ ጋር ከመጨቃጨቅ ብዙም የተለየ ነገር የለውም:: አንዱ ቃል ሁሌ ወደሌላኛው ይመራኝ ነበር" የሚል ምላሽ ሰጠው::

## እርስዎም ይሞክሩት ጥያቄ

1. የካናዳ የመጀመሪያ ጠቅላይ ሚኒስትር ማን ናቸው?
2. የጃፓን ከፍተኛ ተራራ ምን ተብሎ ይጠራል?
3. ከ2010-13 (እ.አ.አ.) የዓለማችን ቁጥር አንድ ባለጸጋ ማን ነበር?
4. በቬኔዙዌላ እና በሱሪናም መካከል ያለችው ሀገር ማን ናት?
5. የኒያሲን እጥረት በሰውነታችን ላይ ምን ዓይነት በሽታ ያስከትላል?

መልሱን በገጽ 21 ይመልከቱ

# የብሄር ፌደራሊዝም ካለ የብሄር...

ከገጽ 6 የዞረ

"Like much of Africa, Ethiopia is at a crossroads. Neither the centralized republic instituted by the Derg military junta in 1974 nor the ethnic federalism of Mr. Zenawi's 1994 Constitution points to a way forward. Mr. Abiy can achieve real progress if Ethiopia embraces a different kind of federation — territorial and not ethnic — where rights in a federal unit are dispensed not on the basis of ethnicity but on residence.

እንደ ብዙ የአፍሪካ ሀገራት፣ ኢትዮጵያ መንታ መንገድ ላይ ትገኛለች:: የደርግ አህዳዊ መንግስትም ሆነ፣ የመለስ ዜናዊ የብሄር ፌደራሊዝም የሚያዋጡ አይደሉም:: ጠ/ሚ/ር ዐቢይ ሀገሪቷን ወደ ዲት ይዘው መሄድ ከፈለጉ፣ ፊታቸውን ወደአዲስ ዓይነት ፌድራሊዝም በማዞር፣ የመብትን መሰረት በብሄር ሳይሆን በዜግነት ላይ ጥለው፣ አስተዳደራዊ (territorial) ፌደሬሽን ተግባራዊ ማድረግ አለባቸው::

ይህንን አቅጣጫ ተገንዝቦ ለውጡ ስር እንዲሰድ ማድረግ የተቀደሰና የተከበረ ዓላማ ነው።

## የሚያሳፍር የወገኖቻችን ሰቆቃ

የፌደራሉ መንግሥት የዜጎችን ሰብአዊ ክብርና መብት የመጠበቅ ሃላፊነት አለበት። ይህ ወገንተኝነትንና አድልዎን ከመቅረፍ አንጻር መታየት ያለበት አደራ ስለሆነ፣ "ህወሓትን ከሥልጣን አውርደናል" የሚሉ ኃይሎችና ክፍሎች ትግሉ ገና የተጀመረ እንጅ ያልተፈጸመ መሆኑን ማወቅ አለባቸው:: "የማንኛውም ኢትዮጵያዊ ደም ደማችን ነው" ወደሚባልበት ደረጃ መሸጋገር አለብን። ትላንት፣ "የሕግ የበላይነት ይከበር" እያሉ ይጮሁ የነበሩ ኃይሎች፣ "እርስ በርስ መጠፋፋት የሕግ የበላይነት ጥሰት ነው" ብለው መናገር ያለባቸው ዛሬ ነው።

በዚህ ገፅ ላይ የሚታየው ህጻን፣ መለያው ሰብእነትና ኢትዮጵያዊነት ነው፤ ብሄር አይደለም። የእኔ ወይንም የአንተ፣ ወይንም የአንች ልጅ፣ ወይንም የልጅ ልጅ ልጅ ሊሆን ይችላል። እሱን አይቶ የማያለቅስ ሰው የሚኖር አይመስለኝም። መጠፋፋት ማንንም አይጠቅምም፤ መጠፋፋት ዝቅ አድርጎናል።

ኢትዮጵያዊነት ማለት ለዚህ ሕጻን ድምጽ ማሰማት ነው። ሰብአዊ መብት ዘውግ፤ ኃይማኖት፤ ጾታ ወይንም እድሜ አይለይም።

ብሄር ተኮር ግጭት ምን መሆኑን ለመረዳት በንጹህ ወገኖቻችን ላይ የሚደርሰውን እልቂት፤ ረሃብና ሌላ ሰቆቃ ማጤን ይበቃል። ሀገራችንን እንወዳለን ስንል፣ ሕዝቧንም እንወዳለን ማለት መሆን አለበት። ኢትዮጵያን እንወዳለን ስንል፣ አንድነቷንና ሉዐላዊነቷን ማስቀደም ማለት ነው። ጥቅም ወዳድ ሆነን ሀገር ወዳድ ለመሆን አንችልም።

## እራሳችንንና ህሊናችንን እንመርምር

"በብሄር ተኮሩ ሕገ መንግሥትና በክልል አወቃቀሩ ላይ መደራደር አይቻልም" በማለት ህወሓትና ኦዴፓ ተመሳሳይ አቋም እያራመዱ ይገኛሉ። ዋናው የለውጥ ትኩረት የስነ-ምግባር፤ የባህርይና የፖለቲካ ባህል ለውጥ መሆን ይገባዋል። ዘውግ ተኮር ባህርያችን ገደሉ ጫፍ ስላደረሰን፤ ልንፋታው ይገባል (Let us park our dysfunctional behavior at the edge of the cliff) ::

የጌድዮን፤ የጎንደርን፤ የኦሮሞን፤ የሶማሌን፤ የለገጣፎን፤ የቡራዩን ወዘተ እናቶችና ህጻናት የኑሮ ሁኔታ አይተን ራሳችንና ህሊናችን እንመራመር፤ የማይካደው ሃቅ አንድ ነው። ብሄር ላይ ተተክለን፤ ኢትዮጵያን ዝቅ እያደረግናት ነው። መጀመሪያ በኢትዮጵያ ብሄራዊ አንደነት ላይ ተመሳሳይ እምነት ይኑረን። ኢትዮጵያን በአንድነት ሆኖ ከመገንባት ውጭ ሌላ አማራጭ የለንም።

ችግሩ የፌደራል ስርዓት አይደለም፤ ዓይነቱ ነው:: በምን መሰረት ላይ ቢቆም ይሻላል? ነው ጥያቄው:: ፌድራሊዝም የተለያዩ ሞዴሎች አሉት። ብሄር ተኮር ፌደራሊዝም ግጭት ፈጣሪ ነው፤ እንደ ዩጎዝላቪያና ሶቭየት ህብረትን የመሳሰሉ ሀገራትን በታትኗል፤ የእኛንም ጫፍ አድርሷታል፤ ሶስት ሚሊየን ወገኖቻችን የተፈናቀሉት በብሄር ፌደራሊዝም ጣጣ ነው:: ከረሃብም ነፃ ያልወጣነው፣ ብሄር ያጣመመውን ፖለቲካ ማቃናት ተስኖን ነው:: የብሄር ፌደራሊዝም የብሄር ፖለቲካ ማህፀን ነው፤ ከብሄር ፌደራሊዝም ሳንላቀቅ ከብሄር ፖለቲካ መፋታት አንችልም::

## "ተፎካካሪ ፓርቲዎች"

"ተፎካካሪ ፓርቲዎች" በእነዚህና በሌሎች አስኳል ብሄራዊ ጉዳዮች ላይ ምን አይነት አቋም ወሰዱ? ችግሩን ለምን ይፈሩታል፤ ማንንስ ይፈራሉ? ችግሮችን ፈርተው ወይንም ሸሽተው፣ "ተፎካካሪ" ሊሆኑ አይችሉም።

የፖለቲካ ምሁራንና ልሂቃን ባለፉት 28 ዓመታት የተካሄደውንና አሁንም የሚካሄደውን ዘውግ ተኮር እልቂት፤ ስደት፤ የሀብት ውድመት፤ ሌብነት፤ የሶስት ሚሊየን ሕዝብ ፍልሰትና ሌላ የተያያዘ ቀውስ ምንጭ (Root, systemic and structural causes) አላጤኑትም ማለት ነው፤ በዐይን የሚታየው ሃቅ አለ፤ ለምሳሌ፣ በጎንደር ብቻ 90,000 ሕዝብ በጠለላ ይኖራል። በጌድዮ በብዙ መቶ ሽህ የሚገመት ሕዝብ በረሃብ ይሰቃያል። ይህ ሁሉ ሰው ሰራሽ ነው፤ ከብሄር ተኮር ፖለቲካ ጋር የተያያዘ ክስተት ነው።

ብሄር ተኮር አመለካከትና የፖለቲካ አደረጃጀት ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል። የሚያዋጣው በማንኛውም ዓለም የሚሰራው በዜግነት ላይ የተመሰርተ ፌደራሊዝም ነው።

## አዲስ አበባን በሚመለከት

የዘውግ ፖለቲካንና አደረጃጀትን የሚደግፉ ኃይሎች፤ በተለይ ጽንፈኞችና ጠባብ ብሄርተኞች የሚያራምዱት ፍልስፍና፣ "እኛ ኢትዮጵያዊያን" የሚለውን ሳይሆን፤ "ኬኛ ኦሮሞ" የሚለውን የአንድ ቋንቋ ተኮር አስተሳሰብ ነው። "አዲስ አበባ የሁላችንም ናት" በሚለው ሁሉን አቀፍ እይታ ፋንታ፣ "ፊንፊኔ ኬኛ" በሚል እየተስተጋባ የሚገኘው የጠባቦች ጩኸት፣ አምስት ሚሊየን የሚሆኑት የአዲስ አበባ ህብረ-ብሄራዊ ነዋሪዎች፣ የባለቤትነት መብት የላቸውም፤ "መጤዎች" ናቸው የሚል ነው። እውነት ለመናገር፣ ይሄ አባባል ቅዠት ነው፤ እርባና የለውም:: ይህም ሆኖ ግን፣ ስሜት ኮርኳሪ ነውና፣ በንቀት ሊታለፍ አይችልም::በአደጉ ሀገራት እንኳን እንደዚህ ዓይነት ቅዠቶች ብዙ ሰዎችን ያሳስታሉ:: ድህነት ባለባት ሀገራችን አንድምታው ይበልጥ ቢሆን፣ ብዙም ሊያስገርም አይችልም::

አዲስ አበባ የሁሉም ኢትዮጵያዊያን ከተማ ናት። በተጨማሪም፤ ይህች ከተማ የአፍሪካም መዲና ናት:: የብዙ ዓለም አቀፍ ተቋማትና የዲፕሎማሲ ማዕከል ናት፤ ከኒውዮርክና ጀኔቭ ቀጥሎ የተባበሩት መንግስታት ዋና መከተሚያ ናት፤ ታላቋን ከተማ ዝቅ አናድጋት። አዲስ አበባን ዝቅ ማድረግ፣ ኢትዮጵያንና ትላቁን የኢትዮጵያን ሕዝብ ዝቅ ከማድረግም ባሻገር አፍሪቃንም ወደታች መጎተት ነው:: አዲስ አበባን ለአንድ ማህበረሰብ ሳይሆን ለአፍሪቃ የምትመጥን ከተማ እናድርጋት፤ ዓለም እኮ እየታዘበን ነው::

አዲስ አበባና ሌሎች ከተማዎች በዘውግ አጥር ተከልለዋል ከተባለ ብልጽግና፤ ዘመናዊነትና ህብረ-ብሄራዊነት ሊያብቡ አይችሉም። ከተሜነት ከዘመናዊ እድገት ጋር ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት አለው። ከተሜነት ማንኛውም ሰው የሚኖርበት፤ ቤትና ንብረት የሚያፈራበት ቦታ ማለት ነው። ከተሜነት ነፃ መንፈስ ይጠይቃል፤ በሩን ለሁሉም የከፈተ፣ ሁሉንም እኩል የሚያስተናግድ፣ የነዋሪው ብዛት እንዲጨምር የሚመኝ የማህበራዊ፣ የኢኮኖሚያዊና የፖለቲካ አየር ይፈልጋል:: እንዴት "በኬኛ" ቅኝት መንድርተኝነትን ለአዲስ አበባ እንመኝላታለን? የአዲስ አበባ የኋልዮሽ ጉዞ የኦሮሞን ህዝብ ከቶ ሊጠቅመው አይችልም:: እንዲያውም በተቃራኒው፣ አዲስ አበባ ለኦሮሞ ህዝብ መድመቂያው ነች፤ ለሁሉም ኢትዮጵያዊ መድመቂያ እንደሆነችው ሁሉ:: የኦሮሞና የአዲስ አበባ ደህንነት የአንድ ሳንቲም ሁለት ግልባጮች ናቸው፤ በከተማዋ ዙሪያ ያሉ ገበሬዎችም፣ የሚደመረው ተደምሮና የሚቀነሰው ተቀንሶ፣ በአዲስ አበባ መኖር ተጠቅመዋል እንጂ አልተጎዱም::

# የአንድ ዓመት አስተዳደርና...

ከገጽ 5 የዞረ

ሐውልት የሚያስቆም ዕድል አያምልጥዎ።

በሥልጣን ላይ ያሉትን የፖለቲካ ፓርቲዎች አባላትን ከጎሰኝነት ርእዮተ ዓለም ወደ ዲሞክራሲ ርእዮተ ዓለም ለመለወጥ የታሰበው ይቅር፥ ይሰረዝ። አባላቱ በጎሰኝነት ነፍረዋል። የነፈረ እህል ለዘር አይሆንም።ርእዮተ ዓለም እንደ ሃይማኖት ነው። አጋጣሚውን ተጠቅሞና ጥቅሙን አይቶ ሃይማኖቱንም ሆነ ርእዮተ ዓለሙን የሚለውጠውን ሰው አናምነውም። እውነት መለወጡን የምናውቀው ተወዳድሮ አሸንፎ ሲመጣ ነው። የፓርቲ አሰላለፍ እንደ ቸዝ ጨዋታ አንዴ ጥቁሩን አንዴ ደግሞ ነጩን ይዞ የሚጋጠሙት አይደለም። በፓርቲ ደረጃ፥ ሁሉም ወይ ጥቁር ወይ ነጭ ነው።

## አዲስ አበባ፤

የአዲስ አበባ ጉዳይ ዶክተር ዐቢይን ማስቆጣቱ መሪያችን ለትውልድ ፓርቲያቸው ማዳላታቸውን ያጋልጣል፤ እኛንም በሳቸው ላይ ያለንን እምነት ያናጋብናል። የኦሮሞች ትግል አዲስ አበባ የኛ ናት ማለታቸው፥ የመንግሥቱ ከተማ አትሁን፥ የአፍሪካ ከተማ አትሁን፥ የዓለም-አቀፍ ከተማ አትሁን ማለታቸው ሳይሆን፥ በከተማም ሆነ በአገር ቤት፥ ለኦሮሞዎች በተሰጠው ክልል ውስጥ የሚኖረው ሕዝብ ኦሮሞ ብቻ፥ ግፋ ቢል ጥገኛ ንኡሳን ጎሳዎች የሚኖሩባቸው ይሆኑ ማለታቸው ነው። ኢትዮጵያን በክልል መከፋፈልን አንቀበልም። ያም ሆኖ አዲስ አበባ አንድ ክልል እንዳትሆን ለመከልከል በቂ ምክንያት የለም። አቶ ለማ መገርሳም ቢሆኑ፥ ኦሮሞዎችን አዲስ አበባ አሰፈርኳቸው እንጂ የአዲስ አበባን ዲሞግራፊ እቀይራለሁ አላልኩም ያሉት ልዩነቱ ቃልና ግብር መሆኑን ልብ ይበሉት። እየዛቱ መሥራትና ሳይዝቱ መሥራት ውጤታቸው አንድ ነው። በኦሮምኛ የተናገሩትና አሁን በአማርኛ የደገሙት አንድ ነው። የተናገሩበትም አንድ የኦሮሞ ሰው ለጠየቀዎ ጥያቄ መልስ ለመስጠት መሆኑም ልዩነት አያመጣም።

የኦሮሞ ገበሬ ጥቅም ተነካ፤ የወንዛችንን ውሐ የአዲስ አበባ ሕዝብ በነፃ ጠጣብን የሚሉት ሰበብ ነው። የወንዝ ውሐ ባለቤት ወንዙ በሚያልፍበት ምድር የሚኖረው ሕዝብ ሁሉ ነው። ወንዞቹ በአዲስ አበባ ሲያልፉ፥ የወንዞቹ ባለቤቶች አዲስ አበቦች ናቸው። በአዲስ አበባና ለኦሮሞ በተሰጠው ክልል የሚያልፍ ወንዝ ውሐውን ይዞ ሄዶ ከሌላ ክልል ሲያፈሰው፥ ኦሮሞዎች እዚያ ሄደው ሊያስገብሩ መብት የላቸውም። አንድ አስተዋይ (አቻም የለህ ታምሩ ይመስለኛል) ዓባይ፥ ጊቤ፥ ዋቢ ሸበሊ . . . ኢትዮጵያ ውስጥ እስከፈሰሱ ድረስ የመላ ኢትዮጵያ ሕዝብ እንጂ የተወሰነ ሕዝብ መብቶች አይደሉም። እነዚህ ወንዞች ኦሮሞዎች ከሰፈሩበት ቦታ ሲደርሱ፥ ለተነሡበት አገር ኦሮሞዎች ቀረጥ ይክፈሉ አይባሉም። አዲስ አበባ ላይ የኦሮሞ ሕዝብ ጥቅም ይከበር ማለት የኢትዮጵያን መከፋፈል ማጽደቅ ነው። ክቡር ዶክተር ዐቢይ፥ እባክዎ ራእዮን የሚያስከብረውን ወገን አያግልሉ። ከቀን ጅብ እንዳዳኑን ከሌሊት ጅብ ያድኑን።

ሽግግሩ ከወያኔ አገዛዝ ወደ ኦነግ አገዛዝ እንዳይሆን በጎሳቸው ምክንያት የሚፈናቀሉትን ይጠብቋቸው። ኦሮሞዎች ኦሮሞ ያልሆኑትን ሲያፈናቀሉ እያየን፥ "የኦሮሞ ሕዝብ አቃፊ ነው" ማለት ሽንገላ እንደሚመስል ጠቅላይ ሚንስቴሩ አይስቱትም። የኢትዮጵያ መሪ እስከሆኑ ድረስ ተፈናቃዮቹም መንጋዎችዎ ናቸው። ዱርየዎችን ለመቈጣጠር ሁኔታው የማይፈቅድልዎ ከሆነ፥ ራሳቸውን እንዲከላከሉ አስታጥቋቸው። የታጠቀን ሕዝብ ዱርየ አይደፍረውም። መንግሥት ፖሊስን የሚያስታጥቀው ሕዝቡን ከዱርየዎች ወንጀል ለማዳን ነው።

# አሜሪካ የአፍሪቃ ቀንድ ...

ከገጽ 16 የዞረ

ምሥራቅ የሚገኙ 70 ሀገራትን በመንገድ እና በባሕር የንግድ መሥመሮች ለማስተሳሰር አቅዳለች::

የዩ.ኤስ. አሜሪካ ፕሬዚዳንት ትራምፕ አስተዳደር ባለፈው ታኅሣሥ ወር ለአፍሪቃ የነደፈውን አዲስ እስትራቴጂ ይፋ ባደረገበት ወቅት፣ የብሔራዊ ጸጥታ አማካሪው፣ ጆን ቦልተን፣ ዕቅዱ ቻይና በአህጉሪቷ ያላትን እንቅስቃሴ እና ይዞታ ማዕከል ያደረገ እንደሆነ ሲያስረዱ፣ "በተለይም፣ ቻይና እና ሩሲያ የመሰሉ ኃያላን ተፎካካሪዎቻችን፣ በአፍሪቃ ያላቸውን የፋይናንስ እና የፖለቲካ ተጽዕኗቸውን በፍጥነት እያስፋፉ እና እያጠናከሩ ነው:: ሆን ብለው መዋዕለ-ንዋያቸውን በአህጉሪቷ ላይ እያፈሰሱ ያሉትም፣ ዩ.ኤስ. አሜሪካ በክልሉ ያላትን የበላይነት ለመንጠቅ ነው" ብለዋል::

ጂቡቲ የቻይና የመጀመሪያው የቻይና የባሕር ማዶ ወታደራዊ የጦር ሰፈር ያለባት ሀገር ብቻ ሳትሆን፣ ከኢትዮጵያ ጋር የሚያገናኛት የባቡር መሥመርም አላት:: በአብዛኛው በቻይና መንግሥት ድጋፍ የተገነባው ይኸው የባቡር መሥመር፣ ቀደም ሲል የተገለጸው ቻይና በአፍሪቃ፣ በእስያ እና በመካከለኛው ምሥራቅ የሚገኙ 70 ሀገራትን ለማስተሳሰር የዘረጋችው Belt and Road Initiative ውጥን አንድ አነስተኛ አካል ነው::

ይሁን እንጂ፣ የአፍሪቃ አህጉርን በሚመለከቱ ፖሊሲዎች ዙሪያ የሠሩ አንድ አንጋፋ የቀድሞ ዋሽንግተን ባለሥልጣን እንደሚሉት፣ ዩ.ኤስ. አሜሪካ ጂቡቲ የሚገኘውን ሌሞኒዬር ወታደራዊ የጦር ሰፈርን በሶማሊያ ካለው ባሌዶግሌ የጦር ሰፈር ጋር ለማስተሳሰር ልትገነባው ስላቀደችው አዲስ የሎጂስቲክስ አቅርቦት መሥመር ሲናገሩ፣ "ፕሮጀክቱ ቻይና በአካባቢው ካላት ተጽዕኖ ጋር የተያያዘ ሳይሆን፣ ዩ.ኤስ. አሜሪካ ለረዥም ዓመታት በክልሉ ካላት ወታደራዊ እንቅስቃሴ ጋር የተሳሰረ እና የሎጂስቲክስ አቅርቦትን ግምት ውስጥ ያስገባ ሳይሆን አይቀርም" ብለዋል::

በደቡብ አፍሪቃ፣ ኬፕ ታውን ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካ ሳይንስ የክብር ፕሮፌሰሩ፣ ሮበርት ሽሪሬ፣ የዋሽንግተን አስተዳደር ቻይና በክልሉ እያደረገች ያለው እንቅስቃሴ ቢያሳስበውም፣ ዩ.ኤስ. አሜሪካ በአፍሪቃ አህጉር የምትገነባቸው የመሠረተ-ልማት ፕሮጄክቶች ሁሌ የፀረ-ሽብር ዘመቻዎችን እና የደኅንነት ሥጋቶችን ማዕከል ያደረጉ እንደሆኑ ተናግረዋል:: የኬፕ ታውን ዩኒቨርሲቲው የክብር ፕሮፌሰር ሽሪሬ፣ "አሜሪካ አፍሪቃ ውስጥ በምንም መልኩ ከቻይና ጋር ልትፎካከር አትችልም:: ዩ.ኤስ. አሜሪካ ከቻይና ጋር በሚኖራት ፉክክር፣ አፍሪቃ ውስጥ የምታፈሰው መዋዕለ-ንዋይ እዚህ ግባ የሚባል አይሆንም" ብለዋል::

# ቦይንግ በፍርድ ቤት ሙሉ ኃላፊነት...

ከገጽ 15 የዞረ

ይህን የሚሉት ከጠበቆቻቸው፣ ከሕዝብ ግንኙነቶቻቸውና ከመሳሰሉ ጋር ተማክረው ነው:: በደንብ ተጠንታ የቀረበች፣ "ብቻዬን የሚያስጠይቀኝ አይደለም" ለማለት ታስባ የተቀየሰች ስልት ነች። እኔ እስከማምንበት ድረስ ግን፣ ቦይንግ ሙሉ ኃላፊነት ነው መውሰድ ያለበት:: በፍርድ ቤት ሙሉ ኃላፊነት እንዲወስድ መደረግ አለበት:: ይህ እንዲሆን የህጉን አካሄድ፣ የአሜሪካንን የፍትህ ስርዓትና ቦይንግ በአውሮፕላኑ አመራረት ላይ የፈፀማቸውን ስህተቶች በዝርዝር አቅርቦ መሞገት ያስፈልጋል::

**ኢትዮጲስ፡- እርስዎ ይህን ጉዳይ በጥብቅና ቢይዙት ውጤቱ ምን ይሆናል ብለው ይገምታሉ?**

**ዶ/ር ሼክስፒር፡-** ቀደም ብዬ እንደገለፅኩት፣ ጉዳዩን ይዤ ሀገሬንና ወገኖቼን ብረዳ ደስ ይለኛል:: ኩባንያው የሰራው ሥራ እጅግ ስሜቴን እንደነካውና፣ ለወደፊቱም እራሱን ከተጠያቂነት ለመከላከል ይሄድበታል ብዬ የማስበዉ መንገድ ስለሚያስጋኝ፣ ብይዘው ደስ ይለኛል::

የህግ ክርክርን ውጤት አስቀድሞ መገመት ቢያስቸግርም፣ መሰል ጉዳዮች ላይ ስለሰራሁና ባልደረቦቼም በዓለም አቀፍ ደረጃ አንቱ የተባሉ ስለሆኑ፣ ስለ ጉዳዩም በቂ ጥናት ስላለን፣ ኩባንያውን ሙሉ በሙሉ ተጠያቂ በማድረግ ፍትህ እናስገኛለን ብዬ አምናለሁ:: የወገኖቼን ጉዳይ ከምንም ነገር በላይ አስበልጬ ነው የማየው:: እነዚያ ህይወታቸውን ያጡ ወገኖቼ ህይወታቸው ተመልሶ ባይገኝም፣ ለህልፈታቸው ምክንያት የሆነው አካል በጥፋቱ ልክ ቅጣቱን ማግኘት አለበት::

**ኢትዮጲስ፡- አንዳንድ በአውሮፕላኑ አደጋ ህይታቸውን ያጡ የውጭ ሀገር ዜጎች የኢትዮጲያ አየር መንገድንም ጭምር ለመክሰስ መዘጋጀታቸውን እየገለፁ ነው : : አየር መንገዱን የሚያስከስሰው የህግ መሠረት አለ?**

**ዶ/ር ሼክስፒር፡-** ይሄም ጥያቄ መሠረታዊ ነው:: ኢትዮጲያ አየር መንገድ የሞንትሪያል ስምምነትን ፈርሟል:: በዚያ ስምምነት መሠረት፣ በአውሮፕላን አደጋ ለሞተ ሰው፣ ምክንያቱ ምንም ሆነ ምን፣ 170000 ዶላር ይከፍላል:: ለዚህ ሊከሰስ ይችላል:: ባይከሰስ ደስ ይለኛል፤ ህጉ ግን ያንን ነው የሚለው:: አየር መንገዱ ግን ለደረሰበት ኪሳራ፣ ለገፅታው መበላሸትና ለመሳሰሉት ቦይንግን መጠየቅ ይገባዋል:: ነገር ግን፣ ቦይንግ ኩባንያ እኮ "ቼን ኦፍ ኢቨንት" በሚለው ሰበቡ፣ አየር መንገዱንም ተጠያቂ ለማድረግ ሊሞክር ይችላል:: ይህን ነው መመከት የሚገባው::

**ኢትዮጲስ፡- የክስ ሂደቱ የት ቢታይ ለእኛ የተሻለ ይሆናል?**

**ዶ/ር ሼክስፒር፡-** አንዱ በጥንቃቄ ልንወስነው የሚገባው ጉዳይ ይሄ ነው:: ቦይንግ አውሮፕላኑ የተከሰከሰው ኢትዮጲያ ውስጥ ስለሆነና፣ አብዛኞቹ የተጎጂ ቤተሰቦች ኢትዮጲያ ስለሚኖሩ፣ በኢትዮጲያ ህግና ኢትዮጲያ ውስጥ ሊታይ ይችላል:: የተጎጂ ቤተሰቦችንም በዚህ ተስማምተው እንዲፈርሙ ለማድረግ ሊሞክር ይችላል:: ነገር ግን፣ የአሜሪካ ህግ ለእንደዚህ ዓይነት ጉዳዮች የሚሰጠው ተኩረት ከፍተኛ ነው:: አጥፊዎች ላይ ጠንከር ያለ እርምጃ ይወስዳል:: ለተጎጂዎችም ጠቀም ያለ ካሳ ይበይናል።

# የሱዳኑ አልበሽር አምባገነናዊ...

ከገጽ 4 የዞረ

መልክ ይዞ፣ ለሦስት አስርት ዓመታት ሥልጣን የቆዩትን አልበሽር ለእስር በመዳረግ ተጠናቋል:: ተቃውሞው ሰላማዊ ሆኖ የጀመረ ቢሆንም፣ መንግስት በወሰደው እርምጃ ከ45 እስከ 60 የሚጠጉ ሰላማዊ ሰልፈኞች ለህልፈተ ህይወት ተዳርገዋል፤ እንዲሁም በመቶዎች የሚቆጠሩ ደግሞ፣ ለእስር ተዳርገው ሰቆቃ (ቶርቸር) ተፈፅሞዋል::

ፕሬዚዳንት አልበሽር ስልጣን እንዲለቁ ለወራት ተቃውሞ ሲያሰሙ የነበሩ በርካታ ሱዳናውያን፣ የሀገሪቱ ጦር እየወሰደ ያለውን እርምጃ ተከትሎ አደባባይ በመውጣት ደስታቸውን ገልፀዋል:: በእስካሁኑ ሂደት ጦሩ የሀገሪቱን የቀድሞ ምክትል ፕሬዚዳንት እና የገዢ ፓርቲውን መሪ ጨምሮ የተለያዩ የመንግስት ባለስልጣናትን አስሯል:: በአንፃሩ በሀገሪቱ ውስጥ የነበሩ የፖለቲካ እስረኞችን በሙሉ እንደተፈቱም ተገልጿል::

የሱናንን ተቃውሞ የመራው "የሱዳን ባለሙያዎች ማህበር (ሱዳን ፕሮፌሽናልስ አሶሴሽን)" የሚባል የሲቪክ ተቋም ሲሆን፣ አልበሽርን በሰላም ለማውረድ ሰላማዊ የእምቢተኝነት አመፆችን አካሄዷል:: በዚህም ሂደት የስራና የትምህርት ማቆም አድማዎች፣ ቤተ መንግስትን ከቦ መቀመጥን የመሳሰሉ እርምጃዎችን ወስዶ፣ የሀገሪቷን የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ እስከማቆም ደርሷል::

የአልበሽርን መውረድ ተከትሎ፣ የሱዳን ባለሙያዎች ማህበር ባወጣው መግለጫ "ስልጣን የያዙት ወታደሮች ህዝባዊ መንግስት እንዲቋቋም አሁኑኑ መፍቀድ አለባቸው" በማለት አዲሱን ወታደራዊ መንግስት ተቃውሟል:: በወታደራዊ መንግስቱ ምትክም፣ በገለልተኛ ወገኖች የሚመራ የባለአደራ መንግስት እንዲቋቋም ጠይቋል:: የባለአደራው መንግስት እድሜም 4 ዓመታት መሆን ይገባዋል ብሏል:: ይህ እስከሚሆን ድረስም፣ በጎዳና ላይ ተቃውሞው እንደሚቀጥልበት አስጠንቅቋል::

በአልበሽር የስልጣን ዘመን፣ ደቡብ ሱዳን ከሰሜን ሱዳን የተገነጠለች ሲሆን፣ እንዲሁም ኤርትራ ከኢትዮጵያ መገንጠሏ ይታወሳል:: በሁለቱም ሂደቶች አልበሽር ቁልፍ ሚና እንደተጫወቱ የፖለቲካ ተንታኞች ይናገራሉ:: ወደ ስልጣን ካመጧቸው የእስልምና አክራሪዎች ጋር የቅርብ ቁርኘት እንዳላቸው የሚነገርላቸው አልበሽር፣ ደቡብ ሱዳን ከሰሜን ሱዳን እንድትገነጠል ያደረጉት እስላማዊ ሪፖብሊክ ለመመስረት በማቀድ እንደሆነ ይነገርላቸዋል:: ከደቡብ ሱዳን መገንጠል በኋላ፣ ሰሜን ሱዳን ሙሉ ለሙሉ እስላማዊ ሀገር ሆና የሸሪያ ህግ ታውጆባታል::

በአባይ ጉዳይ አልበሽር የኢትዮጵያ የቅርብ ደጋፊ ሆነው የቆዩ ሲሆን፣ አዲሱ መንግስት በዚያው አቋሙ መቀጠሉና አለመቀጠሉ አይታወቅም:: ሆኖም፣ ስልጣን በያዘ ጥቂት ሰዓታት በኋላ ባወጣው መግለጫ "ከጎረቤት ሀገራት ጋር ያለን ወዳጅነት እንደቀድሞው ይቀጥላል" ብሏል:: ግብፅ የአልበሽርን መንግስት ለመጣል ውስጥ ውስጡን አበክራ ስትሰራ ከመቆየቷ አንፃር፣ ከአዲሱ መንግስት ጋር ለመወዳጀት ፈጥና ትንቀሳቀሳለች ተብሎ ይጠበቃል:: በአባይ ጉዳይ፣ ግብፅና ሱዳን አጋር ከሆኑ፣ የኃይል ሚዛኑ ወደ አባይ ግድብ ተቃዋሚዎች እንደሚያዘነብልና ኢትዮጵያን እንደሚጎዳት የፖለቲካ ታዛቢዎች ይናገራሉ::

# በአፍሪቃ የሕንድ እና ...

ከገጽ 17 የዞረ

ካበደረችው ገንዘብ ጋር ሲነፃፀር ኢምንት ነው:: ቻይና ከ2000-2016 (እ.አ.አ.) ለአፍሪቃ ሀገራት 124 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር በብድር ሰጥታለች:: ሕንድም ልክ እንደቻይና ብድሩን ስትሰጥ፣ ሀገራቱ ለፕሮጀክቶቹ ሥራ በዋነኝነት የሕንድ ኩባንያዎችን እና በሕንድ የተመረቱ ዕቃዎችን እንዲጠቀሙ የሚያስገድድ ቅድመ-ሁኔታ ታስቀምጣለች::

ቻይና ከጊዜ ወደጊዜ እያደገ የመጣው የአፍሪቃ ወታደራዊ እንቅስቃሴዋ፣ በአህጉሪቷ ከሕንድ የበለጠ መቆናጠጫ መሬት ይሰጣታል:: ቤይጂንግ በአፍሪቃ የመጀመሪያዋን ወታደራዊ የጦር ሰፈር የገነባቸው ባለፈው የፈረንጆች ዓመት በአፍሪቃ ቀንዷ ሀገር፣ ጂቡቲ፣ ነው:: ሕንድ፣ ቻይና ከስሪ ላንካ፣ ከማልዲቭ ደሴቶች እና ከሌሎች አጐራባቾቿ፣ እንዲሁም በሕንድ ውቅያኖስ ምዕራባዊ ጠርዝ ከምትገኘው ጂቡቲ ጋር ያላት ኢኮኖሚያዊም ሆነ ሌላ ዓይነት ግንኙነትን የምትመለከተው በጥርጣሬ ዓይን ነው፤ ሕንድ ይህን አካባቢ የተጽዕኖ ክልሏ አድርጋ የመመልከት ዝንባሌ አላት::

## ቻይናን መቋቋም

ታዲያ፣ ሕንድ፣ ቻይና በሕንድ ውቅያኖስ እያስፋፋች እና እያጠናከረች ያለውን ጂኦፖለቲካዊ ይዞታዋን ከራሷ ብሔራዊ ጥቅም ጋር ለማመጣጠን ምን ማድረግ ትችላለች? ቻይናን ራሷ በምትከተለው ጨዋታ ለማሸነፍ መሞከሩ የማይቻል እና የማይመከር ነው:: ይሁን እንጂ፣ የኒው ዴልሂ አስተዳደር በሕንድ እና በጃፓን መካከል የተፈረመውን እና "የእስያ-አፍሪቃ የእድገት ኮሪዶር" በሚል መጠሪያ የሚታወቀውን የኢኮኖሚ ትብብር ስምምነት ዳግም ነፍስ እንዲዘራ ማድረግ ይችላል:: ሕንድ ይህን የኢኮኖሚ ትብብር ስምምነት በመጠቀም፣ የሕንድ እና የጃፓን ኩባንያዎች በስምምነቱ የሚተገበሩ ፕሮጀክቶች ተጠቃሚነታቸው እንዳለ ሆኖ፣ የአፍሪቃ ሀገራት እውነተኛ እና ትክክለኛ እድገት የሚያስመዘግቡበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይጠበቅባታል::

ከዚህ በተጨማሪም፣ ሕንድ በፖለቲካው መስክ ለአፍሪቃ ሀገራት እገዛ ማድረግ ትችላለች:: ቻይና የልማታዊ መንግሥት ካፒታሊዝምን እና ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝን ስትከተል እና የዩ.ኤስ. አሜሪካ ዴሞክራሲ ለሌሎች ሀገራት የሚሰጠው ትኩረት ሲቀንስ፣ የአፍሪቃ ልማት ባንክ ፕሬዚዳንት አኪንዉሚ አዴሲና እንደተናገሩት፣ ሕንድ "ለቀረው ዓለም የምታበራ የዲሞክራሲ ብርሃን" መሆን ትችላለች:: በርካታ የአፍሪቃ ሀገራት ድኽነትን እና የመብት ጥያቄዎችን ጨምሮ፣ የተፋጠጧቸውን በርካታ ችግሮች በተመለከተ፣ ከቻይና ፈላጭ ቆራጭ ፖለቲካ ይልቅ፣ ከሕንድ በሐውርታዊ ዴሞክራሲ ጋር እጅጉን ይመሳሰላሉ::

በስተመጨረሻም፣ ሕንድ ከሱዳን እስከደቡብ አፍሪቃ ድረስ ባለው የአፍሪቃ ምሥራቃዊ የባሕር ጠረፍ የደኅንነት አጀንዳዋን በማጠናከር፣ እንዲሁም ዩ.ኤስ. አሜሪካ፣ ጃፓን እና አውስታራሊያ ከታቀፉበት እና "ኩዋድ" በሚል መጠሪያ ከሚታወቀው የደኅንነት ጥምረት ጋር የገባችበትን እሰጥ አገባ በመፍታት፣ ቻይና በሕንድ ውቅያኖስ ያላትን የባሕር ኃይል የበላይነት ለመቋቋም መንቀሳቀስ ትችላለች:: ጠቅላይ ሚኒስትር ናሬንድራ ሞዲ ሀገራቸው፣ ሕንድ፣ እና ቻይና ለእስያ አህጉር የተሻለ መጻኢ ሕይወት በጋራ መሥራት እንደሚችሉ ተስፋ ቢያደርጉም፣ የሁለቱን ሀገራት ግንኙነት ለማሻሻል ጠንክረው መሥራት ይጠበቅባቸዋል::

## እንደመደምደሚያ

ቻይና አፍሪቃ ውስጥ ባላት የተለያዩ እንቅስቃሴዎች፣ ሕንድ ብዙውን ጊዜ ትኩረት ሲሰጣት አይስተዋልም:: ይሁን እንጂ፣ ሕንድ ቱርክን እና ብራዚልን ከመሰሉ ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት እያስመዘገቡ ከሚገኙ የዓለማችን ሀገራት ጋር በመሆን፣ ለአፍሪቃ አህጉር ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ እድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያደረገች ትገኛለች:: እነኝህ መስተጋብሮች በጋራ ምዕራባውያን ሀገራት በአፍሪቃ ያላቸውን እንቅስቃሴ፣ ወደተመልካችነት ደረጃ ዝቅ እያደረጉት ነው:: ይሁን እንጂ፣ ሕንድ በአፍሪቃ ላለው ለውጥ ትኩረቷን እስካልሰጠች ድረስ፣ በሕንድ ውቅያኖስ ጂኦፖለቲካ ትልቁን እና ወሳኙን ሚና የምትጫወተው ቻይና እንደሆነች መዘለቋ አይቀርም::

# የሥራ እና የግል ሕይወታችንን...

ከገጽ 18 የዞረ


ከፍቅረኛችን/ከባለቤታችን፣ ከቤተሰባችን ወይም ከወዳጆቻችን ጋር በጋራ የምናከናውናቸውን ሽርሽር፣ ዳንስ ወይም ሥልጠና የመሰሉ ነገሮችን መምረጥ እንችላለን::

• **በበጎ ፈቃደኝነት ሥራ መሰማራት፡-** በተቻለ መጠን ራሳችንን በተለያዩ ድርጊቶች ወይም ኃላፊነቶች መወጠር የለብንም:: ይሁን እንጂ፣ በዘርፉ የተካሄዱ ጥናቶች እንደሚጠቁሙት፣ በበጎ ፈቃደኝነት ሥራ መሰማራት የሥራ እና የግል ሕይወታችንን በማመጣጠኑ ረገድ እገዛ ያደርጋል:: ይህ ዓይነቱ አካሄድ ድካማችንን እና ውጥረታችንን ሊያቃልልን ይችላል:: ከዚህ በተጨማሪም፣ ሥነ-ልቦናዊ እና አካላዊ ጤንነታችንን ያሻሽልልን ይችላል::

• **እርስ በርስ መደጋገፍ፡-** ቤተሰባዊ ችግር ሲፈጠር በሥራ ቦታችን ያለብንን ወይም የተሰጠንን ኃላፊነት ሊሸፍኑልን ከሚችሉ የሥራ ባልደረቦቻችን ጋር ጥሩ ግንኙነት ሊኖረን ይገባል፤ እኛም በተራችን ይህንኑ ልናደርግላቸው ዝግጁ መሆን ይጠበቅብናል::የቤት ውስጥ ኃላፊነታችንን በአግባቡ መወጣት የሚችሉ የታመኑ ወዳጅ ዘመዶችን ማፍራት ይጠበቅብናል::

## መልስ

1. ጆን ኤ. ማክዶናልድ
2. ፉጂ
3. ሜክሲኳዊው ካርሎስ ስሊም
4. ጉያና
5. ፔላግራ



መምህር መዘምር ወ/ ሩፋኤል

# የዘመናት ጩኸት!!!

## “አቤቱ፣ እኔ ስጮኽ የማትሰማው እስከ መቼ ነው?” (ዕን. 1÷2 )

### “ባለቤት ካልጮኸ ጐረቤት አይደርስም”

“ባለቤት ካልጮኸ ጐረቤት አይደርስም” ይላሉ አበው:: ደራሽ ባይኖርና ሰሚ ባይገኝ እንኳ ብሶት ያለበት ሰው መጮኹ የማይቀር ጉዳይ ነው:: ዓለማችን ግፈኞች የበዙባት፣ ክፉዎች የበረቱባት እንደ መሆኗ መጠን፣ መልስ አልባ ጩኸት የሚጮኹ የበረከቱባት የክፉት ዓለም ናት:: ሐዋርያው ዮሐንስ በመልእክቱ “ዓለምም በሞላው በክፉው እንደ ተያዘ እናውቃለን” ያለው ለዚህ ነው (1ዮሐ.5÷19)::

ይልቁንም እንደ መጥምቁ ዮሐንስ ክፉዎችን የመገሠጽ፣ ግፈኞችን ሃይ የማለትና ስግብግቦችን የመቃወም ኃላፊነት የተጣለባት፣ ከእውነት ጋር የመተባበር መርኅን በመከተልም ለእውነተኛ ፍትሕና ሥነ ግምባር ቀደም መሆን ከሚገባት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሳይቀር ፍትሕ ጉድሎ፣ ብልሹ አሠራር ሰፍኖ፣ ሙስና ተንሰራፍቶባት ሲታይ ከምንም በላይ ይቈጫል:: ጥንታዊት፣ ታሪካዊትና ሐዋርያዊት ስለመሆኗ ለዘመናት በተነገረላት ቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ ባለፉት ዓመታት ብዙ ዓይነት ግፍ ስለመፈጸሙ ብዙ ተብሏል::

ይህ ሊሆን የቻለው ስግብግቦችና ከልክ ያለፈ ራስ ወዳድነት የተጸናወታቸው አንዳንዶች በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ፈላጭ ቆራጭ ሆነው ስለቆዩ ነው:: ከዚህ የተነሣ በቅን ልቦና፣ በበጎ ሕሊና የሚሠራ የለውጥ አካል ቢገኝ እንኳ፣ ለዘመናት የለመዱትን ሰዎች ተቋቁሞ ለውጡን እውን ማድረግ ከባድ ነው:: ከሁለት ወራት በፊት ለአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ዋና ሥራ አስኪያጅነት የተሾሙት አባት፣ ኃላፊነቱን ለመቀበል ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀናትን ያስቈጠሩበት ምክንያትም ይኸው እንደ ሆነ ተነግሯል::

ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከተናገሯቸው ወርቃማ ቃላት መካከል፡- “ኦርቶዶክስ ማለት ሀገር ናት” ሲሉ ከፍታዋን የገለጹበት አገላለጽ ይገኝበታል:: እናት ደግሞ ልጆቿን ሁሉ በእኩል ዓይን ማየት፣ በፍቅር መሰብሰብ ይጠበቅባታል:: ባለፉት ሁለት ዐሥርት ዓመታት በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ በግልጽ የታየው እውነት ቢኖር፣ ከላይ የተገለጸውን ወርቃማ ታሪክ የሚያደበዝዝ፣ በጎ ገጽታዋን የሚያጠለሽ ተግባር ሆኖ ታይቷል:: “መቄዶንያ” የተባለው በጎ አድራጎት በየመንገዱ የወደቁትን ወገኖች፣ ሃይማኖትና ብሔር ሳይለይ እየሰበሰበ ባለበት ዘመን፣ የቤተ ክርስቲያኒቱ አገልጋይ የሆኑት ግን፣ አንዳንዶች በፍትሕ እጦት ሲራቡ፣ አንዳንዶች ደግሞ ከነአስኬማቸው (ቆባቸው) እና መስቀላቸው በየመንገዱ ሲለምኑና ምእመናንን ሲያሳቅቁ ማየት ከተለመደ ቆይቷል:: ይህ ሁሉ ሊሆን የቻለው ቤተ ክርስቲያኒቱ ገንዘብ አጥታ ሳይሆን፣ ሀብት ንብረቷ የጥቂቶች መጠቀሚያና መበልጸጊያ እየሆነ በመምጣቱ እንደ ሆነ ብዙዎች ይስማሙበታል::

ብልሹ አሠራር፣ ዘርፈ ብዙ የሆነ ሙስናና፣ የሥነ ምግባር ችግር፣ ዘረኝነትና ወዘተ. የመንሰራፋቱን ነገር ማንም ያውቀዋል:: በሙስናና አስተዳደራዊ ችግር የተማረሩ ካህናትና ምእመናን ድርጊቱን በተቃወሙ ቍጥር፣ ካህናቱንም ሆነ ምእመናኑን፣ “ቀድሶ መሄድና ቤተ ክርስቲያን ተሳልሞ መሄድ እንጂ፣ አስተዳደር ውስጥ ምን አገባቸው” በሚል ፈሊጥ፣ የቤተ ክርስቲያኒቱ ሀብትና ንብረት የጥቂቶች መበልጸጊያ እንደ ሆነ ለዘመናት መዝለቁ የማይካድ ሐቅ ነው::

በተለይም ጥያቄ የሚያነሡትን ካህናት ከሥራ ገበታቸው እንዲፈናቀሉና ከነቤተሰባቸው በረሃብ እንዲቀጡ ማድረግ፣ እንደ ማንኛውም ዜጋ መብታቸውን በሕግ እንዳያስከበሩ እንኳ፣ “ቀዳሽ አወዳሽ” የሚል ሕግ ወጥቶባቸው፣ በአለቆቻቸው ቸርነት ብቻ እንዲኖሩ የተለየ በደል ተፈጽሞባቸዋል:: በዚህ ልዩ ቀንበር ምክንያት መብታቸው የተገፈፈባቸው ካህናት በሙሉ በየጊዜው እየጮሁ ቢሆንም፣ መልስ አልባ ሆነው በርካታ ዓመታት ተቈጥረዋል::

### ከባድ ዋጋ የሚያስከፍለው መንገድ

የዚህች አንሥተኛ መጣጥፍ አቅራቢ፣ ከ1980ዎቹ አጋማሽ ጀምሮ በአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ስር በሚገኙና ከአንድ ደርዘን በላይ በሚሆኑ የተለያዩ አድባራት ተዟዙሬ ሠርቼአለሁ:: በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ የሚታዩትን ብልሹ አሠራሮች መቃወምም ሆነ ማጋለጥ ከባድ ዋጋ እንደሚያስከፍልም አረጋግጬአለሁ:: በዚህ ዙሪያ ያለውን የቤተ ክርስቲያኒቱ ችግር በአንዳንድ መጻሕፍቶቼ በመግለጼ የከፈልኩትን ዋጋም እኔ ብቻ ሳልሆን ብዙዎች ያውቁታል:: ከተሰደዱት ጋር የተሰደድኩ፣ ከሥራ ገበታቸው እንዲባረሩ ከተደረጉት ጋር የተባረርኩ እንደ መሆኔ፣ የካህናቱን ሰቆቃ በቅርበት አውቀዋለሁ::

ስለ ፍትሕ መጓደልና ምእመናን ከጉድለታቸው የሚለገሱት ሀብትና ንብረት ያለ አግባብ መባከን አስመልክቶ ወዘተ. ድርጊቱን በይፋ ማውገዝና መቃወም የተጀመረው ከሃያ ዓመታት በፊት ነበር::በዚህ እንቅስቃሴ ውስጥ በርካታ ብፁዓን አባቶችና የቤተ ክርስቲያኒቱ ኃላፊዎች ጭምር ተሳትፈውበት እንደ ነበርም አውቃለሁ:: በዚህ ተሳትፎ ውስጥ አሉ የተባሉት የቤተ ክርስቲያኒቱ ሠራተኞች ሁሉ “አሳደህ በለው” የሚል አዋጅ ታውጆባቸው ከሥራ ገበታቸው እንዲባረሩ መደረጉን አስታውሳለሁ:: አንዳንዶችም በረሃብ እንደ ተቀጡ፣ ለኅልፈተ፣ ሕይወት የተዳረጉ ነበሩ:: አስተዳደራዊና መንፈሳዊ ችግሮች በአንድ ላይ ተጣምረው ቤተ ክርስቲያኒቱ ወደ ፊት እንዳትራመድ በብዙ መልኩ ወጥመድ ሆነውባት እነሆ እስከ ዛሬ ድረስ ዘልቋል:: “እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይበቀል” ዓይነት አመለካከት ያለውና በግል ጥቅም የታወረ ካልሆነ በቀር፣ ይህን እውነት የሚክድ ይኖራል ብዬ አላስብም::

> “
>
> **የዚህች አንሥተኛ መጣጥፍ አቅራቢ፣ ከ1980ዎቹ አጋማሽ ጀምሮ በአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ስር በሚገኙና ከአንድ ደርዘን በላይ በሚሆኑ የተለያዩ አድባራት ተዟዙሬ ሠርቼአለሁ**

“ማን ያርዳ የቀበረ፣ ማን ይናገር የነበረ” ነውና፣ ባሳለፍናቸው ዓመታት በርካታ የቤተ ክርስያኒቱ ልጆች በግፍ ከሥራ ገበታቸው እንዲባበሩና በእነርሱ ምትክ ሌላ ሰው እንዲመደብ እየተደረገ በረሃብ እንዲሰቃዩ ሆነዋል:: አንዳንዶችም ተስፋ ቆርጠው፣ አገር ጥለው እስከ መሰደድ ደርሰዋል:: በበርካታ ሚዲያዎች እንደ ተዘገበው፣ በቀርብ ጊዜ ብቻ እንኳ ከ300 በላይ የሚሆኑ የቤተ ክርስቲያኒቱ አገልጋዮች ፍትሕ አጥተው፣ ለብዙ ዓመታት ከሥራ ገበታቸው ተፈናቅለው የመቆየታቸው ነገር፣ ለዘመናት በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ሰፍኖ የነበረው ብልሹ አሠራርና ሙስና ያስከተለው ችግር ስለ መሆኑ በግልጽ ተነግሯል:: እነዚህ በወቅቱ የነበሩት ኃላፊዎች አገልጋዮችን ማፈናቀል፣ ምእመናንን ማስመረር ብቻ ሳይሆን፣ ቤተ ክርስቲያኒቱንም ባለ ዕዳ የማድረጋቸው ነገር ብዙዎችን ያሳዘነ ጉዳይ ሆኗል::

ከላይ በቍጥር የተገለጹት ተፈናቃይ ካህናትም ቢሆኑ፣ ሀገራዊ ለውጡን ተከትሎ ለአጭር ጊዜ ብቻ ተቋቁሞ በነበረ አጣሪ ኮሚቴ ስማቸው ተመዝግቦ የተገኘ እንጂ፣ በዚህ ዝርዝር ውስጥ ያልተካተቱና በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ አገልጋዮች አሁንም ድረስ በፍትሕ እጦት እያለቀሱ ናቸው:: “ማየት ማመን ነው” እንደሚባለው፣ ይህን እውነት ለማረጋገጥ የሚፈለግ አካል፣ አዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ጽ/ ቤት በራፍ ላይ በየቀኑ የሚርመሰመሰውን አቤት ባይ መጥቶ መመልከት ይችላል:: ሲኖዶሱ “ቤተ ክርስቲያን በከፈተችው የይቅርታ መድረክ” በሚል ወደ ሀገረ ስብከቱ ጸ/ ቤት ደባደቤዎችን ቢጽፍም፣ እስካሁን ፍትሕ እንዳጡ ለስምንት ወራት እያነቡ ያሉት ካህናት ብዙ ናቸ:: በጥቂቱ እንጀራ የወጣላቸው አንዳንዶችም ቢሆኑ፣ ምክንያተ ነገሩ ሀገራዊ ለውጡ ነውና፣ “ዶክተር ዐቢይ ልጅ ይወጣለት” በማለት እንዲመርቁ አስችሏቸዋል:: ስለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሀገራዊ ባለ ውለታነት በጥዑም አንደበታቸው የመሰከሩት ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አህመድ፣ በቃላት ብቻ ሳይሆን በተግባር ለዚህች ቤተ ክርስቲያን ሲበዛ ባለ ውለታ፣ ባለ ታሪክም ስለመሆናቸው በሥራቸው አስመስክረዋል::

### የውስጥና የውጭ ሲኖዶስ

ቤተ ክርስቲያናችን ከሃያ ዓመታት በላይ ለሁለት ተከፍላ (የውስጥና የውጭ ሲኖዶስ) በሚል ያሳለፈችው አስቀያሚ ታሪክ ተወግዶ፣ በአዲስ ታሪክ እንዲለወጥና ወደ ቀድሞ አንድነቷ እንድትመለስ እግዚአብሔር የተጠቀመባቸው ሰው ናቸውና ክብር ይገባቸዋል:: የ2011 ዓ.ም የጥምቀትን በዓል አስመልክቶ በቤተ ክርስቲያኒቱ አዘጋጅነት በየአደባባዩ ይታዩ የነበሩት ትልልቅ ማስታወቂያዎች ያስረዱትም ባለ ውለታነታቸውን ነው:: ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ በመሃል፣ ሁለቱ ፓትርያርኮች በቀኝና በግራ ሆነው፣ “በተፋቅሮ ዐቢይ ፍቅር እስመ ተደመሩ- በዐቢይ ፍቅር ተዋሕደዋልና” ተብሎ የተጻፈበት ይገኛል::

ይሁንና ከላይ እንደ ተገለጸው “ኦርቶዶክስ” ማለት ሀገራዊ ውለታዋ እጅግ የላቀ መሆኑ እየታወቀ፣ የገዛ አገልጋዮቿ በረሃ ሲቀጡና ሙሰኞች ሲቀናጡ ዝም ብሎ ማየትስ ተገቢ ይሆን? ይህ ድርጊት የቤተ ክርስያኒቱን ክብርና ዝና ዝቅ አያደርግ ይሆን? ኃላፊነት የተጣለብን ሰዎች፣ የክህናቱ ለቅሶና ኃዘን የማይሰማን እስከ መቼ ነው? “የቤተ ክርስቲያኒቱ ሀብትና ንብረት በግለሰቦች እየተዘረፈ ነው” እያለ ለሚጮኸው ምእመን መፍትሔ መሆን ያቀተንስ ምስጢሩ ምን ይሆን? በቅጣዩ መጣጥፌ በስፋት የምመለስበት ቢሆንም፣ ከላይ በግርድፉ የነካካኋቸው የቤተ ክርስቲያኒቱ ዋና ዋና ችግሮች መንስኤያቸው ተጠያቂነት ስስ የሆነበት አሰራር ነው::

እስካሁንም ድረስ ጉዳያቸው እልባት ያላገኘው የቤተ ክርስቲያኒቱ ልጆች፣ ቃላት የማይገልጸው በደል እንደ ተፈጸመባቸው ወራትና ዓመታትን ለማስቈጠር ተገደዋል:: ይህ ሊሆን የቻለውም፣ የተበላሸ አሰራር በመስፈኑ ምክንያት እንደ ሆነ የአደባባይ ምስጢር ነው::

ብዙዎች አደባባይ ወጥተው እንዲጮኹና ባለፉት ተከታታይ ወራት “የመንግሥት ያለህ!” በማለት በመንግሥታዊ ተቋማት ሳይቀር እየዞሩ የብሶት ድምፃቸውን እንዲያሰሙ ግድ የሆኖባቸውም ይኸው ነው:: ሙስና የሰፈነበትን ብልሹ አሠራር የሚቃወም የቤተ ክርስቲያኒቱ አባል፣ ያለ ስሙ ስም እየተሰጠ፣ ያለ ወንጀሉ እንደ ወንጀለኛ እየተቈጠረ፣ በብዙ መልኩ እንዲገፋ ማድረግ የተለመደ አሠራር ሆኖ ቆይቷል:: ለዘመናት በተዘረጋው የድለላ መረብ በኩል ዳጎስ ያለ ገንዘብ ማቅረብ የማይችል የቤተ ክርስቲያኒቱ አገልጋይም፣ ዕደገቱ ቀርቶ የተመደበለትን ወርኃዊ ደመወዝ በአስተማማኝ ሁኔታ እንዳያገኝ እየተደረገና እላዩ ላይ ሌላ ሠራተኛ እየተመደበበት ደም ዕንባ ያለቀሰውን ሠራተኛ ቤቱ ይቍጠረው:: በሙስና በተቃኘው የዘመናት ብልሹ አስተዳደር ምክንያት “ሀገር” የሆነችው ቤተ ክርስቲያን፣ ስሟም ሆነ የቆየ ክብርና ዝናዋ፣ ባሉታዊ መልኩ እንዲነሣ አድርጓል ማለት ይቻላል:: በመሆኑም ይህን ታሪክ የሚቀይር አስተዳደር ለማግኘት የብዙዎች ምኞትና ጸሎት እንደ ሆነ ቀጥሏል:: ከዚህ በኋላ ባለው ዘመንም ከመጥፎ ረብ የፀዱ፣ በክርስቶስ ደም ከወገንና ከቋንቋ ሁሉ ለተዋጀች ቅድስት ቤተ ክርስቲያን (1ጴጥ. 5÷2፤ ራእ.5÷9-10) በቅን ልብ፣ በኃላፊነት የሚሠሩ ሰዎችን ይፍጠርልን ከማለት በቀር ያለፈው ጊዜ ብዙዎችን ያስመረረ ስለመሆኑ ያለ ማቋረጥ ተነግሯል::

ከላይ እንደ ተገለጸው፣ ርእሰ ጉዳዩን የመግቢያ ያህል በግርድፉ ነካካሁት እንጂ፣ በቀጣዩ በስፋት የምመለስበት ይሆናል:: ይኸ ያስፈለገበት ምክንያትም፣ በቀጣዮቹ ዘመናት የትናንቱ ብልሹ አሠራር እንዳይደገም ትምህርት ይሆን ዘንድ ለማሳሰብ ነው:: “አቤቱ!... ዘመናችንን እንደ ቀድሞ አድስ::” (ሰቆ. ኤር. 5÷21):: ይቆየን:: ይቀጥላል::.....

## አልኮል ማስተዋወቅ የሚከለክለው ህግ ከ2 ወር በኋላ ተግባራዊ ይሆናል

አልኮልን በብሮድካስት ማስተዋወቅ የሚከለክለው ህግ ከግንቦት 21 ጀምሮ ተፈጻሚ እንደሚሆን ተገለፀ። ይህን የሚደነግገው የምግብ እና የመድኃኒት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1112፣ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ የካቲት 21 ቀን 2011 ዓ.ም ታትሞ መውጣቱ ይታወሳል። አዋጁ ቁጥር 1112 ባሳለፍነው ጥር 28 ቀን 2011 ዓ.ም በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መፅደቁ ይታወሳል።

በአዋጁ አንቀጽ 74(4) መሰረት የአልኮል መጠጥ በቴሌቪዥን እና ሬድዮ አማካኝነት ማስተዋወቅ ተከልክሏል፡፡ በዚሁ መሰረት፣ ማንኛውም የአልኮል መጠጥ ማስታወቂያ የሚያስተላልፉ ሚድያዎች ለህጉ ተፈጻሚነት ተገቢውን ዝግጅት እንዲያደርጉ ማሳሰቢያ ተሰጥቷቸዋል፡፡ እንዲሁም፣ እድሜያቸው ከ21 ዓመት በታች ለሆኑ ሰዎች የአልኮል መጠጥ መሸጥን የተከለከለ ሲሆን፣ በኢትዮጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲ በጸደቀው ደረጃ መሰረት ትክክለኛው የአልኮል መጠን 0.5 እንዲሆን ግዴታ አስቀምጧል።

ከዚህ በተጨማሪም የአልኮል መጠጥን ከሎተሪ እጣ ወይም ከሽልማት ጋር በማያያዝ፣ በቢልቦርድ ማስተዋወቅ ተከልክሏል፡፡ በተጨማሪም እድሜው ከ21 አመት በታች ለሆነ ሰው የትንባሆ ምርትን መሸጥ፣ ወይም ከ21 አመት በታች በሆነ ሰው እንዲሸጥ ማድረግም በአዋጁ የተከለከለ ተግባር ሆኗል።

# በአዲስ አበባ ወጣቶች ማህበር ብሔር ተኮር ለውጥ እየተደረገ ነው ተባለ

ከ21 ዓመታት በፊት « መደራጀት ኃይል ነው» በሚል መሪ ቃል የተቋቋመው የአዲስ አበባ የወጣቶች ማህበር የቦሌ ክፍለ ከተማ የቀድሞው አመራር፣ በታከለ ኡማ ከሚመራው የአዲስ አበባ አስተዳደር ጋር ከፍተና ውዝግብ ውስጥ ገብቷል:: የአዲስ አበባ ወጣቶች ማህበር የኢህአዴግ አጋር ሲሆን፣ ነፃ ቢባልም እንቅስቃሴውን ሙሉ ለሙሉ የሚቆጣረው ኢህአዴግ ነው::

በህወሓት መራሹ ኢህአዴግ ዘመን የተቋቋመው ይህ ማህበር፣ ከጥር ወር ወዲህ ዘር ተኮር የአመራር ምርጫ በማድረግ፣ የወጣት ማህበሩ በኦሮሞ ተወላጆች በብልጫ እንዲያዝ ተደርጓል የሚል ቅሬታ በቀድሞው አመራር አባላቱ እየቀረበ ይገኛል::

የቀድሞ አመራሩ፣ በቦሌ ክፍለ ከተማ 15 ወረዳዎች በተካሄዱ ጉባኤዎች ላይ ታየ ያለውን የመመሪያና የደንብ ጥሰት አስመልክቶ ለክፍለ ከተማውና ለአዲስ አበባ ወጣቶች ማህበር አቤቱታ አቅርቧል:: እንደ ቀድሞዎቹ አመራሮች ቅሬታ ከሆነ፣ በተለመደው አሰራር መሰረት ሊካሄድ የነበሩ ጉባኤዎች በመንግስት ኃላፊዎች እና በወረዳዎቹ አንዳንድ ስራ አስፈጻሚ አካላት እንዲታገዱ ተደርጓል:: በእገዳውም፣ በክፍለ ከተማው ካለ አንድ ወረዳ በስተቀር የሌሎቹ በሙሉ እንዲራዘም እንደተደረገ ለማወቅ ተችሏል::

ተፅዕኖውን ተቋቁሞ በወቅቱ ጉባኤውን ያካሄደው ወረዳ 2 ሲሆን፣ ጉባኤው ከመካሄዱ በፊት አባላት ላልሆኑ ወጣቶች ጥሪ እንዲያደርግ ቢታዘዝም፣ መግቢያ ላይ ቁጥጥር በማድረግና በጉባኤው ወቅት የተነሱ ረብሻዎችን በማረጋጋት፣ በደንቡ መሰረት ህጋዊ ምርጫ አካሂዷል:: ጉባኤው ሲካሄድ አንዳንድ አባላት ስርአት በጎደለው መልክ፣ “የእኛ ብሄር ለምን ከሌላው በበለጠ ተጠቃሚ አይሆንም?” በማለት ሌሎቹን ለመጨፍለቅ ሞክረዋል::

ከዚህ ወረዳ ውጭ ባሉት የቦሌ ክፍለ ከተማ 14 ወረዳዎች፣ ህጋዊው መንገድ ሳይፈጸም፣ ነባር አመራሮች በጥሪው ወረቀት ብተና ላይ ሳይሳተፉ፣ ከአባላቶቻቸው ቁጥር በላይ የሆነና በወረዳው ነዋሪዎች የማይታወቁ ተሳታፊዎች ተገኝተው ጉባኤዎቹ ተካሂደዋል:: ጥሪው በመንግስት ኃላፊዎች ጣልቃ ገብነት ተካሄዶ እንደነበር የቀድሞ አመራሮቹ ይናገራሉ:: በ3 ወረዳዎች በአይሱዚ የተጫኑ ሰዎች ወደ ጉባኤው ገብተው እንደተሳተፉ በቃለ ጉባኤ ደረጃ ተይዞ በሰነድ ተቀምጦ ይገኛል::

በወረዳ 15 አንድን ብሄር ያተኮረ ጥሪ ተካሂዶ፣ የወረዳው ነዋሪ ያልሆነ ግለሰብ በሰብሳቢነት ተመርጧል:: ከማህበሩ ህግና ደንብ ውጭ አባል ያልሆነ እንዲሳተፍ እየተደረገ፣ ከአባሉ ቁጥር በላይ ተሳታፊዎች እንዲገኙ እየተደረገ አመራሮች ተመርጠዋል የተባለ ሲሆን፣ በጉባኤው ሂደት በግልጽ “እገሌን ምረጥ” እየተባለ የጎሳ ኔትወርክ ተፈጥሯል ተብሏል::

በወረዳ 15፣ ከዘር ተጽዕኖ በተጨማሪ፣ በመታወቂያ አሰጣጥ ላይ ልዩነት ይደረጋል ተብሏል:: “ የማህበሩ መታወቂያ ይሰጠን” ብለን ብዙ ጊዜ የጠየቅን ቢሆንም፣ መልስ የለም፤ አባላቱም በእኩልነት ስለማይታዩ፣ እየተሰጠ ያለው ለውስጥ ሰው ብቻ ነው ብለዋል::

“ይህን በደላችንን እስከ ከንቲባውና ጠቅላይ ሚኒስትሩ ድረስ አቤት በማለት፣ አንድ ብሄር ብቻ እንዲመራ የተደረገብንን አሰራር በመቃወም፣ ጉባኤዎቹ በድጋሚ ተደርገው አሰራሩ እንዲስተካከል ጠይቀናል” ብለዋል የቀድሞ የወረዳ 15 አመራሮች::

በወረዳ 11 ጥሪ ከተደረገላቸው 400 ሌላ የማይታወቁ 500 ሰዎች ተሳትፈው መርጠዋል:: በዚህም ሳቢያ፣ በምክር ቤቱም ካሉ 31 አባላት 17 የኦሮሞ ብሄር ተወላጆች እንዲሆን ተደርጓል:: ስራ የሚበዛባቸው የወረዳው አመራሮች ጭምር የምክር ቤቱ አባልና አመራር በመሆን እንደተመረጡ ለማወቅ ተችሏል::

በወረዳ 7 ደግሞ፣ የወረዳው ወጣት ማህበር የማያቃቸው በምርጫው ተገንተው፣ በዋና ስራ አስፈጻሚና በድርጅት ኃላፊዎች ተጽእኖ በመታገዝ፣ ማህበሩ የመረጠውን በማስቀረት የፈለጉትን መርጠው ቃለ ጉባኤው ሳይጸድቅ ስብሰባውን በትነውታል::

የቦሌ ክ/ከተማ የወጣቶች ማህበር ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ባስገባው ቅሬታ፣ መመሪያና ህገደንብ ተጥሷል በማለት፣ የተከሰቱትን ጥሰቶች በመዘርዘር ምላሽ እንዲሰጠው ጠይቋል::

ከጉባኤው ጥሪ አሰጣጥ ጀምሮ ዝግጅቱ ከማህበሩ አባላት ዕውቅና ውጭ ነው የተፈጸመው ያለው የማህበሩ ማመልከቻ፣ ጉባኤዎቹ የተመሩት በመንግስት አካላት በመሆኑ፣ የድርጅት ጣልቃ ገብነት አለው ብሏል:: በዚህ ህገ ወጥ ባለው የአመራረጥ ሂደት፣ ዕድሜያቸው ከወጣትነት ያለፉና፣ በማህበሩ አባልነትም ሆነ በአስፈጻሚነት ድርሻ ያልነበራቸው ግለሰቦች በአመራርነት ተመርጠዋል::

ETHIOPIS
on
ኢትዮጲስ
You Tube
Facebook page : ethiopis ኢትዮጲስ

ወደ 20 ዞሯል

አዘጋጅ፡- ማውሮ

# ከፕሪሚየር ሊጉ ለቻምፒየንስ ሊግ የሚያልፉ ቡድኖች ስንት ናቸው?

በፕሪሚየር ሊጉ የደረጃ ሰንጠረዥ ከአንድ እስከአራተኛ የሆኑት ቡድኖች ለቀጣዩ ቻምፒየንስ ሊግ ጠውድድር ዘመን እንደሚያልፉ የታወቀ ነው:: ከዚህ በተጨማሪም፣ የኤፍ.ኤ. ዋንጫ አሸናፊ እና በደረጃ ሰንጠረዡ በአምስተኛ ደረጃ ጀተቀመጠው ቡድን ደግሞ፣ ለአውሮጳ ሊግ ጨዋታዎች ያልፋሉ:: የካራባዎ ዋንጫ አሸናፊም ለሁለተኛው የማጣሪያ ዙር ያልፋል::

ይሁን እንጂ፣ የኤፍ.ኤ. እና/ወይም የካራባዎ ዋንጫዎች አሸናፊዎች በሊጉ በኩል ለአውሮጳ ጨዋታዎች የሚያልፉበት መንገድ ውስብስብ ነው:: በዘንድሮ የውድድር ዘመን ደግሞ፣ ማንቸስተር ሲቲ የሊጉን ዋንጫ በማሸነፉ፣ በፕሪሚየር ሊጉ የደረጃ ሰንጠረዥ በስድስተኛ ደረጃ የተቀመጠው ቡድን በአውሮፓ ሊግ የመጫወት ዕድል ይኖረዋል:: ነገሮችን ይበልጥ ውስብስብ የሚያደርገው ደግሞ፣ የቻምፒየንስ ሊግ እና የአውሮጳ ሊግ አሸናፊዎች በቀጣዩ የውድድር ዘመን የቻምፒየንስ ሊጉ የምድብ ጨዋታዎች ማለፋቸው ነው::

ዋትፎርድ ሲቲ በኤፍ.ኤ. ዋንጫው የፍጻሜ ጨዋታ ማንቸስተር ሲቲን ካሸነፈ፣ ለአውሮጳ ጨዋታ በቀጥታ የሚያልፍ ይሆናል:: ማንቸስተር ሲቲ ካሸነፈ ግን፣ በፕሪሚየር ሊጉ የደረጃ ሰንጠረዥ በሰባተኛ ቦታ የተቀመጠው ቡድን ለአውሮጳ ጨዋታዎች ያልፋል::

እስከ 2015 (እ.አ.አ.) ድረስ በኤፍ.ኤ. ዋንጫው የፍጻሜ ጨዋታ አሸናፊው ቡድን ቀደም ሲል በቻማፒየንስ ሊጉ የመጫወት ዕድል ካገኘ፣ ተሸናፊው ቡድን ለአውሮጳ ጨዋታዎች ማለፍ ይችል ነበር:: ስቶክ ሲቲ እና ሃል ይኸው ሕግ ከመለወጡ በፊት በአውሮጳ ዋታዎች የመሰለፍ ዕድል አግኝተው ነበር:: በአሁኑ ወቅት ግን፣ አንድ ቡድን በአውሮጳ ጨዋታዎች ለመጫወት በፍጻሜው ጨዋታ ማሸነፍ ይጠበቅበታል:: ዋትፎርድ ሲቲ የኤፍ.ኤ. ዋንጫውን የፍጻሜ ጨዋታ ማሸነፍ ከቻለ፣ በፕሪሚየር ሊጉ የደረጃ ሰንጠረዥ በስድስተኛ ቦታ የሚገኝ ቡድን ሐምሌ 25 2019 (እ.አ.አ.) በሚደረገው የአውሮጳ ሊግ የማጣሪያ ጨዋታዎች መሳተፍ ይኖርበታል::

ከቻምፒየንስ ሊጉ የሩብ ፍጻሜ ተፋላሚዎች መካከል ግማሾቹ የእንግሊዝ ቡድኖች ናቸው:: ቡድኖቹም ማንቸስተር ሲቲ፣ ማንቸስተር ዩናይትድ፣ ቶተንሃም ሆትስፐር እና ሊቨርፑል ናቸው::

አንድ ቡድን የአውሮጳ ሻምፒዮን እና በፕሪሚየር ሊጉ የደረጃ ሰንጠረዥ እስከአራተኛ ደረጃ ቢጨርስ፣ በቀጣዩ የውድድር ዘመን ለቻምፒየንስ ሊጉ የሚያልፉ የእንግሊዝ ቡድኖች አራት ብቻ ናቸው:: በዚህ አጋጣሚ በምድብ ጨዋታው በተጨማሪነት የመጫወት ዕድል የሚኖረው የኦስትሪያ ሊግ አሸናፊ ነው:: ይሁን እንጂ፣ የቻምፒየንስ ሊጉ አሸናፊ የእንግሊዝ ቡድን ከሆነ እና ይኸው ቡድን በውድድር ዘመኑ በፕሪሚየር ሊጉ የደረጃ ሰንጠረዥ እስከአራተኛ ደረጃ ድረስ ባለው ቦታ ካጠናቀቀ፣ አምስት የእንግሊዝ ቡድኖች በቀጣዩ የውድድር ዘመን የምድብ ጨዋታ የመሳተፍ ዕድል ይኖራቸዋል::

የአውሮጳ እግር ኳስ ማኅበር የጨዋታ ሕጉን የለወጠው ባለፈው የፈረንጆች ዓመት ነው:: ቶተንሃም በ2012 (እ.አ.አ.) የውድድር ዘመን በፕሪሚየር ሊጉ የደረጃ ሰንጠረዥ በአራተኝነት ቢያጠናቅቅመር፣ ቼልሲ የቻምፒየንስ ሊጉን ዋንጫ በማንሣቱ፣ በአውሮጳ መድረክ የመሰለፍ ዕድል ሳያገኝ ቀርቷል:: አሁን ግን ሕጉ በመለወጡ፣ ቶተንሃም የማለፍ ዕድል ይኖረው ነበር::

አርሰናል እና ቼልሲ በዘንድሮ የውድድር ዘመን ለአውሮጳ ሊግ ግማሽ ፍጻሜ ደርሰዋል:: ሁለቱ የእንግሊዝ ቡድኖች ባኩ በሚደረገው የፍጻሜው ጨዋታ ዋንጫውን ያነሣሉ የሚል ቅድሚያ ግምት ተሰጥቷቸዋል:: ከሁለቱ ቡድኖች መካከል አንዱ የፍጻሜ ጨዋታውን ቢያሸንፍ፣ በቀጣዩ የውድድር ዘመን የቻምፒየንስ ሊጉ የምድብ ጨዋታዎች የመጫወት ዕድል ይኖራቸዋል:: የፍጻሜው ጨዋታ አሸናፊ በፕሪሚየር ሊጉ የደረጃ ሰንጠረዥ ከአራተኛ በታች ሆነው ቢያጠናቅቁ፣ አምስት የእንግሊዝ ቡድኖች በጨዋታው የመሰለፍ ዕድል ይኖራቸዋል::

ይሁን እንጂ፣ የአውሮጳ ሊጉ የፍጻሜ ጨዋታ ያሸነፈው የእንግሊዝ ቡድን ከሆነ፣ የፕሪሚየር ሊጉ ቡድን በአውሮጳ ጨዋታዎች የመጫወት ዕድል የሚኖረውን ትርፍ ክለብ አይኖርም:: በዚህ ምትክ በፈረንሳይ ሊግ አሥስተኛ ደረጃ ያጠናቀቀ ቡድን በአውሮጳ ጨዋታዎች የመሰለፍ ዕድል ይኖረዋል::

## ኦሌ ጉናር ሶልክሻየር

# "ፖል ፖግባ ማንቸስተር ዩናይትድን አይለቅም"

የማንቸስተር ዩናይትድ አሠልጣኝ፣ ኦሌ ጉናር ሶልክሻየር፣ ፖል ፖግባ በዘንድሮ የውድድር ዘመን ክለቡን እንደማይለቅ አስታውቀዋል:: በነሐሴ 2016 (እ.አ.አ.) ከማንቸስተር ዩናይትድ ጋር ዳግም የተቀላቀለው ፈረንሳዊው አማካይ፣ ወደሪያል ማድሪድ ይዛወራል ተብሎ እየተገመተ ነበር::




ሶልክሻየር፣ "ፖል ፖግባ ከቡድናችን ጋር ይቀጥላል:: ፖግባ ምርጥ አቋም ላይ ከሆነ፣ የቡድኑ ሞተር ነው:: በቀጣዩ የውድድር ዘመን ከማንቸስተር ዩናይትድ ጋር እንደሚቀጥል ሊታወቅ ይገባል" ሲሉ ተናግረዋል::

ፖግባ በመጀመሪያው ጨዋታ ከሜዳ በመባረሩ፣ ማንቸስተር ዩናይትድ ከፓሪስ ሳን-ዠርሜን ጋር ባደረገው ጨዋታ ተሰልፎ የመጫወት ዕድል አልነበረውም::

ሆሴ ሙሪኖ ባለፈው ታኅሣሥ ወር ከማንቸስተር ዩናይትድ አሠልጣኝነታቸው ከመባረራቸው በፊት በፖርቱጋላዊው አሠልጣን እና በፖግባ መካከል አለመግባባት ተፈጥሮ እንደነበር ሲዘገብ ቆይቷል:: የቀድሞው የጁቬንቱስ ፈረንሳዊው አማካይ በሶልክሻየር አሠልጣኝነት ሥር በ23 ጨዋታዎች ዘጠኝ ግቦችን አስቆጥሯል::

የማንቸስተር ዩናይትዱ ኖርዌያዊ አሠልጣኝ ሶልክሻየር አያይዘውም፣ "ፖግባ ፍጹም የማንቸስተር ዩናይትድ ተጫዋች ነው:: ፈረንሳዊው አማካይ በትላልቅ ጨዋታዎች ከትላልቅ ተጫዋቾቻችን መካከል አንዱ ነው:: ቀደም ሲል ከፒ.ኤስ.ጂ. ጋር በነበረን ጨዋታ ጥሩ አቋም ላይ እንዳልነበረ ታውቆታል:: የፖግባ ሥራ ጨዋታውን የማሳመር፣ ኳሷን ከባላንጣ ተጫዋቾች መንጠቅ፣ እንዲሁም ግብ የሚሆኑ ኳችን አመቻችቶ መስጠት ነው" ብለዋል::

የዘንድሮ የውድድር ዘመን ሲያበቃ እስከስድስት የሚደርሱ የማንቸስተር ዩናይትድ ተጫዋቾች ክለቡን ይለቃሉ ተብሎ ይጠበቃል:: ከእነኝህም መካከል አንዴር ሄሬራ፣ ዡዋን ማታ እና አሌክሲስ ሳንቼዝ ተጠቃሾች ናቸው::

# አጫጭር ዜናዎች

ማንቸስተር ዩናይትድ ለዌስት ሃም አማካዩ፣ ዴክላን ራይስ፣ በቀጣዩ የበጋ ወቅት ዝውውር 50 ሚሊዮን የእንግሊዝ ፓውንድ ለማውጣት መዘጋጀቱን አስታውቋል::

***

የ20 ዓመቱ የእንግሊዝ ብሔራዊ ቡድን ተሰላፊ ዴክላን ራይስ ቼልሲ በ14 ዓመቱ ከለቀቀው በኋላ ከዌስት ሃም ጋር መቀላቀሉ "የሕይወቱ ትልቁ ውሳኔ" እንደሆነ ተናግሯል::

***

የማንቸስተር ዩናይትድ ረዳት አሠልጣኝ፣ ማይክ ፊላን፣ የ26 ዓመቱ ፈረንሳዊ አማካይ፣ ፖል ፖግባ፣ ኦልድ ትራፎርድን እንዲለቅ የማይፈልጉ መሆኑን ተናግረዋል::

***

ፍራንስ ፉትቦል መጽሔት ፖል ፖግባ በቀጣዩ የዝውውር መስኮት ኦልድ ትራፎርድን ለቅቆ ከሪያል ማድሪድ ጋር እንዲቀላቀል ሐሳብ አቅርቧል::

***

የባርሴሎና ፕሬዚዳንት፣ ጆሴፕ ማሪያ ባርቶሚው፣ ክለባቸው ፖግባን ማስፈረም ቢፈልግም፣ ተጫዋቹ በ2016 (እ.አ.አ.) ጁቬንቱስን እንደለቀቀ ከማንቸስተር ዩናይትድ ጋር መፎካከር እንዳልቻለ ተናግረዋል::

***

የአያክስ አምስተርዳም የግራ መሥመር ተመላላሽ፣ ኒኮላስ ታሊያፊኮ፣ በቀጣዩ የውድድር ዘመን ወደእንግሊዝ ፕሪሚየር ሊግ መዘዋወር እንደሚፈልግ ተናግሯል:: አርሰናል የ26 ዓመቱን አርጀንቲናዊ ማስፈረም እንደሚፈልግ አስታውቋል::

***

ኤቨርተን የ22 ዓመቱን የእንግሊዝ ብሔራዊ ቡድን ተሰላፊውን የበርሚንግሃም ሲቲ አጥቂ፣ ቼ አዳምስ፣ ማስፈረም እንደሚፈልግ ገልጿል::

***

ዌስት ሃም ዩናይትድ በቀጣዩ የዝውውር መስኮት ከ30 ዓመቱ ተጫዋች፣ አንዲ ካሮል፣ ጋር መቀጠል እንደማይፈልግ አስታውቋል:: የእንግሊዝ ብሔራዊ ቡድን አጥቂው ቁርጭምጭሚቱ ላይ በደረሰበት ጉዳት ቀሪ የውድድር ዘመኑን ሳይጫወት ለማሳለፍ ተገድዷል::

***

አንዲ ካሮል ከዌስት ሃም ዩናይትድ ጋር ያለው ውል እንዳበቃ ወደ ዩ.ኤስ. አሜሪካ ሜጀር ሊግ ሊያመራ እንደሚችል ተነግሯል::

***

ዌስት ሃም ዩናይትድ የ28 ዓመቱን የሊቨርፑል እና የእንግሊዝ ብሔራዊ ቡድን ተከላካዩን፣ ናታንኤል ክላይን፣ ለማስፈረም ከቡርንማውዝ ጋር መፎካከሩ አይቀርም::

***

የ24 ዓመቱ የዲ.ሲ. ዩናይትዱ እና አርጀንቲና ብሔራዊ ቡድን አማካይ፣ ሉቺያኖ አኮስታ፣ ማንቸስተር ዩናይትድ ትኩረት ስለሰጠው እንዳስደሰተው ተናግሯል::

***

የ19 ዓመቱ የዌልሽስ እና የፖርቱጋል ብሔራዊ ቡድን የግራ ተመላላሹ፣ ሩበን ቪናግር፣ በሊቨርፑል እና ባርሴሎና የሚፈለግ ተጫዋች ሆኗል::

***

የ24 ዓመቱን ብራዚላዊ የብራጋ ተከላካይ፣ ብሩኖ ቪያና፣ ሌስተር ሲቲ እና ሊድስ ዩናይትድ ሊያስፈርሙት ይፈልጋሉ::

***

የ26 ዓመቱ የቤሌጂየም ብሔራዊ ቡድን አማካይ፣ ቶርጋን ሃዛርድ፣ በ40 ሚሊዮን ዩሮ ቦሩሲያ ሞንቸንግላድባክን ለቅቆ ወደ ቦሩሲያ ዶርትሙንድ ሊቀላቀል ነው::

***